# እ ሰ ይ ፡

እሰይ ፡ እሰይ ፡ እንበል ፡ ለዚህ ፡ ከበቃን ፣
የልጆቻችንን ፡ ጋብቻ ፡ ካየን ።

የመውለድ ፡ ውጤቱ ፡ ፍሬው ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ነው ፣
ካደጉ ፡ ተምረው ፡ ትዳር ፡ ማስያዙ ፡ ነው ።

የጥንቱ ፡ ጋብቻ ፡ እንደምን ፡ ነበረ ፣
ዘር ፡ ይቆጠር ፡ ነበር ፡ ባህል ፡ እየተመረ ፣

ዛሬ ፡ ግን ፡ ቀረና ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጣጣ ፣
እቀበለዋለሁ ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፡ ይምጣ ።

ጋብቻው ፡ በገንዘብ ፡ ይመሠረትና ፣
ዕድሜው ፡ አጭር ፡ ሆኖ ፡ ይቀረዋል ፡ መና ።

የዘመኑ ፡ ፍቅር ፣ የዘመኑ ፡ ሰው ፣
ብናየው ፡ ገላልጠን ፡ ውስጡ ፡ ባዶ ፡ ነው ።

ዐወቀች ፡ ልጃችን ፡ ተመራመረች ፣
በሠርጓ ፡ ምክንያት ፡ ድግሱን ፡ ጠላች ።

አልተሳሳተችም ፡ ጠልቃ ፡ ነው ፡ ያየችው ፣
ለባልና ፡ ሚስቱ ፡ ምንም ፡ አይጠቅማቸው ።

ለደስታው ፡ ምንጩ ፡ እነርሱ ፡ ከሆኑ ፣
ከቶ ፡ ለምን ፡ ይሆን ፡ ሀብት ፡ መባከኑ ?
በሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ ዐውቀውት ፡ ይመኑ ።

ጋብቻ ፡ እንዲጸና ፡ ሕጉ ፡ እንዲፈጸም ፣
ይታሰብ ፡ ይመከር ፡ ፍችው ፡ ይታረም ።



ክፍል ፡ ፲፩ ፡

# ታሪካዊ፡ሥፍራዎችን፡መጎብኘት፡

በሀብት ፡ ደረጃን ፣ በልጆች ፡ አበባ ፡ አጌጥን ። ለመማር፡ ዕድል፡ ባይኖረንም ፡ ማየት ፡ ትምህርት ፡ ስለሆነ ፣ ወጣ ፡ ብለን ፡ ሀገር፡ እንድ ናይ ፡ ለፀሐይ ፡ አማከርኳት ።

ጥሩ ፡ ሐሳብ ፡ አመነጨህ ፣ ለነቡርክት ፡ ብናማክራቸው ፡ አይሻ ልምን ? አለችኝ ፡ ፀሐይ ።

የውጭውን ፡ ዓለም ፡ ቡርክት ፡ ስለምታውቅ ፡ ሐሳባችንን ፡ በበ ለጠ ፡ ታብራራዋለች ፡ ተባባልንና ፡ ጥሪ ፡ ላክን ። በጥሪያችን ፡ መሠ ረት ፡ ቡርክትና ፡ ዕምላዕሉ ፡ ስለመጡ፡ በመከባከብ፡ ተቀበልናቸው ። በአቀባበላችን ፡ ቡርክት፡ ተደነቀችና ፡ እማማ፡ ልጆች ፡ መሆናችንን ፡ ረሳሽ ፡ የተለየ ፡ አቀባበል ፡ የምታደርጊልን ፡ አለቻት ።

ልጄ ፡ የሀገር ፡ ትዝታ ፡ ልንገርሽ ፡ «ባለቤቱ ፡ የናቀውን፡ አሞሌ፡ ባለዕዳ ፡ አይቀበለውም። » እኛ ፡ ካላከበርናችሁ ፡ ሌላው ፡ አያከብራች ሁም ። ደግሞም ፡ ሰውን ፡ ሰው ፡ የሚያከብረው ፡ አይምሰልሽ ። ሰው ፡ የሚከበረው ፡ ራሱን ፡ ያስከበረ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።»

ላቋርጥሽና ፡ እማማ ፡ እንዴት ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ያከብራል ፡ አለች ቡርክት ፣ ስሚ ፡ አለችና ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ የሚያስከብረው ፡ በሚያሳ የው ፡ መልካም ፡ ምግባር ፡ ነው ። ምግባረቢስ ፡ ከሆነ ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ ይናቃል ። አይከበርም ። ልጆቻችንን ፡ የምናከብራችሁ ፡ በምግ ባራችሁ ፡ ነው ፣ ምግባር ፡ ከወንዝ ፡ አይቀዳም ። ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ካለው ፡ ቤተሰብና ፡ ከትምህርት ፡ የሚገኝ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ፀሐይ ፡ መልስ፡ ሰጠቻት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የተጠሩበትን ፡ እንድገልጥላቸው ፡ በዓይን፡ጥቅሻ፡ ምልክት ፡ ሰጠችኝ ፡ ፀሐይ ፡—የምናካፍላችሁ ፡ ሐሳብ ፡ በተለይ፡ ለቡ ርክት ፡ ቀላል ፡ ይሆናል ። እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ዓለም ፡ ሰፊ ፡ ነው ። በስፋት ፡ የተዘረጋው ፡ ዓለም ፡ በሰባት ፡ ተከፍሎ ፡ እስያ ፣ አፍ ሪካ ፣ ኤሮፓ ፣ ሰሜን፡ አሜሪካ ፣ ደቡብ ፡ አሜሪካ ፣ አትላንቲክ ፣ አው ስትራሊያ ፡ ተብሎ ፡ መጠራቱን ፡ የምታውቂት ፡ ነው ።

መቼም ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ ማየት ፡ ራስን ፡ ለማወቅ ፡ ይረዳል ፤ የማያውቁት ፡ ይታወቃል ፤ ጠባብ ፡ የነበረው ፡ አስተያየትም ፡ ይሰፋል ። ስለዚህ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ያለውን ፡ ልጃችንን ፡ ለማየት ፡ ጭምር ፡ ወደ ፡ አሜሪካን ፡ ለመሄድ ፡ አስበናል ፡ አልኳቸው ።

ስለውጭው ፡ ዓለም ፡ በበለጠ ፡ ስለምታውቅ ፡ ብርከት ፡ ትናገር ፤ አለ ፡ ዕምላዕሉ ። ቡርከትም ፡ ሳቅ ፡ አለችና ፡ አባባንና ፡ እማማን ፡ ከልብ ፡ አመሰግናለሁ ። መሠረታዊ ፡ የሆነ ፡ ሐሳባችሁ ፡ የሚደገፍ ፡ ነው ። የፈረንጆችን ፡ ሀገር ፡ ለማየት ፡ ጊዜ ፡ መምረጥ ፡ ያስፈልጋል ።

በክረምት ፡ ወይም ፡ በሙቀት ፡ ወራት ፡ ሳይሆን ፡ ሙቀቱ ፡ መለስተኛ ፡ በሚሆንበት ፡ ክረምቱ ፡ ከመግባቱ ፡ በፊት ፡ ያሉት ፡ ወራቶች፣ የተመረጡ ፡ ናቸው ። ወራቶቹ ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ በየሀገሩ ፡ ስትደርሱ ፡ ልታደርጉ ፡ የሚገባውን ፡ ማጥናት ፡ አለባችሁ ፡ አለችን ።

ሰው ፡ ራሱን ፡ በአሰበው ፡ ሊያራምድ፣ ባለመቻሉ፣ በጅምር፣ቀረ፣ እንጂ ፡ በትምህርት ፡ ዓለም ፡ በነበርንበት ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዝኛና ፡ ፈረንሳዊኛ ፡ ተከታትለን ፡ ነበር ። ኑሮዋችን ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ በግብርና ፡ ሆኖ ፡ ልናስፋፋው፣ አልቻልንም። መሠረት፣ ስላለን፣ ለአንድ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ብንቀጥል ፡ ራሳችንን ፡ እንችላለንና ፡ በማስተማር ፡ ዘዴ ፡ የተለየ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው ፡ ቀጥራችሁ ፡ ላኩልን ፡ አለቻቸው ፡ ፀሐይ ።

ንግግራችንን ፡ በዚሀ ፡ ላይ ፡ አቁመን ፡ ስለቤታችን ፡ አጠባበቅ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ስናዘጋጅ ፡ ዕምላዕሉ ፡ አስተማሪውን፣ አመጣልን፣ የሚኖርበትን ፡ ቤት ፡ አዘጋጅተን ፡ ስለነበር ፡ አስተማሪው ፡ ማረፊያውን ፡ ተረከበና ፡ የትምህርት ፡ አሰጣጡን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡አዘጋጅቶ፣ የእንግሊዝኛ ፡ ቋንቋ ፡ አስጀመረን ።

ሰው ፡ ቆርጦ ፡ ከተነሣ ፡ አሰበው ፡ ግብ ፡ ይደርሳል ። በኔና ፡ በፀሐይ ፡ የትምህርት ፡ አቀባበል ፡ አስተማሪያችን ፡ ተደሰተ ። እነቡርከት ፡ ሊጠይቁን ፡ መጡ ። በራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፡ እማማ፣ ትምህርቱን ፡ ወደድሽው ፡ ብላ ፡ ቡርከት ፡ፀሐይን ፡ ጠየቀቻት ። ትምህርት ፡ እንኳን ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ለእንስሳትም ፡ ይጠቅማል ፤ የሥጋ ፡ ፍላጐት ፡ ባልተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ። ዕውቀትን ፡ ለመመራመር ፡ ዕድሜ ፡ መጋረጃ ፡ ባይሆንም ፡ የመማሪያው ፡ ጊዜ ፡ ካለፈ ፡ በቀላል ፡ አይገባም ።



ስለትምህርት ፡ ይዞታችን ፡ አስተማሪያችን፣ ይንገርሽ ፤ አሳባችንን፣ የተነሣሣ፣ስለሆነ፣ በምንሄድበት፣ ሀገር፣ የምንፈልገውን፣ ለማወቅ፣ በልሳናችን ፡ መናገር ፡ አለብን ። ለዚህ ፡ የሚያበቃ ፡ ችሎታ ፡ እንዲኖረን ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ እናጠናለን ፤ አለቻት ፡ ፀሐይ ።

አስተማሪያችን ፡ ከነፈ ፡ ርግብ ፤ ሳቅ ፡ ሳቅ ፡ እያለ ፡ ሰው ፡ የደከመበትን ፡ የሚቀበለው ፡ ሲያገኝ ፡ ደስ ፡ እንደሚለው፣የታወቀ ፡ ነው ። የሰው ፡ ድካምና ፡ የሥራ ፡ ልክ ፡ መመዘን ፡ አለበት ። ምርትና፣ ግርዱ፣ ተበጥሮ ፡ ያልጠራ ፡ ፍሬ ፡ ፍሬነቱ ፡ እንደማይታወቅ ፡ ሌላውም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ።

እነወይዘሮ ፡ ፀሐይን ፡ ለማስተማር ፡ ስመጣ ፤ በትምህርት ፡ አቀባበል ፡ ይህ ፡ ይገጥመኛል ፡ ብዬ ፡ አላሰብኩም ፡ ነበር ። በነርሱ፣ዕድሜ፣ ያሉትን ፡ ማስተማር ፡ ጀምሬ ፡ በትምህርት ፡ አቀባበል ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ ዐይቻለሁ ። ሰልችተውም ፡ ያቋርጣሉ ።

እነወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ ለተነሱበት ፡ ዓላማ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ አላቸው ። መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ካለ ፡ አሸንፎ ፡ የሚቀር ፡ ባለመኖሩ ፡ አሸናፊ ፡ ሆኑ ። ትምህርት ፡ ከጀመሩ ፡ በስድስት ፡ወር ፡ ሆኗል ። የዓመቱን ፡ ትምህርት ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ አጠናቀዋል ።

በትጋታቸውና ፡ በትምህርት ፡ አቀባበላቸው ፡ በጣም ፡ አድንቄያቸዋለሁ ። ከዚህም ፡ ጋር ፡ የብዙዎችን ፡ ባልና ፡ ሚስቶች ፡ ኑሮ ፡ ዐይቻለሁ ። የነወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ የተቀደሰ ፡ ሆኖ ፡ ስላየሁት ፡ መንፈሳዊ ፡ ቅናት ፡ አሳድሮብኛል ።

አቶ ፡ መክብብ ፡ የሚደሰትበትን ፡ ወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ አጥብቃ ፡ ስትሻ ፤ ወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ የምትደሰትበትንም ፡ አቶ ፡ መክብብ ፡ ያስባል ። ሰው ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ የሚደሰትበት ፡ አያጣም ። በተለይ፣በቤት፣ ውስጥ ፡ የሚገኝና ፡ ደክመው ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ አግኝቶ ፡ ሲታይ ፡ ደስታው ፡ ከሁሉም ፡ የበለጠ ፡ ይሆናል ፡ አለ ።

ፀሐይ ፡ ቀጠል ፡ አድርጋ ፡ ከኛ ፡ ይልቅ ፡ የምትመሰገን ፡ አንተ ፡ ነህ ። ትምህርቱን ፡ እንደሚገባን ፡ አድርገህ ፡ በአጭር ፡ መንገድ ፡ ስለአቀረብክልን ፡ ለመከታተል ፡ አልተቸገርንም ፡ አለችው ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ከራት ፡ መልስ ፡ ስለጉዞዋችን ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡
ስንለዋወጥ ፡ ማንኛውን ፡ ሀገር ፡ በቅድሚያ ፡ ማየት ፡ እንዳለብን ፡ መም
ሀራችን ፡ ሐሳብ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተጠየቀ ።

ይህ ፡ ያልጠበቅሁት ፡ ጥያቄ ፡ ነው ፡ አለና ፡ የጐብኝታችሁ ፡ መጀ
መሪያ ፡ ከአፍሪካ ፡ ሆኖ ፡ ነፃ ፡ የወጡትንና ፡ ነፃ ፡ ያልወጡትን ፡ ሀገሮች፡
ጐብኙ ። ከእስያና ፡ ከኤሮፓም ፡ እንደዚሁ ፡ ካያችሁ ፡ ወደ፡ አሜ
ሪካን ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ብትሄድ ፡ ሌላ ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ ተብሎ፡ ቅጽል ፡
ስም ፡ በተሰጠው ፡ በአሜሪካ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም፡ ስትደርሱ ፡ የምታዩት ፡
ሁሉ፡ አዲስ ፡ እየሆነባችሁ ፡ የምትሰጡት ፡ አድናቆት ፡ የተቀነሰ ፡
ይሆናል ፡ አለን ።

ቡርክት፡ ሐሳቡዋን ፡ ከክንፈ ፡ ርግብ ፡ ጋር ፡ አስተባብራ ፡ የምታ
ዩት ፡ ተለይቶ ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። በየደረሳችሁበት ፡ ሀገር ፡ አስተ
ናጋጅዎች ፡ አሉ፤ የሚያሳዩዋችሁ ፡ እንደየዝንባሌያችሁ፡ ነው፤ የከተማ፡
ውበትና ፡ የመሳሰለውን ፡ ብቻ ፡ አይቶ ፡ የሚረካ ፡ አለ ።

ታሪካዊ ፡ ሥፍራዎችን ፡ በማየት ፡ የጥንቱንና ፡ የዛሬውን ፡ የሚ
ያመዛዝን ፡ አለ ። በዛሬው ፡ ዓለም ፡ በጥበብ ፡ የሚደነቁ ፡ ከዛሬ ፡ መቶ ፡
ዓመት ፡ በፊት ፡ እምን ፡ ላይ ፡ እንደነበሩ ፡ መረዳት ፡ የሚፈልግ ፡ አለ ።

በሰው ፡ ጥበባዊ ፡ አዕምሮ ፡ ተፈልስፈው ፡በአንድ፡ በኩል፡ ለሰው፡
ልጅ ፡ ለሕይወታዊ ፡ ኑሮው ፡ የሚጠቅሙ ፤ በሌላ ፡ በኩል ፡ ለሰው ፡
ልጅ ፡ ማጥፊያ ፡ የሆኑትን ፡ ማየት ፡ የሚፈልግ ፡ አለ ። እነዚህን ፡ ለማ
የት ፡ ደንታ ፡ የሌለው ፡ በጨዋታና ፡ ይህን ፡ በመሳሰለ ፡ በሌሊቱ ፡ የዕ
ረፍት ፡ ጊዜ ፤ ናይት ፡ ክለብ ፤ እየተባለ ፡ በሚጠራው ፡ የሚሠራውን፡
ድርጊት ፡ ለማየት ፡ የሚፈልግ ፡ አለ ።

እንግዲህ ፡ ከነዚህ ፡ ማናቸውንም ፡ አቅጣጫ ፡ እንደምትመርጡ ፡
አባባና ፡ እማማ ፡ አስቡበት ፤ እንደእኔ ፡ ከሆነ ፡ ሁሉንም ፡ ዕወቁት ፡
ሁሉንም ፡ እይውት ፡ መጥፎንና ፡ ደጉን ፡ ትለዩታላችሁ ።

የሁለቱንም ፡ ሐሳብ ፡ በትዕግሥት ፡ አዳመጥን ። የጉዳዩ ፡ ባለቤ
ቶች ፡ እንደመሆናችን ፡ መርጠ ፡ መወሰን ፡ የኛ ፡ ፋንታ ፡ ሆነ ። ከፀሐይ ፡
ጋር ፡ ዓይን ፡ ለዓይን ፡ ተያየን ። ከመናገሬ ፡ በፊት ፡ ፀሐይ ፡ እንድትና
ገር ፡ ዓይኔን ፡ ከዓይንዋ ፡ ሳላነሣ ፡ ጠበቅሁ ። ርስዋም ፡ በበኩልዋ ፡ ዓይ
ንዋን ፡ ከዓይኔ ፡ ላይ ፡ ጣል ፡ አድርጋ ፡ እናገር ፡ እንደሆነ ፡ ጠበቀችኝ ።



ልናገር፡ ስል፡ አንድ፡ ጥያቄ፡ አለኝ ፡ አለች፡ ፀሐይ ። የምናያቸውን፡
መርጠን ፡ መወሰን ፡ እንዳለብን ፡ ቡርክት ፡ ዘርዝራዋለች ። ከተነገሩት፡
ስንቱ ፡ በሀገራችን ፡ አሉ ? ወይስ ፡ የሉም ፤ ይህን ፡ በቅድሚያ ፡
ማወቅ ፡ አይኖርም ?

ብዙዎች ፡ አሉ ፡ አልኳት ፡ ታዲያ ፡ በሀገራችን ፡ ምድር ፡ የሚ
ገኙትን ፡ ሳናውቃቸው ፡ የሌላውን ፡ ሀገር ፡ ማወቃችን ፡ አያሳፍረንም ፡
አለች ። በሁላችንም ፡ አሳብ ፡ የሌለውንና ፡ ቅድሚያ ፡ የሚሰጠውን ፡
እማማ ፡ አስታወሰች ። የሀገርን ፡ ጉዳይ ፡ ሳያውቁ ፡ መሄድ ፡ የሚያሳፍ
ርና ፡ የሚያስገምት ፡ ነው ።

ስለሌላው ፡ ሀገር ፡ ማወቅ ፡ እንደምንፈልግ ፤ ሌላውም ፡ ስለሀገራ
ችን ፡ ማወቅ ፡ ይፈልጋል ። ይልቁንም ፡ በታሪክ ፡ ያወቁ፡ በበለጠ ፡ ለመ
ረዳት ፡ ይጠይቃሉ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አላቅም ፡ ማለት ፡ ወይም ፡ ያልሆነውን ፡ መና
ገር ፡ ሀገራችንን ፡ እንደማናውቅ ፡ አድርጎ ፡ ያስገምታል ። በብዙ ፡ ሀገ
ሮች ፡ ገበሬው ፡ ነጋዴው ፡ ተራው ፡ የቀን ፡ ሠራተኛ ፡ ሳይቀር ፡ ስለሀ
ገሩ ፡ የተጠየቀ ፡ እንደሆነ ፤ በፖለቲኩ ፤ በኢኮኖሚው ፡ በአስተዳደሩ ፡
በጠቅላላው ፡ ሀገሩን ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ ተወክሎ ፡ መልስ ፡ ይሰ
ጣል ። ሀገር ፡ የሁላችንም ፡ ናት ። ደስታዋ ፡ ደስታችን ፡ ስለሆነ ፤ ልባዊ ፡
አስተሳሰብ ፡ የሚኖረን ፡ ማናቸውንም ፡ የሀገራችንን ፡ ጉዳይ፡ እኩል ፡
ተካፍለን ፡ ያወቅን ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።

የሌላውን ፡ ሀገር ፡ ከራሳችን ፡ ጋር ፡ ለማመዛዘን ፤ የራሳችንን ፡ ለማ
ወቅ ፡ ቅድሚያ ፡ ይኑራችሁ ፡ ብላ ፡ ተናገረች ።

በመሠረቱ ፡ ሐሳቡ ፡ ተስማማንና ፡ በሀገር ፡ ውስጥ፡ በምናደርገው፡
ጉዞ ፡ ክንፈ፡ ርግብ ፡ አብሮን ፡ ተጓዥ ፡ እንዲሆን ፡ ወሰን ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚገኙትን ፡ የታሪክ ፡
ሥፍራዎች ፡ ለማየት፡ በወሎ፡ ጠቅላይ፡ ግዛት ፤ በላስታ፡ አውራጃ ፡ የሚ
ገኘውን ፡ ስመ፡ጥሩውን ፡ የቅዱስ ፡ ላሊበላን ፡ ሕንፃ ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡
ለማየት ፡ ተጓዝን ።

እንደአጋጣሚ ፡ ወሩ ፡ ታኅሣሥ ፡ ስለነበር ፤ ጌታችን ፡ መድኃኒ
ታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በልደት ፡ የተገኘበት ፡ ዕለት ፡ በትልቅ ፡
ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ይከበር ፡ ኖሮ ፤ ከበዓሉ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ስን

ደርስ ፣ የበዓሉ ፣ አከባበር ፣ ዝግጅት ፣ በሰፊው ፣ ይሰናዳ፣ ነበር ። በዓሉን፣ ለማክበር ፣ ዕድል ፣ አገኘን ። ከበዓሉ ፣ በኋላ ፣ አሥሩን ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ እየተዘዋወርን ፣ ዐየን ። ሕንፃው ፣ በመሬት ፣ ላይ ፣ ታንፆ ፣ የተቀመጠ ፣ ሳይሆን ፣ ከመሬት ፣ ውስጥ ፣ ያለው ፣ ተፈልፍሎ ፣ የወጣ ፣ ስለሆነ ፤ ወሬውን ፣ በአድናቆት ፣ ከመናገር ፣ በቀር ፣ ስለሥራው ፣ ዝርዝር ፣ ለመናገር ፣ ችሎታችን ፣ የማይፈቅድ ፣ ሆኖ ፣ አገኘነው ።

የስምንት ፣ መቶ ፣ ዘመን ፣ ዕድሜ ፣ ያላቸው ፣ እነዚህ ፣ ሕንፃዎች ፣ በዚያን ፣ ጊዜ ፣ በኢትዮጵያውያን ፣ የታነፁ ፣ ይሆኑ ? የሚል ፣ ጥርጣሬ፣ አድሮብን ፣ ታሪኩን ፣ ያውቃል ፣ የተባለውን ፣ አስረዷ፣ ጠየቅን።

በኢትዮጵያውያን ፣ ዐዋቂዎች ፣ የታነፁ ፣ መሆናቸውን ፣ ሲያረጋግጥልን ፤ እነዚህን ፣ ተወዳዳሪ ፣ የሌላቸውን ፣ አስደናቂ ፣ ሕንፃዎች ፣ የጐበኘ ፣ ሁሉ ፣ ተመሳሳይ ፣ ጥያቄ ፣ ይጠይቃል ።

የኢትዮጵያን፣ ጥንታዊ፣ ሥልጣኔ፣ መቀበል፣ የማይወዱ ፤ የውጪ፣ ሰው፣ እጅ ፣ እንዳለበት ፣ ከመናገራቸው ፣ በቀር ፣ ሕንፃዎቹን ፣ ቅዱስ፣ ላሊበላ ፣ ያሳነፃቸው ፣ ናቸው ፣ አለን ።

ኢትዮጵያውያን ፣ ሆነን ፣ በሀገራችን ፣ የሚገኙትን ፣ እነዚህን ፣ ታሪካዊ ፣ ሕንፃዎች ፣ እስካሁን ፣ ሳናውቃቸው ፣ መኖራችን ፣ የሚያሳፍር ፣ መሆኑን ፣ አመንበት ። አሁንም ፣ ለማየት ፣ ዕድል ፣ ያገኘነው ፣ ከሀገራችን ፣ ውጪ ፣ ያሉትን ፤ ለማየት ፣ ብንነሣ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ይህ ፣ ምክንያት ፣ ባይኖር ፣ ምንም ፣ ጊዜም ፣ አናያቸው ፣ ነበር ።

መሶባችንን ፣ ከበን ፣ ራታችንን ፣ስንመገብ ፤ ቀኑን ፣ ሙሉ ፣ ስለ ፣ አየናቸው ፣ ታሪካዊ ፣ ሕንፃዎችና ፣ ዕቃዎች ፣ መነጋገር ፣ ጀመርን ።

ውድይቱን ፣ ፀሐይ ፣ በቅድሚያ፣ ስትከፍት ፤ መላ ፣ አካላችን ፣ የሚመራው፣ በዓይን ፣ ብርሃናችን፣ ነው ። የእግዚአብሔር ፣ ሥነ፣ ፍጥረትና፣ ጥበብ ፣ የተገለጸላቸው ፣ አገናኝተው ፣ በዓይን ፣ እንዲታዩ ፣ በእጅ ፣ እንዲዳሰሱ ፣ ያደረግዋቸውን ፣ በዓይናችን ፣ ብርሃን ፣ ልናያቸው ፣ ሲገባን ፤ በተወሰነ ፣ ሥፍራ ፣ ተቀምጠን ፣ ዘወትር ፣ አንድ ፣ ዓይነት ፣ ነገር ፣ ብቻ ፣ በማየታችን ፣ ዕውቀታችንም ፣ ሆነ ፣ አስተሳሰባችን ፣ በዚሁ ፣ መጠን ፣ የተወሰነ ፣ ሆኗል ።

በሰው ፣ ኃይልና ፣ የአዕምሮ ፣ ዕውቀት ፣ ተሠርተው ፣ ዛሬ ፣ ያየናቸውን ፣ ሕንፃ ፣ አብያተ ፣ ክርስቲያናት ፣ ስንመለከት፤ የሰው ፣ ብርቱነትና ፣ ተሰፋው ፣ ምን ፣ ያህል ፣ መሆኑን ፣ አልተማርንም? እነዚህንና ፣



እነዚህን ፣ የመሳሰሉትን ፣ ሳናይ ፤ የአዕምሮና ፣ የዓይን ፣ ብርሃናችን ፣ ተጋርዶ ፤ በጥበብ ፣ ወደኋላ ፣ ቀረን ።

እነዚህን ፣ የመሳሰሉ ፣ ብዙዎችን ፣ እናያለን ። የምናያቸው፣ ሁሉ፣ የሚያስደንቁ ፣ ስለሆኑ ፣ በኢትዮጵያውያን ፣ የተሠሩ ፣ በመሆናቸው ፣ የመንፈስ ፣ ኩራት ፣ ይሰማናል ። ራሳችን ፣ እስካሁን ፣ ድረስ ፣ ባለማየታችን ፣ ራሳችንን ፣ በራሳችን ፣ እንደ ፣ ታዘብነው ፤ እነዚህን ፣ ለመሳሰሉ ፣ የታሪክ ፣ ቅርሶች ፣ ከፍተኛ ፣ ግምትና ፣ ዋጋ ፣ የሚሰጡ ፣ በታሪክ ፣ እየተመሩ ፣ ከልዩ ፣ ልዩ ፣ ሀገር ፣ በብዛት ፣ እየመጡ ፣ ዓይተው ፤ የሥራቸውን ፣ አስደናቂነት ፣ ለዓለም ፣ ያሰራጫሉ ።

የታሪኩ ፣ ባለቤት ፣ የሆን ፣ የማየት ፣ ስሜታችን፣ የደከመው ፣ ካለማወቅ ፣ የተነሣ ፣ ስለሆነ ፤ ተምረን ፣ ማስተማር፣ አለብን ። የታሪክ ፣ ቅርሶች ፣ የሀገራችንን ፣ ታሪካዊ ፣ አቀዋም ፣ የሚመሰክሩ ፤ ከዓለም ፣ ሕዝብ ፣ ጋር፣ የሚያስተዋውቁና፣ የሚያቀራርቡ፣ የሀብትም ፣ ምንጮች፣ ናቸው ፣ አለች ።

የተሠራ ፣ ሥራ ፣ የሚወድቅበትና፣ የሚነሣበት ፣ ጊዜ ፣ አለ ።በዘመን ፣ የሚነሡ፣ በዘመናቸው ፣ ለመሥራት፣ የጋለ ፣ ፍላጎት ፣ ስላላቸው፣ ከነርሱ ፣ በፊት ፣ ስለነበረው ፣ ያላቸው፣ አስተሳሰብ ፣ የቀዘቀዘ ፣ ይሆናል ። ከነርሱም ፣ በኋላ ፣ የሚነሣው ፣ አስተሳሰቡ ፣ እንደነርሱ ፣ ስለሆነ ፣ የዘመኑን ፣ ሥራ ፣ አጥብቆ ፣ ሲከታተል ፣ ያለፉትን ፣ ቸል ፣ ማለቱ ፣ አይቀርም ።

የዓለም ፣ ሰው ፣ አሮጌውን ፣ በአዲስ ፣ ለውጦ ፣ እየተራቀቀ ፣ ይጓዝና ፤ ያሁን ፣ ዘመን ፣ ሰዎች ፣ ይህን ፣ ሠራን ። ቀደም ፣ ብለው ፣ የነበሩት ፣ የሠሩትን ፣ ዕንወቅ ፣ ብሎ ፣ በታሪክ ፣ መሪነት ፣ ለማወቅ ፣ ችግሉን ፣ ይቀጥላል ። ከዚህም ፣ የተነሣ፣ በምድር ፣ ማኅፀን ፣ የተቀበሩት ፣ በጠቢባን ፣ እየተቆፈሩ ፣ ይወጣሉ። ከመሬት ፣ በላይ ፣ ያሉትም፣ ሕጋዊ ፣ አጠባበቅ ፣ ይደረግላቸዋል ። ሰዎች ፣ በዘመናቸው ፣ የሠርዋቸውን ፣ ሥራዎች ፣ በዘመናት ፣ ብዛት ፣ የማይጠፉ ፣ ለዘለዓለም ፣ የሚኖሩ ፣ ናቸው ።

እነዚህን ፣ ታሪካዊ ፣ ሕንፃዎች ፣ ያስገኙ ፣ ዛሬ ፣ ወዴት ፣ ናቸው? በአካለ ፣ ሥጋ ፣ አንያቸው ፣ እንጂ ፣ ሥራዎቻቸው ፣ ምስክር ፣ ሆነው፣ በመንፈስ ፣ እናያቸዋለን ።

እነዚህን ፡ ታሪካዊ ፡ ሕንፃዎች ፡ ትተውልን ፡ ባያልፉ ፡ ማንነታቸውን ፡ በምን ፡ እናውቅ ፡ ነበር ። ስለዚህ ፡ በሚያልፍ ፡ ሕይወት ፡ የማያልፍ ፡ ሥራ ፡ ሥራበት ፡ ያለው ፡ ሊቁ ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ በበኩሌ ፡ ተናገርኩ ።

በዚሁ ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ሆነ ። በሁላችንም ፡ ዓይን ፡ ላይ ፡ እንቅልፍ ፡ አንዣቧልና ፡ ዐረፍ ፡ እንበል ፡ ብለን ፡ በየመኝታ ፡ ክፍላችን፡ ገብተን ፡ በየአልጋችን ፡ ላይ ፡ ጋደም ፡ እንዳልን፡ እንቅልፍ ፡ አሸለበን ። ከሌሊቱ፡ በስምንት፡ ሰዓት፡ ነቃሁ ። በአልጋዬ፡ ላይ ፡ እንደሆንኩ ፡ ብገላበጥም ፡ እንቅልፍ ፡ አሻፈረኝ፡ ብሎ ፡ ከዓይኔ፡ ጠፋ ። ዓይኔን ፡ ወደ ፡ መስኮቱ ፡ ጣል ፡ ባደርገው ፡ በመስኮቱ ፡ የሚታየው ፡ የጨረቃዋ ፡ ብርሃን ፡ ጨለማውን ፡ አስወግዶት ፡ ውጭው ፡ ይታያል ።

የሠፈርንበት ፡ ቤት ፡ የሚገኘው፡ ከከፍተኛ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ፡ ከበረንዳ ፡ ላይ ፡ ቁጭ ፡ ብዬ ፡ ስመለከት ፡ የሚነፍሰው ፡ ነፋስ ፡ ሕይወት ፡ ያድሳል ። የተጣራውን ፡ አየር ፡ እየተመገብኩ፡ ዓይኔን ፡ በማንከራተት ፡ ግራ ፡ ቀኙን ፡ ስመለከት ፤ አካባቢው ፡ ተራራማና ፡ ጕራንጕር ፡ ሲሆን ፡ ይህን ፡ ታሪካዊ ፡ ሕንፃ ፡ ያስገኙ፡ በመሠረቱ፡ እንደምን፡ ከዚህ ፡ ተራራና ፡ ጕራንጕር ፡ ድረስ ፡ መጡ ።

የሕንፃውም ፡ ሥራ ፡ በሰው ፡ ኃይል፡ የተሠራ፡ ነው፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ ያጠራጥራል ። የሰው ፡ ጉልበት ፡ የተወሰነ ፡ ነው። ሰው ፡ በአዕምሮው ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ያስባል። በሰውነቱ፡ ግን ፡ ከተወሰነ ፡ ክብደት፡ በላይ ፡ መሸከም ፡ አይችልም ፡ እያልኩ ፡ ራሴን ፡ በራሴ ፡ ሳነጋግር ፡ የሰው ፡ ድምፅ ፡ ሰማሁ ።

ሐሳቤን ፡ ሁሉ ፡ ፀጥ ፡ አድርጌ ፡ ሳዳምጥ ፡ ድምፁ ፡ እየቀረበኝ ፡ የበለጠ ፡ ስለተሰማኝ ፡ ከተቀመጥኩበት ፡ ፈቀቅ፡ ብዬ ፡ በዓይኔ ፡ማየት፡ ወደድሁ ። ሰው ፡ ነኝና ፡ በሰው ፡ ባሕርይ ፡ ቸኰልኩ ፡ እንጂ፡ የሰማሁት ፡ ድምፅ ፡ ሳያቋርጥ ፡ እንዳነበነበ ፡ በጣም ፡ ቀረበኝ ።

አንገቴን ፡ መዘዝ ፡ አድርጌ ፡ ባይ ፡ ከፍ፡ ያለ ፡ ጥምጥም፡ የጠመጠሙ፡ አረጋዊ ፡ ኖረው ፤ ሳይርቁኝ ፡ አባቴ ፡ አልኳቸው ። ደንገጥ ፡ ብለው ፡ በስመ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ፡ አሉና ፡ ማነህ ፡ ወዳጄ፡ አሉኝ ።



እንግዳ ፡ ነኝ ፡ እያውቁኝም ፡ ወዴት ፡ ይሄዳሉ ፡ ብላቸው ፡ እንደ እኔ ፡ ያለ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ወዴት፡ የሚሄድ ፡ ይመስልኻል ፤ ሰዓታት፡ ለመቆም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እሄዳለሁ ፡ ብለው ፡ መልስ ፡ ሰጡኝ ። ቀጠል ፡ አደረጉና ፡ ወዳጄ ፡ አንተስ ፡ በአሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ከዚህ፡ ምን ፡ ታደርጋለህ ፡ ብለው ፡ ጠየቁኝ ።

እንግዳነቴን ፡ በማስረዳት ፡ ሀገሩ ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ ስላለው ፡ በጨረቃዋ ፡ ብርሃን ፡ ቀዝቃዛውን ፡ ነፋስ ፡ እየተመገብኩ ፡ ተራራውንና ፡ ሸንተረሩን ፡ እመለከታለሁ ። ተራራማ ና ፡ ጕራንጕር ፡ ሲሆን ፡ ታሪካዊውን ፡ ሕንፃ ፡ ያስገኘው ፡ ንጉሥ ፡ ላሊበላ ፤ በምን ፡ ሁኔታ ፡ ተገፋፍቶ ፡ ከዚህ ፡ እንደመጣ ፡ ገርሞኛል ።

ታሪካዊ ፡ ሕንፃዎቹም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደምን ፡ ባለ ፡ መሣሪያና ፡ የጥበብ ፡ ሰዎች ፡ እንደተሠሩ ፡ ለማወቅ ፡ እመራመራለሁ ። ሕንፃውን ፡ የሠሩት ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፤ ኢትዮጵያውያን ፡ አይደሉም ፤ የሚል ፡ ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ ወሬ ፡ ሰምቻለሁ ፡ በበኩልዎ ፡ ስለዚህ ፡ የሚያውቁትን ፡ ቢነግሩኝ ፡ አመሰግናለሁ ፡ አልኳቸው ።

ምን ፡ አለ ፡ መቆየት ፡ ብዙ ፡ ያሰማል ፤ እንደዚህ ፡ መባሉን ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ሰምቻለሁ ፤ ወሬው ፡ በመስፋፋቱ ፡ አንተም ፡ ሰምተሃል ። ብታምንበትም ፡ ባታምንበትም ፡ ልንገርህ ፤ ክርስቲያን ፡ ትመስለኛለህ ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ ሃይማኖት ፡ አለህ ፡ ብዬ ፡ አምናለሁ ። ብለው ፡ ንግግራቸውን ፡ ሊቀጥሉ ፡ ሲሉ ፡ አባቴ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ በዚህ ፡ አይጠራጠሩ ፡ አልኳቸው ።

ጐሽ ፡ ልጄ ፡ አሉና ፡ የሃይማኖት ፡ ሰው ፡ ከሆንክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሳነው ፡ ነገር ፡ አለ ? «ለእግዚአብሔር፡ የሚሳነውስ ፡ ነገር፡ የለም ፡ » ብዬ ፡ መለስኩላቸው ።

ልጄ ፤ ይህን ፡ ካመንክማ ፡ ሠሪና ፡ አሠሪው ፡ እግዚአብሔር፡ ነው። ሰው ፡ ግን ፡ መሣርያ ፡ ነው ። የነዚህ ፡ ሕንፃዎች ፡ አሠራር ፡ ንጉሥ ፡ ላሊበላ ፡ በተአምራዊ ፡ ሥራ ፡ በመላእክት ፡ እየተረዳ ፡ ማከናወኑን ፡ የተናገሩለትንና ፡ የጻፉለትን ፡ ጥንታውያን ፡ ሰዎች ፡ እንዳስቸገረው፡ ዓይነት ፡ እስከዛሬም ፡ ድረስ ፡ ለሕንፃ ፡ ሊቃውንትና ፡ ዐዋቂዎች ፡ ትርጓሜ ፡ የሌለው ፡ ዕንቈቅልሽ ፡ ሆኖባቸዋል ።

ባየኻቸው ፡ ታሪካዊ ፡ ሕንፃዎች ፡ የውጭ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እንዳለ ፡ ሲነገር ፣ ያላየኻቸው ፡ ብዙዎች ፡ በዚህ ፡ አካባቢና ፡ ከዚህም፡ ራቅ ፡ ባለ ፡ ሥፍራ ፡ ይገኛሉ ። እንግዲህ ፡ እነዚህና ፡ ሌሎችም ፡ በውጭ ፡ ሰው ፡ የተሠሩ ፡ ናቸው ፡ ማለት ፡ ስሕተት ፡ እንጂ፡ ትክክለኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ አለመሆኑን ፡ ብታምን ፡ እወዳለሁ ።

ስለሀገሩና ፡ አካባቢው ፡ ሁኔታ ፡ ልጠይቃቸው ፡ ስወድ ፡ ልጇ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምናቀርበውን ፡ ምስጋና፡ የምንጀምርበት ፡ ሰዓት፡ ሊተላለፍብኝ ፡ ነውና ፣ ሌላ ፡ ጥያቄ ፡ ልቀበልህ፡ አልችልምና፡ ልሂድ፡ አሉኝ ።

እባክዎ ፡ አባቴ ፡ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ ብነጋገር፡ እወዳለሁና፣ አንዳንድ፡ ነገር ፡ እንድጠይቅዎ ፡ ፈቃድዎ ፡ ይሁን ፡ አልኳቸው ።

አዬ፡ ልጄ፡«የንግግር፡ ብዛት፡ በአህያ፡ አይጫንም፡ » ዛሬ፡ በሥራ፡ ከሚገለጸው ፡ በንግግር ፡ ብቻ ፡ የሚተረከው፡ እየበዛ፡ ንግግርና ፡ ሥራ፡ ሳይገናኙ፡ይኖራሉ ። በኔ ፡ ዕድሜ፡ካሉ ፡ ጠይቆ ፡ መማር ፡ በተጠላበት ፡ ጊዜ፡እንዴት ፡ አንተ ፡ እኔን ፡ በማነጋገር ፡ በዕድሜህ፡ የማታውቀውን፡ ለማወቅ ፡ ፈለገህ ? ልጄ ፡ በዕድሜዬ ፡ ያየሁትንና ፡ የተማርሁትን ፡ ብነግርህ ፡ በወደድሁ ። ይሁንና ፡ የትም ፡ የት ፡ ብትሄድ ፡ ንግግር ፡ ብቻ ፡ ትሰማለህ ፣ ንግግር ፡ ካልተሠራበት ፡ በኖ ፡ ይቀራል ።

ዘመኑ ፡ የረቀቀ ፡ ዘመን ፡ ነው ። በዱሮ ፡ ዘመን ፣ ሰውን ፡ ሰው ፡ በንግግር ፡ ብቻ ፡ ያሳምን ፡ ነበር ። የዛሬ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በዓይኑ ፡ ካላየ ፡ በእጁ ፡ ካልዳሰሰ ፡ በንግግር ፡ ብቻ ፡ አያምንም። እኔም ፡ በወሬ ፡ የሰማሁትን ፡ ሳይሆን ፡ በዓይኔ ፡ ያየሁትን ፡ ብነግርህ ፡ እኔ ፡ የነገርኩህን ፡ በቃልም ፡ ሆነ ፡ በጽሕፈት ፡ ብታወራው ፡ ተቀባይ ፡ ላታገኝ፡ ምን አታከተህ ።

እንደዚህ ፡ ያለ ፡ የተጠራጣሪና ፡ የተመራማሪ ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ የገመተ ፡ የለም ፡ እንጂ ፣ በየዋህነት፡ ከመመራት ፡ መጠራጠር ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፣ የላሊበላ ፡ ታሪካዊ ፡ ሕንፃ ፡ ሥራ ፡ ዛሬ ፡ ለሚያየው ፡ ሁሉ ፡ እያጠራጠረ ፡ ራስ ፡ ምታት ፡ የሆነውን ፡ ራሱ ፡ ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ እንደሠራው ፡ በዘመኑ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ አብራርተው ፡ ይጽፉት ፡ ነበር ።



ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ እውነትን ፡ እንጂ ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ ያልሆነውን ፡ እንደሆነ ፡ አድርጎ ፡ አጋኖ ፡ ቢጽፈውም ፡ የሰውን ፡ የመመራመር ፡ አስተያየት ፡ ወደ ፡ ጥርጣሬ ፡ ከመምራት ፡ በቀር ፡ ተቀባይነት ፡ አያገኝም ። ታሪክ ፡ በአጻጻፍ ፡ ላይ ፡ ቁልምጫ ፡ የማይፈልግ ፡ ሥራንና፡ አሠራርን ፡ ብቻ ፡ የሚያስተዋውቅ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ መታሰቢያ ፡ ስለሆነ፡ ሐቀኛ ፡ ሰው ፡ ይፈልጋል ።

አሁን ፡ ያለንበት ፡ ሥፍራ ፡ ኍራንኍር ፡ ስለሆነ፣ ምኞት ፡ የለውም፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ታምራት ፡ የሚሠራባቸውና ፡ ታሪክ፡ የሚገለጽባቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚመረጡት ፡ በሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ ሳይሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ በመረጠው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ ያ፡ ሰው፡ የታዘዘውን፡ ሥራ፡ በዚያ ፡ ለመሥራት ፡ ምክንያት ፡ ይሆናል ። ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ በዚህ ፡ ሥፍራ፡ እነዚህን ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት ፡ ያነፀው ፡ በሰው ፡ የባሕርይ ፡ ኃይል ፡ ሳይሆን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ነው፡ ብለን ፡ እናምናለን ።

ከባሕር ፡ ማዶ ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ የሠሩት ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፣ እግዚአብሔር ፡ በሰው ፡ ላይ፡ አድሮ፡ ስለሚሠራው፡ ሥራ ፡ እምነት ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ። ልጄ ፡ ይብቃህ ፣ እኔም ፡ ወደ ፡ ተግባሬ ፡ ልሂድ ፣ አንተም ፡ ገብተህ ፡ የቀረውን ፡ ሌሊት ፡ በእንቅልፍ ፡ አሳልፍ ፡ አሉኝ ። ንግግራቸው ፡ ስለጣመኝ ፡ አባቴ ፡ ንግግርዎ፡ ሙት፡ ያስነሣል ፣ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሄዱት ፡ ዘወትር ፡ ነው ፡ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ አለ ?

አዬ ፡ ልጄ ፡ ይህን ፡ ስዘረዝር ፡ እዚሁ፡ ላነጋው፡ ነው፡ ሌላ ፡ ጥያቄ፡ አልቀበልም ፡ ይህን ፡ ግን ፡ አስረዳኻለሁ ። በየሳምንቱ ፡ ዕለተ ፡ ሰንበት ፡ በአጽዋማት ፡ ጊዜ ፡ ጾሙ ፡ ከተጀመረ ፡ እስኪፈጸምና ፡ በወራቶች ፡ መካከል ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ በዓላት ፡ በጠቅላላው ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ አምስት ፡ ቀናት ፡ የሚበልጡትን ፡ አገልግሎት ፡ እንሰጥባቸዋለን ። ይኸውም ፡ ማኅበራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ማለቴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በየግላችን ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ በቀናትና ፡ በሰዓታት ፡ ሳንወሰን ፡ በቤተ ፡ ግዚአብሔር ፡ እየተገኘን ፡ እንደየስሜታችን ፡ ከፈጣሪያችን ፡ ጋር ፡ እንነጋገራለን ።

አባቴ ፡ ከይቅርታ ፡ ጋር ፡ ላቋርጥዎ ፡ አልኩና ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዓይናችሁ ፡ እያያችሁ ፡ በቃላችሁ ፡ ታነጋግሩት ፡ አላችሁ?

ጉድ ፡ ነው ፡ እኮ ፡ አሉና ፡ ማሃይምን ፡ ነህ ፡ እንዳልል ፡ የተማርክ ፡ ትመስላለህ ፣ ጥራዝ ፡ ነጠቅ ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ከመጋለብ ፡ በቀር ፡ ጠለቅ ፡ ብሎ ፡ ምሥጢር ፡ አይመረምርም ! የእግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ በሚቀደስበት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የተቆረሰ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ለማስታወስ፡ በሚሠዋበት ፡ ተገኝቶ ፡ ልቦናን ፡ ለርሱ ፡ ሰጥቶ ፡ የሚደረገው ፡ ልባዊ ፡ ጸሎት ፡ ሁሉ ፣ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ የሚያነጋግር ፡ ነው ። እኛ ፡ እናየውም ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ ያየናል ። ልቦናችንን ፡ ከሰጠነው ፡ እንደሚያየንና ፡ እንደሚሰማን ፡ እናምናለን ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚቀርብ ፡ የሕሊና ፡ ጸሎት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋር ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የሚያነጋግር ፡ መሆኑን ፡ እመን ።

ዕድሜዬ ፡ ዘጠና ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ነው ፣ እስከ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ያለውን ፡ ለማጣራት ፡ እንኳን ፡ ባልችልም ፣ ከአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ዕድሜዬ ፡ የማውቀውን ፡ ልነግርህ ፡ ከወደድህ ፣ ጠዋት ፡ ጠብቀኝና ፡ እነግርሃለሁ ። አሁን ፡ ግን ፡ ወደተግባሬ ፡ ልሂድ ፡ ብለውኝ ፡ ሄዱ ።

ፀሐይ ፡ ድንገት ፡ ከእንቅልፍ ፡ ነቅታ ፡ ስታጣኝ ፡ ትደነግጥ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ መኝታ ፡ ቤት ፡ ስገባ ፡ እንደፈራሁት ፡ ፀሐይ ፡ በድንጋጤ ፡ ስትፈልገኝ ፡ ደረስኩ ።በውጭ ፡ የቆየሁበትን ፡ ምክንያት ፡ አጫወትኳት ።

ፀሐይ ፡ ከቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ መነጋገር ፡ ስለምትወድ ፡ ነገ ፡ ውለንም ፡ ቢሆን ፡ አረጋዊውን ፡ ብናነጋግራቸው ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ አለች ። ቀጥሎም ፡ አባቶች፡ በረዥም ፡ የዕድሜ ፡ ዘመን፡ ያዩትንና፡ ያወቁትን ፡ መስማት ፡ ቀላል ፡ አይደለም። ነገ ፡ ለዛሬ ፡ አያገለግልም ፡ ነገ ፡ የራሱን ፡ ድርሻ ፡ ሠርቶ ፡ ወር ፡ ተራውን ፡ ለዛሬ ፡ ሰጥቶ ፡ አልፍዋል ፡ እየተባለ ፡ ሰው ፡ ስለነገው ፡ ግዴታ ፡ የሌለው ፡ እየሆነ ፡ የነገውን ፡ በዛሬ ፡ እየረሳ ፡ የወደፊቱን ፡ ብቻ ፡ ይከተላል ።

ይሁንና፡ ነገ ፡ ለዛሬ፡ ትቶ ፡ የሚሄደው ፡ ለዛሬ ፡ ሳይሆን ፡ ለወደፊቱ ፡ እየተከታተሉ ፡ ለሚመጡት ፡ ታሪኮች ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል ። ጠቢቡ ፡ ሰሎሞን ፡ «በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ፡» ያለውን ፡ እናስብ ፡ ቀናት ፣ ወራት ፣ ዓመታት ፡ ቢለዋወጡም ፡ ለኛ ፡ የዕድሜ ፡ መለኪያ ፡ ይሆናሉ ፡ እንጂ ፡ ቀናት ፣ ወራትና ፡ ዓመታት ፡ እየተለዋወጡ ፡ ይመጣሉ ።



አትክልትና ፡ አዝርዕት ፣ ዕፀዋት ፡ የታዩት ፡ ሲጠፉ፡ ያልታዩት፡ ይተካሉ ። በጠቅላላው ፡ የትናንትናዎቹን ፡ ዛሬ ፡ ባናያቸውም ፣ የትናንትናዎቹን ፡ ስም ፣ መልክና ፡ ቅርጽ፡ የያዙት ፡ ይተካሉ ። ከሰው ፡ ጀምሮ ፡ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ ፍጥረታት ፣ የነበሩት ፡ ሲጠፉ ፡ ያንኑ ፡ ቅርጽና ፡ አቅዋም ፡ የያዙ ፡ ይተካሉ ። ሰሎሞን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ያለው ፡ የነበረው ፡ ሲጠፋ ፡ ያልነበረው ፡ ሲተካ ፡ በመኖሩ ፡ ነው ።

ሳይጠፉ ፡ ለዘለዓለም ፡ በመፈራረቅ ፡ የሚኖሩ ፡ ቀናት ፣ ወራት ፣ ዓመታት ፣ ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፣ ከዋክብት ፡ ናቸው ። ሌሎቹ፡ ፍጥረታት ፡ ይመጣሉ ፣ ይሄዳሉ ፣ ይተካሉ፣እንዳለች ፡ ፀሐይ ፡ ሐሳብዋን ፡ አቋርጩ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ እንደነበረ ፡ ሆኖ ፡ የሚቀር ፡ የለም ። ለምሳሌ ፡ የዛሬው ፡ ለነገ ፡ አይሆንም ፣« ነገ ፡ ለራሱ ፡ ያስባል ፡» እንደተባለው ፡ የነገው ፡ ሌላ ፡ ነው ። ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብት፡ ዛሬ ፡ አገልግሎት ፡ የሰጡት ፡ ሁኔታቸው ፡ ባይለወጥም ፣ የዛሬዎቹ ፡ ከዛሬ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ አልፈው ፣ የነገዎቹ ፡ ከነገው ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ስለሚሰለፉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚታየው ፡ ማናቸውም ፡ ሥነ ፡ ፍጥረት ፡ አላፊና ፡ ተተኪ ፡ እንጂ ፡ ነዋሪ ፡ ሆኖ ፡ አይቀርም ፡ አልኳት ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጥሩ ፡ አስተውለኻል ፣ ከሌሎች ፡ ፍጥረታት ፡ ሁሉ ፡ ፀሐይንና ፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትንም ፡ ለየት ፡ አድርጌ ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ያበረከቱት ፡ ከዛሬው ፡ ጋር ፡ ወር ፡ ተራቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ከነገ ፡ ጋር ፡ የሚሰለፉት ፡ ሌሎች ፡ መሆናቸው ፡ ርግጥ ፡ ስለሆነ ፣ ሁሉም ፡ ተላላፊ ፡ መንገደኛ ፡ መሆናቸውን ፡ አስተዋልኩ ፡ አለችኝ ።

ይህንና ፡ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ስንነጋገር ፡ ሌሊቱ ፡ ለቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ተራውን ፡ ለቆ ፡ የቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ተተካ ፣ ንጋቱንም ፡ አዕዋፍ ፡ በድምፃቸው ፡ አበሰሩ ። የሌሊቱን ፡ የንጋት ፡ መቃረብ ፡ ዶሮች ፡ እያከታተሉ ፡ ቀደም፡ ብለው፡ ድምፃቸውን ፡ በማሰማት፡ ነግረውን ፡ ነበር ።

አሁንም ፡ ደግሞ ፡ የሌሊቱን ፡ ንጋት ፡ አዕዋፍ ፡ ድምፃቸውን ፡ በማሰማት ፡ አበሰሩ ። ከእንግዲህ ፡ በኋላ ፡ እንቅልፍ ፡ ማሸለብ ፡ አንችልም ። አረጋዊ ፡ ማለዳ ፡ እመጣለሁ ፡ ብለውኛልና ፡ ብቅ ፡ ብዬ ፡ ልጠብቃቸው ፡ አልኩና ፡ ከመኝታ ፡ ቤቴ ፡ ወጣ ፡ ብዬ ፡ በቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ተራራውንና ፡ ሸንተረሩን ፡ በአድናቆት ፡ ስመለከት ፡ አረጋዊው ፡ ከተፍ ፡ አሉ ።

ገና ፡ እንዳዩኝ ፡ ሌሊት ፡ ያነጋገርከኝ ፡ አንተነህ? ከዚሁ ፡ ትቼህ፡ እንደሄድኩ ፡ ተመልሼ ፡ ከዚሁ ፡ ያገኘሁህ ፡ አሉኝ ። አዎን ፡ አባቴ ፤ ማለዳ ፡ እመጣለሁ ፡ ብለው ፡ ቃል ፡ ገብተውልኝ ፡ ስለነበር ፡ መምጣትዎን ፡ በናፍቆት ፡ ስጠባበቅ ፡ ነው ፡ አልኳቸው ።

መልካም ፡ ነው ፡ ልጄ ፡ በል ፡ አሁን ፡ ረጋ ፡ ብለን ፡ እንነጋገር ፡ አሉኝ ። እሺ ፡ አባቴ ፡ ወደማረፊያ ፡ ክፍሌ ፡ እንግባና ፡ ከባለቤቴና ፡ ከአስተማሪያችን ፡ ጋር ፡ ላስተዋውቅዎ ። ሌሊት ፡ ከርስዎ ፡ ጋር ፡ ያደረግነውን ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ለሚስቴ ፡ ነግሬያት ፡ እንደርስዎ ፡ ያሉ ፡ አባት ፡ አረጋዊ ፡ ስለምትወድ ፡ በመጓጓት ፡ ትጠብቅዎታለች ፡ አልኳቸው ።

ሚስትህ ፡ አካልህ ፡ ስለሆነች ፤ ርስዋ ፡ ባለችበት ፡ ብንነጋገር ፡ እወዳለሁ ። የሌላ ፡ መጨመር ፡ ግን ፡ ከወሬ ፡ በቀር ፡ የሚጠቅም ፡ አይመስለኝም ። ሆኖም ፡ አንተ ፡ ያመንከውን ፡ እኔ ፡ ተጠራጥሬ ፡ ተጠራጣሪ ፡ አላደርግም ። እኛ ፡ የቀድሞ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉንም ፡ በየዋህነትና ፡ በገርነት ፡ በንጹሕ ፡ ልቦና ፡ በማየታችን ፡ ለሠራነው ፡ ሥራ ፡ የሚበቃ፡ ማስረጃ ፡ የሚሆን ፡ በጽሕፈትና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ማስረጃ ፡ ባለማቆየታችን ፡ የተሠራው ፡ ታሪካዊ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የሌላ ፡ ጠቢባን ፡ እጅ ፡ ይዞ ርበት ፡ ይሆናል ፡ የማለት ፡ ጥርጣሬ ፡ ፈጥሮዋል ።

ስለዚህ ፡ በትክክል ፡ ካላወቁት ፡ ጋር ፡ ገልጦ ፡ መነጋገር ፡ ያልታሰበ ፡ ነገር ፡ ያስከትላል ፡ እየተባለ ፤ ሰውን ፡ ሰው ፡ እንደአውሬ ፡ ሲሸሸው ፡ አያለሁ ። እኔ ፡ በዚህ ፡ ዕድሜዬ ፡ ምንስ ፡ እናገራለሁ ? ብናገርስ ፡ ሽማግሌው ፡ የሚናገረውን፡ አያውቅም፡ ይቀባጥራል፤ እባላለሁ ፡ እንጂ ፤ ነገሬን ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ የሚወስደው ፡ የለም።

ቢሆንም ፡ ልጄ ፡ በክረምት ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ የሞሉ ፡ ጅረቶች ፡ ከሚገናኙበት ፡ ላይ ፡ የተገኘውን ፡ ተላላፊ ፡ ተቀባብለው ፡ እያጣደፉ፡ እንደሚወስዱት ፤ ከአንደበት ፡ የሚወጣውን ፡ የሚነጥቁ፡ ጭልፊቶች፡ አሉ ፡ ሲባል ፡ ስለምሰማ ፡ ብትጠነቀቅ ፡ እወዳለሁ ፡ አሉኝና ፡ ወደማረፊያ ፡ ክፍሌ ፡ ገባን ።

በዚያም ፡ ፀሐይና፡ ክነፊ፡ርግብ ፡ ለአባት ፡ አረጋዊ ፡ የሚገባውን፡ ትሕትናዊ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርበው ፡ መስቀል ፡ ተሳለሙ ። ሁላችንም ፡ ከተቀመጥን ፡ በኋላ ፤ ቡና ፡ ወይም ፡ ሻይ ፡ ልዘዝ፡ አልኳቸው ። አወይ ፡ ልጄ ፡ ምን ፡ አልኩህ ? ማን ፡ እንደሠራው ፡ ማን ፡ ባርኮ፡ እንዳረደው፡



ሳላውቅ ፡ በሆቴል ፡ የተሠራ ፡ ልመገብ ? አላደርገውም ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ገና ፡ ማለዳ ፡ ስለሆነ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ አያስፈልገኝም ፡ አሉኝ ።

አባቴ ፡ ዕድሜዎ ፡ ዘጠና ፡ አምስት ፡ መሆኑን ፡ ነግረውኛል ፤ የወዘናዎና ፡ የሰውነትዎ ፡ ጥንካሬ ፡ ከዕድሜዎ ፡ ጋር ፡ ሲመዛዘን ፡ የሰባ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ እንኳን ፡ አይመስሉም ፤ ከቶ ፡ ምን ፡ ቢመገቡ ፡ ይሆን ? ብዬ ፡ ጠየቅኋቸው ።

ልጄ ፤ ምን ፡ የምመገብ ፡ ይመስልኻል ? በልማዴ፡ በቀን፡ አንድ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እመመገበው ፤ ምግቤም ፡ ዳቦና ፡ እንጀራ ፡ ሲሆን ፤ አብዛኛውን ፡ የምመገበው ፡ ግን ፡ ጥራ ፡ ጥሬ ፤ ቆሎ ፤ አሹቅ ፤ ንፍሮ ፡ ነው ። በመጠጥ ፡ በኩል ፡ በፍስክ ፡ ወራት ፡ ትኩስ ፡ ወተት። በጾም፡ ወራት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠላ ፤ የሚበልጠውን ፡ ጊዜ ፡ ግን፡ የተልባና፡ የሱፍ ፡ ጭልቃ ፡ በማር ፡ ነው ።

አረጋዊው ፡ ንግግራቸውን ፡ በመቀጠል ፡ ልጄ ፡ ቀድሞ ፡ እኛ ፡ ስንማር ፡ የሚበልጠውን ፡ ጊዜ ፡ ምግባችን፡ ውጥንቅጥ ፡ ጥሬ፡ ስለሆነ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አዘውትሬ ፡ እመገብ ፡ ስለነበር ፤ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ምግብ ፡ ብመገብ ፡ በመጠኑም ፡ ቢሆን ፡ ጥሬ ፡ ካልጨመርኩ ፡ የተመገብኩ ፡ አይመስለኝም ፡ እንዳሉ ፤ አባቴ ፡ ጨዋታዎ ፡ እንደመጣሙ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ማዳመጥ ፡ በተገባኝ ፡ ነበር ። ግን ፡ አንዳንድ ፡ የማላውቃቸው ፡ ቃላት ፡ ሲናገሩ ፡ ማወቁ ፡ ለእኔ ፡ ትምህርት ፡ ስለሆነ ፡ አልኩና ፡ «ውጥንቅጥ ፡ ጥሬ ፡» ያሉት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ እንዲነግሩኝ ፡ ላቋርጥ ፡ ወደድሁ ፡ አልኳቸው ።

መልካም ፡ ነው ፡ ልጄ ፡ አሉና ፡ «ውጥንቅጥ፡ ጥሬ ፡ » ፡ ያልኩት፡ ከትምህርት ፡ ውጭ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ገብስ ፤ ስንዴ ፤ ባቄላ ፤ ሽንብራ ፤ ኑግ ፤ ተልባ ፤ በቆሎ ፤ ዘንጋዳ ፤ ማሽላ ፤ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሳሰለውን፡ ከሕዝቡ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እየጠራን ፡ ለምነን ፡ ሲዘከረን ፡ ቀላቅለን ፡ እንይዘዋለን ።

አባቴ ፡ አመሰግንዎታለሁ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጐልማሳ ፡ ስለሆኑ ፡ አሁን ፡ በዘጠና ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜዎ ፡ በጥርስዎ ፡ በኩል ፡ አይቸገሩም ?

አዬ ፡ አለማወቅ ፤ አለማወቅ ፡ ለካ ፡ እንዴት ፡ መጥፎ ፡ ነው ። ከአንተና ፡ ከኔ ፡ ጥርስ ፡ በል ፡ የማንኛችን ፡ ተፈጥሮውን ፡ ጠብቆ፡ እንዳለ፡ እንተያይ ፡ አሉና ፡ ከፊት ፡ ጥርሳቸው ፡ ጀምሮ ፡ መንጋጋቸውን ፡ ከፍ

ተው ፡ ቢያሳዩኝ ፡ ከንጣቱና ፡ ከንጽሕናው ፡ ጋር ፡ ግጥግጥ ፡ እንዳለ ፡
ከመታየቱም ፡ ይልቅ ፤ ባነቃንቀው ፡ ጥንካሬው ፡ እንኳን ፡ ቆሎ ፡ ድን
ጋይ ፡ ይሰብራል ። ምክንያቱንም ፡ ሲያስረዱኝ ፡ ቆሎ ፡ አዘውትሮ ፡
የሚመገብ ፡ ሁሉ ፡ ጥርሱ ፡ ይጠነክራል ። እኔ ፡ አባትህ ፡ ቆሎ ፡ ብመ
ገብም ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ መፋቂያ ፡ ጥርሴን ፡ ፍቄ ፡ በውሃ ፡ እጉመጠ
መጣለሁ ፡ ብለው ፡ ከእጇ ፡ ጠባባቸው ፡ ኪስ ፡ መፋቂያ ፡ ወጣ ፡ አድር
ገው ፡ አሳዩኝ ።

ፀሐይና ፡ ከነፈ፡ ርግብ ፡ በአረጋዊው ፡ አገላለጥ ፡ ተመስጠው ፡
ፍጹም ፡ በሆነ ፡ ፀጥታ ፡ ሲያዳምጡ፡ ልጄ ፡ አንተና ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ እን
መላለሳለን ፡ እንጂ ፤ ባለቤትህና ፡ ጓደኛህ ፡ ዝምታ፡ ስላበዙ ፡ ምንም፡
እንኳን ፡ እንደእኔ ፡ ከመለፍለፍ፡ ዝምታ ፡ የሚመረጥም፡ ቢሆን፤ ዝም፡
የሚል ፡ ሬሳ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሕይወት ፡ ካለ ፡ መናገር ፡ ይገባል፡ አሉ።

አባቴ ፡ ይቅርታ ፡ ያድርጉልኝ ። ንግግርዎ ፡ በአዕምሮዋችን ፡
ጠልቆ ፡ ስለገባና ፡ የማናውቀውን ፡ ስለተማርን፡ ያዳመጥንዎ፡ ከልብ፡
ነው ፤ አለችና ፡ ፀሐይ ፤ በሰውነትዎ ፡ ላይ ፡ የረበበ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡
አለ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ዕድሜዎ ፡ ዘጠና ፡ አምስት፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡
በሰውነትዎ ፡ ላይ ፡ የሚታየውን ፡ ወዘና ፡ ይህ፡ ነው፡ ብዬ ፡ ልናገረው፡
ከቶ ፡ አልችልም ። ምግብዎንና ፡ መጠጥዎን፡ እንደነገሩን ፡ በጉልማስ
ነትዎ ፡ ወራት ፡ ማለት ፡ የእሳት ፡ ባሕርይ ፡ ይሰማዎት፡ በነበረበት ፡
ወቅት ፡ የሚያጽታውሱት ፡ የልጅነት ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ነበር ?

እሃ ፡ ለካስ ፡ ብርቱ ፡ ነሽ ፡ አሉና፡ እግዚአብሔር፡ አላደኸየኝም፡
አላከበረኝም ፤ በመካከለኛ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ፡ ላይ ፡ አቁሞኛል ። ለሰው ፡
ባልተርፍም ፡ የሰው ፡ አልከጅልም ። በሰው ፡ ላይ ፡ የማየው ፡ አያጓጓ
ኝም ፤ የሰጠኝን ፡ በምስጋና ፡ በመቀበሌ ፡ በቤቴ ፡ የገባው ፡ ትንሹ ፡
ይበረከታል ።

ሰው ፡ የእሳት ፤ የውሃ ፤ የመሬት ፡ የነፋስ ፡ ባሕርይ ፡ እንዳለው ፡
ሁሉ ፡ እንዚህ ፡ ከዕድሜ ፡ ጋር ፡ የሚጐዳኙ፡ የሰው፡ የሕይወት ፡ ታሪክ፡
ናቸው ። ያም ፡ ሆነ ፡ ይህ ፤ የሚጠቅምንና፡ የማይጠቅምን፡ የማመዛዘን፡
ኃይል ፡ በሰው ፡ የተፈጥሮ ፡ ባሕርይ ፡ ውስጥ ፡ አለ ።

ይህ ፡ በሥራ ፡ የሚገለጠው ፡ በሥጋ ፡ ፍላጐት ፡ ድል ፡ ከመሆን፡
የተነሣ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠኝ፡ ጸጋ ፡ ሥጋዊ ፡ፍላ
ጐቴን ፡ ድል ፡ አድርጌው ፡ ከዚህ ፡ ደረስኩ ፡ እንጂ ፡ ድል ፡ አላደረገ



ኝም። ከዚህም ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ የተሰጠኝ ፡ ጸጋ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ቢሆን፡
የሚያናድደኝ ፤ የሚያበሳጨኝ ፤ የሚያሳዝነኝም ፡ ነገር ፡ የለም ።

ምንም ፡ ብሰማ ፡ በሳቅና ፡ በትዝብት፡ አልፈዋለሁ ። ጦር ፡ መዞ፡
ጐራዴ፡ ነቅንቆ ፡ ጠብመንጃ፡ አቀባብሎ፡ ሊገልህ ፡ መጣ፡ ቢሉኝ፡ እስ
ቃለሁ ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ አልፈራም ። አልጨነቅም ፤ አላስብም፤ ወደዚህ
ዓለም ፡ ያመጣኝ ፡ የሰጠኝን ፡ ዕድል ፡ ማንም፡ ስለማያስቀረውና፡ ሁን፡
ያለው ፡ መሆኑ ፡ ስለማይቀር ፡ ነው ።

በተማሪ ፡ ቤት ፡ በነበርኩበት ፡ በጐልማሳ፡ ወራቴ፤ ንጽሕናዬን፡
ጠብቄ ፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አገለግል ፡ ነበር። ትምህርቴን ፡ አጠ
ናቅቄ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሀገሬ ፡ ስመጣ ፡ አባትና ፡ እናቴ፡ ስለነበሩ ፡
በብርቅ ፡ ተቀብለው ፡ አሁን ፡ አብራኝ ፡ ያለችውን ፤ የትናንትዋን ፡
ጉብል ፡ የዛሬዋን ፡ አሮጊት ፡ በነርሱ ፡ መራጭነት፡ በሕግ ፡ በሥጋ ፡
ወደሙ ፡ ዳሩኝ ።

በማከታተል ፡ ሁለት ፡ ወንዶችና ፡ ሁለት ፡ ሴቶች ፡ ወለድን ።
አባትና ፡ እናቴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፤ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡
ያላቸው ፤ በምግባራቸው ፡ በሀገር ፡ የታወቁ ፡ በግብርናና ፡ በንግድ ፡
የሚኖሩ ፡ መሃይምናን ፡ ነበሩ ።

ባለማወቅ ፡ ከሚያደርጉት ፡ በቀር ፡ እያወቁ ፡ ሰውን ፡ የሚያሳዝ
ኑና ፡ የሚጐዳ ፡ የማይሠሩ ፤ ፍጹም ፡ የሆኑ ፡ ደጎች ፤ ቸሮችና ፡ ርኅ
ሩኆች ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ጠባያቸው ፡ ተከብረውና፡ ፍቅርን፡ ከሀገሬው፡
ሕዝብ ፡ አትርፈው ፡ የኖሩ ፡ ናቸው ።

በልጅ ፡ በኩል ፡ ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ የላቸውም ። ለትምህ
ርት ፡ ወደሰሜን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሄድኩ፡ ጊዜ ፡ የተሰማቸው ፡ ኀዘን ፡
እጅግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደነበር ፡ ሳወሳው ፤ በተመለስኩ፡ ጊዜ ፡ ይታይ
ባቸው ፡ የነበረው ፡ ደስታ ፡ በዚሁ ፡ መጠን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበር ።

ከዚህም ፡ የተነሣ ፤ እንደመጣሁ ፡ ሚስት ፡ አጋቡኝ። የልጅ ፡ ልጆ
ቻቸውን ፡ ዐይተው ፡ ድካም ፡ ወደሌለበት ፡ ዓለም፡ በሞት ፡ ተለዩን ።
ወንዶቹ ፡ ልጆቼ ፡ ጠለቅ ፡ ብለው ፡ መንፈሳዊ፡ ትምህርት ፤ ስለተከታ
ተሉ ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነታቸውን ፡ ጠብቀው፡ በግብርና ፡ ሥራ ፡ ይኖሩ፡
እንጂ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ዕድል ፡ አግኝተው ፤ በእግሬ ፡
ተተክተዋል ።

ሴቶች ፡ ልጆቼም ፡ እንደዚሁ ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ያላቸውን ፡ አግብተው ፡ ይኖራሉ ። እያንዳንዳቸው ፡ በርከት፣ ያሉ ፡ ልጆች ፡ ወልደው ፡ ቅድመ ፡ አያት ፡ ሆኛለሁ ። የዚህ ፡ ዓለም፣ ኑሮ ፡ ቢመርም ፡ እየታገሉ ፡ መኖር ፡ ይመረጣል ፡ እንጂ ፤ በቃኝ ፡ የሚል፣ የለም ።

የዘጠና ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ሽማግሌ ፤ እስካሁን ፡ ከሰው፣ እጅ፣ አልወደቅሁም ። እንደዚህ ፡ እንዳማረብኝ ፡ ብሸኝ ፡ እወዳለሁ ። ከቆየሁ ፡ የተወደድኩትንና ፡ የተከበርኩትን ፡ ያህል ፡ ጥላቻንና ፡ መሰልቸትን ፡ አተርፋለሁ ። አሁን ፡ እንኳን ፡ የሽማግሌ፣ ነገር ፡ ሆኖ ፤ የማያስፈልገውን ፡ ሁሉ ፡ ስዘበዝብ ፡ ሳትሰለቹኝና፣ ሳትታዘቡኝ፣ አልቀራችሁም ፡ ብለው ፡ ንግግራቸውን ፡ ጨረሱ ።

እወይ ፤ ምነው፣ አባቴ! አለችና፣ ፀሐይ ፡ የነገሩን ፡ ከመኖር ፡ የተገኘ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ ስለሆነ ፤ ትምህርት ፡ ነው ። ይልቁንም፣ ለዛ በአለው ፡ አነጋገርዎ ፡ ሀገሩ ፡ ተራራማና ፡ ጉራንጉር ፡ ሲሆን፤ የሕዝቡን ፡ አኗኗር ፡ በቀድሞውና ፡ በዛሬው ፡ መካከል፣ ያለውን፣ ልዩነት፣ ቢነግሩን ፡ አለቻቸው ።

ዋ ፤ የቀድሞና ፡ የዛሬ ፡ አኗኗር ፡ በጣም፣ የተለወጠ ፡ ስለሆነ፣ ስንቱን ፡ እነግራችኋለሁ ? የቀድሞ ፡ ሰው ፡ ፍላጎት ፡ የተወሰነ ፡ ነበር። ኑሮው ፡ ጠባብ ፡ ነው ። ጌታ ፡ የሚባለው ፡ ጠጅና ፡ ሥጋ ፡ ተመግቦ ፡ የሚመግብ ፡ ነበር ። ያንዱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከሌላው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ጋር ፡ የነበረው ፡ ግንኙነት ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ ነበር። በአንዱ ፡ ወረዳ ፡ ግዛት ፡ የደረሰው ፡ ክፉውና ፡ ደጉ ፡ በቀላል ፡ አይሰማም ፡ ነበር ።

ያንዱን ፡ ባህልና ፡ የውስጥ ፡ አኗኗር ፡ ሌላው ፡ በቀላል ፡ አያውቅም ፡ ነበር ። ልጄ ፡ እኔ ፡ ስንቱን ፡ ልንገራችሁ ? በሰዎች ፡ መካከል ፡ ይታይ ፡ የነበረው ፡ ፍቅርና ፡ መተማመን ፡ ቀላል፣ አልነበረም። ቃል ፡ ይከበር ፡ ነበር ፤ የሚበልጠው ፡ ቁም ፡ ነገር፣ ይሠራ ፡ የነበረው፣ በቃል ፡ ተነጋግሮ ፡ በመተማመን ፡ ነበር ። ከፍ፣ ያለ፣ ገንዘብና ፡ ይህን፣ የመሰለ ፡ የክብር ፡ ዕቃ ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ዘንድ፣ አደራ ፡ የሚያስቀምጠው ፡ በቃል ፡ ንግግር ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

«ባልንጀራህን ፡ እንደራስህ ፡ ውደደው፣ » የተባለው ፡ ቃል ፡ ይፈጸምበት ፡ የነበረው ፡ ዘመን ፡ አለፈ ፤ ለወደደው ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ አሳ



ልፎ ፡ ይሰጥ ፡ የነበረበት ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ እንዳልነበረ ፡ ሆነ ። ዕድሜ ፡ መስተዋት፣ ስለሆነ ፤ ያንንም ፡ ይህንንም ፡ በማየቴ፣ በትካዜ፣ ተውጬ፣ የምደነቅባቸው ፡ ነገሮች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ የጠቀስኳቸውን ፡ ቁም ፡ ነገሮች ፡ ሲሠርዋቸውና፣ ሲያሠርዋቸው ፡ የነበሩት ፤ በተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ የተሰጣቸው ፡ በሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ ግን ፡ ትምህርት ፡ የሌላቸው ፡ ነበሩ ።

እነዚህን ፡ የመሰሉት ፡ ሰዎች ፡ በዛሬ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠሩበት ፡ ስም፣ መሃይምን ፡ ነው ። ልጄ ፡ ሰው ፡ የተፈጥሮ ፡ ዕውቀት ፡ ያለው፣ ስለሆነ፣ መሃይምን ፡ ሊባል ፡ አይገባም ። እንዲያውም ፡ የሚጽፍ ፡ አባይ ፡ ጠንቋይ ፡ እየተባለ ፡ ይጠላ ፡ የነበረበት ፡ ዘመን ፡ አልፎ ፤ ያልጻፈ ፡ መሃይምን ፡ ነው ፡ ከተባለበት ፡ ዘመን ፡ ደረስን ፡ ሲሉ ፤ ፀሐይ ፡ አባታችን ! አለችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ጥንት ፡ በመኖራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆኑ ፡ መጻሕፍት ፡ በጥሩ ፡ የእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ በመጻፋቸው ፤ ዛሬ ፡ ለታሪክ ፡ ማስረጃዎች ፡ ሆነዋል ። አባይ ፡ ጠንቋይ ፡ እየተባሉ ፡ ይጠሩ ፡ የነበሩት ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ? ብላ ፡ ጠየቀቻቸው ።

ልጄ ፤ ይህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ያንቺ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ዛሬ ፡ የሁሉም፣ ሆንዋል ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አልነበረም ። እንዲያውም ፡ ልጄ ፡ ጥሬት ፡ የተማረ ፡ ወይም ፡ ያወቀ ፡ እንደሆነ ፡ ጠንቋይ፣ ይሆናል፣ እያሉ ፡ ልጆቻቸው ፡ እንዳይማሩ ፡ ይከላከሉ ፡ ነበር ። እኔም፣ ከወላጆቼ፣ ጋር ፡ ተቀምጬ ፡ ትኩስ ፡ እንጀራ ፡ እየተመገብኩ ፡ መማር ፡ ስወድ ፡ ወላጆቼ ፡ እንድማር ፡ ፍላጎት ፡ እንደሌላቸው ፡ ዐውቄ ፡ ነው፣ ጠፍቼ፣ ሄጄ ፡ በልመና ፡ የተማርኩት ።

በጽሕፈትም ፤ ቁም ፡ ጸሐፊ ፡ ስለሆንኩ ፤ የጻፍኩት ፡ ዳዊትና ፡ ተአምረ ፡ ማርያም ፡ እያንዳንዱ ፡ ፊደል ፡ የአንቺን ፡ ዓይን ፡ ይመስላል። ልጄ ፡ ምን፣ ያደርጋል ? ርጅና ፡ መጣ ። ርጅናና ፡ ሞት ፡ ቀን ፡ ቈጥረው ፡ የሚመጡ ፡ ስለሆኑ ፤ ዓይን ፡ ሳይፈዝ ፡ ጉልበት ፡ ሳይደክም ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ የሚያስታውስ ፡ ሥራ ፡ ለመተው ፡ መጣጣር ፡ ያስፈልጋል ። ከሠራኋቸው ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፤ ማንነቴን ፡ ሲመሰክሩ ፡ የሚኖሩ ፡ በእጄ ፡ የጻፍኳቸው ፡ ናቸው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ጽሕፈት ፡ ካወቀ ፡ ጠንቋይ ፡ ይሆናል ፡ እያሉ፣ ልጆቻቸው ፡ እንዳይማሩ ፡ ያደረጉት ፤ እጠነቀቃለሁ፣

ማለትና ፡ ማስጠንቀል ፤ ለክርስትና ፡ እምነት ፡ ነቅ ፡ የሚያስከትል ፡ እየመሰላቸው ፡ ነበር ። በጽሕፈት ፡ ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ይልቅ ፡ በቃል ፡ ተነጋግሮ ፡ የሚሠራው ፡ የበለጠ ፡ ዋጋም ፡ ነበረው ።

ልጄ ፡ እስቲ ፡ ልጠይቅሽ ፤ ዛሬ ፡ እንደምንሰማው ፡ ከሆነ ፤ በጽሕፈትና ፡ በፊርማ ፡ የታሠረው ፡ ቃል፡ ይከዳል ፡ ይላሉ ። ልጄ ፤ በዘመነ፡ ብሉይ ፡ የነበረውና ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ የሆነውንም ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘውን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፤ በዘመናት ፡ የነበሩት ፡ በጽሕፈት ፡ ቢያቆዩት ፡ አይደለም ፡ ዓለም ፡ በብርሃኑ ፡ የሚመራው ?

ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዘመን ፡ ከተቈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ያለው ፡ ወደፊትም ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ የሚኖረው ፡ ከቃል ፡ ወይም ፡ ከአንደበት ፡ የሚወጣውና ፡ የወጣው ፡ በጽሕፈት ፡ እየሆነ ፡ በመተላለፉ ፤ ያለፈውንም ፡ ሆነ ፡ የወደፊቱን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ እያወቀ ፡ በመመራመሩ ፡ በጥበብ ፡ ተራቆ ፡ ከዚህ ፡ ከረቀቀው ፡ ዘመን ፡ ደርሰዋል ።

በዕድሜ ፡ የገፉን ፤ ያለፈውንና ፡ አሁን ፡ ያለበትን ፡ ዘመን ፡ ስናስተያይ ፤ ለውጡ ፡ እየተፋጠነ ፡ ሄዶ ፡ የሰው ፡ አዕምሮ፡ ይሆናል፡ ብሎ፡ የማይገምተው ፡ ሆነ ። ወደፊት ፡ ከዚህ ፡ የበለጠም ፡ ይታይ፡ ይሆናል፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ እኔና ፡ እኔን ፡ የመሰሉ ፡ በዕድሜ ፡ የገፉ ፡ የማየት ፡ ዕድል፡ አይኖራቸውም ፡ ይሆናል ።

ልጄ ፡ በጥያቄሽ ፡ ላይ ፡ ሀገሩ፡ ተራራማና ፡ ጕራንጕር ፡ ሲሆን ፤ ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ እንደምን ፡ ከዚህ ፡ ሥፍራ ፤ እነዚህን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አሳነፀ ፡ ብለሻል ? ዋ ፤ ልጄ ፡ ታምራት ፡ የሚሠራበትና ፡ የሚገለጽበት ፡ ሥፍራ ፡ አሳቻ ፡ የሆነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምቾትን ፡ ብቻ ፡ የሚመለከት ፡ አይደለም ።

ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ «በአንድ፡ ሺህ ፡ አንድ ፡ መቶ፡ አንድ፡ በላስታ፡ አውራጃ ፡ በቡግና ፡ ወረዳ ፡ ሮሀ ፡ ከምትባል ፡ ዋሻ፡ ተወለደ ። በልደቱ፡ ጊዜ ፡ መላእክት ፡ በንቦች ፡ ተመስለው ፡ ከበውታል ። ወላጅ ፡ እናቱ ፡ በንቦች ፡ መከበቡን ፡ አይታ ፡ የዋግ ፡ ተወላጅ፡ ስለነበረች ፡ በአገውኛ፡ ቋንቋ ፡ ላል ፡ ከቦታል ፡ አለች ። ላል ፡ ማለት ፡ በአገውኛ ፡ ቋንቋ ፡ ንብ ማለት ፡ ነው ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አናግርዋት ፤ ይህ ፡ ሕፃን ፡ ትልቅ ፡ ንጉሥ ፡ ይሆናል ፡ ብላ ፡ ትንቢት ፡ ተናግራ ፡ ነበር ፡ ይባላል ።



ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ለአካለ፡ መጠን፡ ደርሶ ፡ በወንድሙ ፡ በገብረ ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲወጣ ፡ ሲገባ ፤ በመልኩ ፡ ማማርና ፡ በግርማ ፡ ሞገሱ ፡ ይንግሣል ፡ እያሉ ፡ በጥርጣሬ ፡ ስለፈሩት፤ ቤተሰቡ፡ ጠሉት ። ይህ፡ በዚህ ፡ ሳለ ፡ ከዕለታት ፡ አንድ፡ ቀን፡ የኮሶ፡ መድኃኒት፡ መጠጣቱን ፡ ለእኅቱ ፡ ነገራት ። የአባቱ ፡ ልጅ ፡ እኅቱም ፡ በዘመኑ ፡ የነገሠው ፡ ከአንድ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ የሚወለድ ፡ ወንድምዋ ፡ ስለነበር ፤ ለርሱ ፡ አድልታ ፤ ደግ ፡ ነገር ፡ ያዘጋጀች ፡ አስመስላ ፤ እሩት ፡ የሚባል ፡ መርዝ ፡ ከጠላ ፡ ጋር ፡ ቀላቅላ ፡ ላከችለት ።

የላከችው ፡ በዲያቆን ፡ እጅ ፡ ስለነበር ፤ ቀምሶ ፡ መስጠት ፡ ሥርዓት ፡ ስልሆነ ፤ ጠላውን ፡ በጽዋ ፡ ቀድቶ ፡ ቀምሶ ፡ ከላሊበላ ፡ ፊት ፡ አስቀምጦ ፡ መለስ ፡ ሲል ፤ ወድቆ ፡ አስታውኮ ፡ ሞተ ። በዚህን፡ ጊዜ፡ ውሻ ፡ ስለነበር ፡ ትውኪያውን ፡ ቢቀምስ ፡ ወደዚያው ፡ ሞትዋል ።

ላሊበላ ፡ ግን ፡ ለርሱ ፡ በተዘጋጀው ፡ መርዝ ፡ ሁለት ፡ ነፍሳት ፡ በመሞታቸው ፡ ሞትን ፡ ሳይፈራ፡ ከፊቱ ፡ የተቀመጠውን ፡ ጽዋ ፡ አንሥቶ ፡ ጠጣው ። መርዙ ፡ እርሱን ፡ ሳይጎዳ ፡ እንዲያውም ፡ በሆዱ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የኖረ ፡ ደዌ፡ ፈውሶት፡ መድኃኒት፡ ሆነው ፡ » ይባላል ።

በአጭር ፡ የነገርኳችሁ ፤ ስለራሱ ፡ ታሪክ ፡ ሲሆን ፤ ስለአሳነፃቸው ፡ ሕንፃ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በጥቂቱ ፡ ልነግራችሁ፡ እወዳለሁ።

«ገናና ፡ የነበረው ፡ የአክሱም ፡ መንግሥት፡ እየተዳከመ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፤ የመንግሥቱ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ የላስታ ፡ አውራጃ ፡ ከተማ ፡ ወደ ነበረችው ፡ ወደ፡ ሮሀ ፡ ተዛወረ ።

ሮሀ ፡ ዛሬ፡ ላሊበላ፡ ተብሎ፡ በሚጠራው ፡ በአሥራ ፡ ሁለተኛው፡ መቶ ፡ዓመት፡ ነግሦ ፡ በነበረው ፡ በዛጔ ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ ስም ፡ ትጠራለች።ንጉሡ፡ ነገሥት፡ ላሊበላ፡ ብዙዎች፡ ከዓለት፡ ድንጋይ፡ ተጠርበው፡ የተሠሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በማሳነፅ ፡ ስመ ፡ ጥሩነትን ፡ አግኝቷል ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በዓለም ፡ መንፈሳዊ ፡ ገዥ ፡ ስለነበረ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ብላ ፡ ሰይመዋለች ። የቤተ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ሕንፃዎች ፡ ያማረ ፡ አሠራር ፡ ስላላቸው ፡ ከዓለም ፡ እየመጡ ፡ ይጐበኙዋቸዋል ።

ቤተ ፡ አማኑኤል ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕንፃ ፡ የሚያምርና፡ የሚያስደንቅ ፡ ነው ። ተጠርቦ ፡ ከወጣበት ፡ ዓለትም ፡ ባጌጠ ፡ ሁኔታ ፡ ተቀርጾ ፡ ይታያል ። ለአክሱም ፡ ሐውልት ፡ መሰልነት ፡ ባለው ፡ ዓይነት ፡ ምድር ፡ ቤትና ፡ ፎቅ ፡ መስኮቶችም ፡ ተበጅተውበት ፡ የታነፀው፡ መቅደስ ፡ በመሠራቱ ፡ ጥንታዊውን ፡ የአክሱማውያንን ፡ የሕንፃ፡ አሠራር፡ ዕቅድ ፡ የተከተለ ፡ ይመስላል ። ውስጡ ፡ አራት ፡ ዓምዶች ፡ ያሉበት ፡ አዳራሽ ፡ ወይም ፡ ሰፊ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ወደሠገነቱም ፡ የሚያወጣው፡ ደረጃ ፡ ከዚያው ፡ ከዓለቱ ፡ ተጠርቦ ፡ የተበጀ ፡ ነው ።

የበሮቹም ፡ ሣንቃዎች ፡ በወፍራሙ ፡ ተጠርበው ፡ በአራቱ፡ በር፡ ምድራክና ፡ ጕበን ፡ ተሹለው ፡ የገቡ ፡ ስለሆኑ ፤ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ የሚሆነውን ፡ ጊዜ ፡ ሳይናወፁ ፡ አሳልፈውታል ።

ቤተ ፡ ሊባኖስና ፡ ቤተ ፡ ገብርኤል ፤ በቤተ ፡ አማኑኤል፡ አጠገብ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ይገኛሉ ። ቤተ ፡ ገብርኤል ፤ (ሩፋኤል ፡ ) የዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንፃ ፡ ወደፊት ፡ በኩል ፡ በጐኑ ፡ ኪስ ፡ ዓይነት ፡ በሆኑ ፡ ቅርፆች ፡ ተጊጧል ። አናቱም ፡ የአክሱም ፡ ሐውልቶች ፡ ከወደ አናታቸው ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ቅርፅ ፡ ይመስላል ። ወደ ፡ መቅደሱ ፡ የሚወስደው ፡ መተላለፊያ ፡ በግንዶች ፡ የተበጀ ፡ ድልድይ ፡ ነው ። መቅደሱ ፡ በቅስት ፡ ዓምዶች ፡ የተሠራ ፡ ነው ። በጌጠኛነቱ ፡ ግን፡ የአማኑኤልን ፡ መቅደስ ፡ አያክልም ።

እነዚህ ፡ አራት ፡ መቅደሶች ፡ በመጨረሻ ፡ ያሠራቸው ፡ ናቸው ፡ ይባላል ። በጥንት ፡ ጊዜ ፡ ከአንዱ ፡ መቅደስ፡ ወደሌላው ፡ የሚያስተላልፍ ፡ የተፈለፈለ ፡ የውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ መንገድ ፡ ነበራቸው ። በአንዳንድ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አሁንም ፡ መውጫ ፡ መግቢያ ፡ የነበረው ፡ ፍልፍል፡ በር ፡ ይታያል ። ካንዱ ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ አያዘልቅም፡ እንጂ፡ወደ፡ ውስጥ ፡ ጥቂት ፡ መንገድ፡ ያስኬዳል። የቀረውን፡ ቦታ ፡ ግን፡ ለስላሳው፡ ተጠራቢ ፡ ድንጋይ ፡ ደፍኖታል ።

ቤተ ፡ ሊባኖስ ፤ ላዩ ፡ እንዳለ ፡ አፈር ፡ የለበሰ ፡ መሬት ፡ ሆኖ ፡ መቅደሱ ፡ ዙሪያውን ፡ ከዓለቱ ፡ እንደዋሻ ፡ ተፈልፍሎ ፡ በሚያምር ፡ ቅርፅ ፡ ታንፆ ፡ ይገኛል ። የመቅደሱ ፡ ሕንፃ ፡ ዓይነት ፡ ከሌሎቹ ፡ መቅደሶች ፡ የሚለየው ፡ አናቱ ፡ ተፈልፍሎ ፡ ከተበጀለት ፡ ዓለት ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ በመገኘቱ ፡ ነው ። መቅደሱ፡ መጠነኛ ፡ ነው ። ሥራው፡ግን፡ ውጪውንም ፡ ሆነ ፡ በውስጡ ፡ በኩል ፡ የሚወጣለት ፡ ሳኻ ፡ ወይም ፡



እንከን ፡ የለውም ። የመቅደሱ ፡ አናት ፡ ከታነፀበት ፡ ዓለት፡ ያልተለየ፡ በመሆኑ ፡ በላሊበላ ፡ ያሉት ፡ ሕንፃዎች ፡ ሥራ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደተከናወነ ፡ ያስረዳል ።

ቤተ ፡ መርቆሬዎስ ፤ መቅደሱ ፡ የዋሻ ፡ ቅጥ ፡ ያለው ፡ ነው ። ሥራው ፡ ዓምዶችና ፡ መስኮቶች ፡ ስላሉት ፡ ነው፡ እንጂ ፤ እንደሌሎቹ፡ ጌጠኝነት ፡ የለውም ። የነበሩት ፡ ዓምዶች ፡ በዘመን ፡ ተበልተው፡ ተሰባብረዋል ። መቅደሱም ፡ ራሱ ፡ ከእርጅናው ፡ የተነሣ ፡ ተጐሳቁሏል ።

ቤተ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፤ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕንፃ ፡ ሥራ ፤ እንኳንስ ፡ በቅስት ፡ በተያያዙ ፡ ዓምዶች ፡ ያጌጠው ፡ ሰፊው ፡ የውስጡ ፡ መቅደስ ፡ ይቅርና ፡ የመቅደሱ ፡ ሕንፃ ፡ ውጪውም ፡ ግሩም ፡ በሆነ ፡ ቅርፅ ፡ ተጊጦና ፡ ተሸልሞ ፡ የተሠራ ፡ ነው ። የሕንፃው ፡ ቅርፅ ፡ መስቀልኛ ፡ ስለሆነ ፤ አጠር ፡ ያለ ፡ ነው ። ውጪውን ፡ የሚታየው ፡ የመቅደሱ ፡ አናት ፡ በመስኮቶች ፡ በበሮች ፡ አምሳል ፡ ተፈልፍሎ ፡ ቅስት ፡ ባለው ፡ ቅርፅ ፡ ተጊጥዋል ። ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕንፃ ፡ ስብሳብ፡እንዲሆነው ፡ የተበጀ ፤ ተዛነቡም ፡ በክፈፍ፡ ተጊጦ ፤ ተቀርፆ ፤ ዙሪያውን፡ አያሌ ፡ ዓምዶች ፡ በተስተካከለ ፡ ተራ ፡ ደግፈውታል ። በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ቅስቶች ፡ ባማረ ፡ የሐረግ ፡ ጌጥ ፡ የተሸለሙ ፡ ናቸው። የቤተ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ሕንፃ ፡ በጌጠኝነቱ ፡ ሆነ ፡ በአሠራሩ ፡ የተለየ ፡ ዓይነት ፡ አለው ።

ቤተ ፡ ማርያም ፤ ቤተ ፡ መድኃኔ ፡ ዓለም ፡ ተፈልፍሎ፡ ከወጣበት፡ አቈቋማ ፡ ዓለት ፡ ኮረብታ ፡ ተፈልፍላ ፡ የወጣች ፡ ናት ፤ ይህችም፡የቅድስት ፡ ማርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአማረ ፡ ሁኔታ ፡ ታንፃ ፡ የተሠራች ፡ ናት ። ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ካነፃቸው ፡ ሕንፃዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ያነፃት ፡ እርስዋን ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይተረካል ። የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕንፃ ፡ ውስጡ ፡ ግሩም ፡ በሆነው ፡ የሐረግ ፡ ቅርፅ ፡ በኩልም ፡ ሆነ ፡ በውስጥ ፡ በሚገኙት ፡ ዓምዶችም ፡ ቅርፅና ፡ በአናታቸው ፡ ላይ ፡ በሚገኙት ፡ ቅስቶችም ፡ ቢሆን ፡ ጌጠኛ ፡ ሆኖ ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ይህች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ሲጸልይባት ፡ የነበረችና ፡ እንደሚባለውም ፡ የሕንፃ ፡ ሥራዎቹ ፡ መጀመሪያ ፡ እንደመሆንዋ ፡ ሁሉ ፡ የመቅደሱ ፡ አሠራር ፡ በውስጡ ፡ ጌጠኝነትና ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በጣራውና ፡ በቅስቶቹ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ተደናቂ ፡ ነው ። በውጪ ፡ ግድግዳዋ ፡

በምዕራቡ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ጦር ፡ የያዙ ፡ የሁለት ፡ ፈረሰኞች ፡ ምስል ፡ ባለው ፡ አቀራረፅ ፡ ስልት ፡ ተስለው ፡ ይታያሉ ።

ቀደም ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ ፈረስ ፡ ቀኝ ፡ ታፋ ፡ ላይ ፡ የአሞራ ፡ (የንስር ፡ ) ሥዕል ፡ አለበት ። በፈረሱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የፀሐይ ፡ ምልክት፡ እንዲሆን ፡ ታስቦ ፡ የተቀረፀ ፡ ነው ። በላሊበላ ፡ የሚገኙት ፡ ከአንዱ ፡ ድንጋይ ፡ ወጥ ፡ ሆኖ ፡ የተሠሩት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕንፃዎች ፡ ሥራ ፡ መሪና ፡ ሊቅ ፡ የነበረው ፡ አሠሪ ፡ ግሩም ፡ የሆነውን ፡ የሥራውን ፡ ጥበብ ፡ በዚች ፡ በቤተ ፡ ማርያም ፡ ሕንፃ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ጌጥ ፡ ሊገልጥ ፡ ችልዋል ።

ቤተ ፡ ሚካኤል ፤ የመቅደሱ ፡ ሕንፃ ፡ ከፍተኛና ፡ ሰፋትም ፡ያለው ነው ። ከስፋቱ ፡ የተነሣ ፡ የመቅደሱ ፡ ሕንፃ ፡ ውስጡ ፡ ሁለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ። ይህ ፡ ቤተ ፡ ሚካኤል ፡ የተባለው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቤተ ፡ ማርያም ፡ በስተምዕራብ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ። በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ ጽላቶች ፡ ይገኙበታል ። በአንደኛው ፡ በሩን ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ባለው ፡ ክፍል ፤ የቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ጽላት ፡ አለበት ። ወደውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ደግሞ ፡ በሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ ስድስት ፡ ጽላቶች ፡ አሉ ። በቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ስም ፡ የተቀረፀው ፡ ጽላትም ፡ በዚሁ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ይገኛል ። የቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ መቃብር ፡ ዋሻው ፡ ተፈልፍሎ ፡ በተሠራው ፡ በዚሁ ፡ መቅደስ ፡ ሥር፡ በሚገኘው፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ግሩማን ፡ የሆኑ ፡ መስቀሎችና፡ ንዋየ፡ ቅድሳት ፡ አሉ ። ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ይጸልይ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ይደገፍበት ፡ የነበረው ፡ መቋሚያው ፡ በዚሁ ፡ በቤተ ፡ ሚካኤል፡ መቅደስ፡ ይገኛል ። ቤተ ፡ ሚካኤል ፡ መቅደሱ ፡ ትልቅ ፡ ነው ። በውስጡም ፡ እስከ ፡ ጓዳዎቹ ፡ አራት ፡ ክፍሎች ፡ አሉበት ። በሌሎች ፡ መቅደሶች ፡ የሌሉ ፡ በጉበተኛ ፡ ቅርፅ ፡ የተበጁ ፡ የቅዱሳን ፡ ምስሎች፡ ይገኙበታል፡ የሕንፃውም ፡ ውስጡ ፡ ዓምዶችና ፡ ቅስቶች ፡ አሉ ።

ቤተ ፡ ጊዮርጊስ ፤ ከአንድ ፡ ድንጋይ ፡ ወጥ ፡ ሆነው ፡ ተጠርበው፡ ከታነፁት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ የአሠራር ፡ ሁኔታው ፡ በጣም ፡ የሚያምርና ፡ የመስቀል ፡ ቅርፅ ፡ ያለው ፡ ነው ። ከእናቱ ፡ ጀምሮ ፡ ወደታች ፡ በመውረድ ፡ የታነፀ ፡ መሆኑ ፡ ይገመታል ።



ከሁለቱ ፡ የሕንፃ ፡ ክፍሎች ፤ የቤተ ፡ አማኑኤልና ፡ የቤተ ፡ ማርያም ፡ ሕንፃዎች ፡ ፊንጠር ፡ ብሎ ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ የቤተ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ሕንፃ ፡ የሚገኘው ፡ በሁለት ፡ ወገኖቹ ፡ ወንዞች ፡ በሚገኙበት ፡ ሸንተረር ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ነው ። የሕንፃው ፡ ውስጡ ፡ ጣሪያውና ፡ ቅስት፡ያላቸው ፡ አራቱ ፡ ዓምዶች ፡ በተስተካከለ ፡ ኀብር ፡ የታነፁ ፡ ናቸው።ጠቅላላው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሕንፃም ፡ ዕፁብ ፡ ተብሎ ፡ የሚደነቅ ፡ አሠራር ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

በላስታ ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ካነፃቸው ፡ አስደናቂ ፡ መቅደሶች ፡ በዕድሜ ፡ የሚቀድሙ ፡ አሉ ። መቅደሶቹም ፡ እንደ ላሊበላ ፡ ሕንፃዎች ፡ ዓለቱ ፡ ድንጋይ ፡ ተጠርቦ ፡ የታነፁ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ በመሆናቸው ፡ ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ላነፃቸው ፡ ሕንፃዎች ፡ አያቶቻቸው ፡ ይሆናሉ፡» ብለውን፡ ሲሰናበቱን፡ ሸኝተናቸው ፡ ተመለስን።

በተሰጠን፡ ገለጣ፡ መሠረት፡ እንደገና ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ፡ እየተዘዋወርን፡ዐይተን ፤ ሌሊቱን ፡ ለማሳለፍ ፡ በማረፊያችን ፡ እንደተሰበሰብን ፤ በከተሜና ፡ በባላገር ፡ ኗሪዎች ፡ መካከል፡ ያለውን፡ አስተሳሰብ፡ ፀሐይ፡ አንስታ ፤ ትናንት ፡ ያነጋገርናቸው ፡ አባት ፡ ሽማግሌ ፤ የቀድሞና ፡ የዛሬ ፡ ዘመን ፡ የሰዎች ፡ እምነት ፡ በምን ፡ ላይ ፡ እንደተመሠረተ፡ከኛ፡ በበለጠ ፡ ርሳቸው ፡ አስተውለውታል ።

ቀደም ፡ ብለው ፡ የተፈጠሩትና ፡ አሁን ፡ የተፈጠርነው ፤ ለሰው፡ ልጅ ፡ ደስታ ፡ የሚሰጡ ፤ ዛሬ ፡ ያሉት ፤ ቀድሞ ፡ ባይኖሩም ፤ ቀደም ፡ የነበሩት ፡ ዛሬ ፡ የሉም ። በቀድሞውም ፡ ሆነ ፤ በዛሬው ፡ ያው ፡ ተደሳቹ ፡ በዘመኑ ፡ የነበረው ፡ ስለሆነ ፤ የቀድሞዎቹ ፡ የዛሬውን ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አላዩምና ፡ ደስታቸው ፡ የተወሰነ ፡ ነበር ። የዛሬዎቹ ፡ ምኞት ፡ የበለጠ ፡ ነውና ፡ ተደስተዋል ፡ ብሎ ፡ ለመገመት፡ ያስቸግራል።ደስታ፡ ማለት ፡ የመንፈስ ፡ ስለሆነ ፤ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ለማግኘት፡ ከቀድሞ፡ ሰዎችና ፡ ከዛሬ ፡ ማንኛዎቹ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ለማለት ፡ ያስቸግር ፡ ይሆናል ።

የመንፈስ ፡ ደስታና ፡ የመንፈስ ፡ ፀጥታ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ክብር ፡ ወይም ፡ ሀብት ፡ የሚገዛ ፡ አይደለም ። እንዲያውም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የመንፈስ ፡ ደስታ ፡ ካጣ ፡ የያዘውና ፡ የጨበጠው ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ፡ነው። የመንፈስ ፡ ደስታና ፡ ፀጥታ ፡ የሚጠፋው ፡ እንዴት ፡ ነው ? በምንስ ፡ ነው ? እስቲ ፡ መክብብ ፡ አንተ ፡ ንገረን ? አለችኝ ፡ ፀሐይ ።

ፀሐይ ፡ ጥያቄሽ ፡ ከባድ ፡ ነው ። የመንፈስ ፡ ደስታና ፡ ፀጥታ ፡ የሚገኘው ፡ ከማንም ፡ ሳይሆን ፤ «ሰላምን ፡ እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን፡ እሰጣችኋለሁ ፤ እኔ ፡ የምሰጣችሁ ፡ ዓለም ፡ እንደሚሰጠው፡ አይደለም፡ ልባችሁ ፡ አይታወክ ፤ አይፍራም ፡ » ካለው ፡ ይገኛል ። ይህን ፡ ለማግ ኘት ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ፡ እምነት ፡ በልቦና ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ። ያስፈል ጋል ። የሰው ፡ ልጅ ፡ ደስታን ፤ ፀጥታን ፡ ሰላምን ፡ ያራቀው ፡ በራሱ ፡ እየተመካ ፡ ነው ።

የዓለም ፡ ብርሃናት ፡ የሆኑት ፡ ሐዋርያት ፤ መንፈስ ፡ ከቀላከላ ቸው ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ በዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ቋንቋ ፡ እየተናገሩ ፤ ወንጌልን ፡ ያስተምሩትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ታምራት ፡ የሠሩት ። የሳይንስና ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ሥራ ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። የሰው ፡ ልጅ ፡ በሳይንስ ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ ያለው ፡ በዓይኑ ፡ ስለሚያይ ፡ በእጁ ፡ ስለሚጨብጥ ፡ ነው ። በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተና ፡ የሚመሠረት ፡ እምነት ፡ በዓ ይን ፡ በማይታይ ፡ በእጅ ፡ በማይዳሰስ ፡ ላይ ፡ ስለሆነ ፤ ዘወትር ፡ ጥር ጣሬን ፡ ይፈጥራል ። ጥርጣሬ ፡ ካለ ፤ ሰው ፡ የተመኘውን ፡ ወይም ፡ ያሰ በውን ፡ አያገኝም ።

ሳይሳሳ ፡ ከሚሰጥና ፡ ሰጥቶ፡ ከማያልቅበት፡ ከእውነተኛ፡ ምንጭ፡ የሚገኝ ፡ ስጦታ ፡ ክብርን፡ ያጐናጽፋል። እምነት፡ ያድናል። ከእምነት፡ ምንጭ ፡ ለመጠጣት ፤ ትዕግሥት ፡ ያስፈልጋል ። ኢዮብ፡ የሰይጣንን፡ ፈተና ፡ ድል ፡ ያደረገው ፡ በእምነት ፡ ሲሆን ፤ የእምነቱ፡ የመጨረሻ ፡ ተስፋ ፡ የሆነው ፡ የደረሰበትን ፡ ሁሉ ፡ በትዕግሥት፡ መቀበሉ ፡ ነው ።

በዘመናችን ፡ እንደኢዮብ ፡ የሚሆን ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ ይገ ኛል ፡ አልልም ። እንኳን ፡ የኢዮብን ፡ ያህል፡ መከራ፡ ወይም ፡ ፈተና፡ የደረሰበት ፤ የጠየቅሁት ፡ አልተፈጸመም፤ የተመኘሁት ፡ አልሆነም ፤ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ሠርቶ ፡ የሚሞተው፡ ስንት ፡ ነው ? ።

እምነት ፡ በማይታይና ፡ በማይዳሰስ ፡ ላይ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፤ ያልከው ፡ ትክክል ፡ ነው ። እምነትና ፡ ተስፋ ፡ ከሌሉ፡ ሰው ፡ መኖር ፡ አይችልም ። ለምሳሌ ፡ ሞት ፡ ተፈጥሮ ፡ ነው ። የሚመጣበት ፡ ቀን ፡ አይታወቅም። የሰው ልጅ ፡ ሞትን ፡ ረስቶ ፤ ብዙ፡ ዘመን፡ እኖራለሁ፡ የማለት ፡ እምነት ፡ ስላለው ፡ ይወጣል ፤ ይወርዳል፤ ለፊቱም ፡ ዘመን ፡ የሚሆነውን ፡ ያዘጋጃል ።



ጥርጣሬ ፡ ከእምነት ፡ ጉድለት ፡ የሚመጣ ፡ የደካማዎች ፡ አስተሳ ሰብ ፡ ነው ። ተጠራጣሪው ፡ ከወዴት ፡ መጣ ? ያመጣጡ ፡ ታሪኩስ ፡ እንዴት ፡ ነው ? ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፤ የፍጥረታትን፡ አመ ጣጥ ፡ በታሪክ ፡ ከማወቁ፡ በቀር ፤ የራሱን ፡ አመጣጥ፡ በዚያ ፡ በጉዞው፡ ላይ ፡ በነበረበት ፡ ወቅት ፡ አያውቅም። ለመምጣቱ ፡ ምክንያት፡ የሆኑ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። እነዚህም ፡ አባትና ፡ እናት ፡ ናቸው ። እነሱን ፡ አልወለዱኝም ፡ ብሎ ፡ የሚጠራጠር ፡ የለም ፡ ብላ ፡ ተናገረች፡ ፀሐይ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በላሊበላ ፡ የምናደርገውን ፡ ጉብኝት ፡ ጨርሰን ፤ በማለዳ ፡ ጉዞዎችንን ፡ ወደ ፡ ጐንደር፡ ከተማ ፡ ቀጥለን ፤ ፋሲል ፡ የኢ ትዮጵያ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ እንድትሆን ፡ በአሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከመሠረትዋት ፡ ጐንደር ፡ ከተማ ፡ ገባን ። የጉብኝታ ችን ፡ መጀመሪያ ፡ የፋሲል ፡ ግንብ ፡ የሚባለውን ፡ ትልቅ ፡ ግርማ ፡ ያለውን ፡ ባለአንድ ፡ ደርብ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አድርገን ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሕንፃ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ አዳራሽ ፡ ሥር ፡ ምድር ፡ ቤት ፤ ከደርቡ ፡ በላይ ፡ የጐንደርን ፡ ከተማና ፡ በአሻጋሪው ፡ ያለውን ፡ ለጥ ፡ ያለውን ፡ የደንቢያን ፡ ሜዳ ፡ እስከ ፡ ጣና ፡ ሐይቅ ፡ የሚያሳየውን ፡ ተመለከትን ።

የጻድቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ልጅ ፡ አፄ ፡ ኢያሱ ፡ ያሠሩትን ፡ የደብረ ብር ሃን ፡ ሥላሴን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተመለከትን ፤ ውስጡ፡ በሥዕሎች፡ ያጌጠ ፡ ነው ።

ከጐንደር ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አጥር ፡ ግቢ ፡ ውጪ ፡ በቀሐ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ በሚገኘው ፡ ረፃዳ ፡ መሬት ፡ አፄ ፡ ፋሲል ፡ የአሠ ሩት ፡ የመዋኛ ፡ ኩሬ ፡ ያለውን ፡ ባለሁለት ፡ ደርብ ፡ አነስተኛ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጐበኘን ።

በዚሁ ፡ የመዋኛ ፡ ኩሬ ፡ ባለው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አጠገብ ፡ ከወደ ፡ እናትዋ ፡ ክብ ፡ የሆነች፡ ትንሽ ፡ ግንብ፡ አለች። ይህች ፡ ግንብ፡ ዞቢል ፡ የተባለው ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ የአፄ ፡ ፋሲል ፡ ፈረስ ፡ መቃብር ፡ ናት ፡ የሚባለውንም ፡ ዐየን ።

ከእነዚህም ፡ ሌላ ፡ በአሠራሩ ፡ ሌሎችን ፡ የቤተ፡ መንግሥት ፡ ሕን ፃዎች ፡ የሚመስል ፡ ራስ ፡ ስሁል ፡ ሚካኤል ፡ ይኖሩበት ፡ የነበረ ፡ አነ ስተኛ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሕንፃ ፡ ዐይተናል ።

እነዚህን ፡ እጅግ ፡ አስደናቂ ፡ የሆኑ ፡ ሕንፃዎች ፡ በመዘዋወር፡ ስንመለከት ፡ ይሰማን፡ የነበረው፡ ደስታ፡ ይህ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለመናገር፡ ያዳግታል ። በጠቅላላው ፡ የመንፈስ ፡ ኵራት፡ ተሰማን ። የበጌምድር፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሰፊ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ በጐንደር ፡ ከተማ ፡ በቆየንባቸው ፡ ቀናት ፡ በአየሩ ፡ ተስማሚነት ፡ በተለይ ፡ የተሰማን ፡ ደስታ ፡ ከተማውን ፡ ለቀን ፡ ለመሄድ ፡ አልወደድንም ፡ ነበር ።

በጐንደር ፡ ከተማ ፡ የምናደርገውን ፡ ጉብኝት፡ ፈጽመን ፤ ወደ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ተጉዘን ፡ የተንጣለለውን ፡ የጣናን ፡ ባሕርና፡ የፋሲልን፡ ድልድይ ፤ የዓባይን ፡ ፏፏቴ ፡ ዐይተናል ። በጣና ፡ ባሕር፡ ውስጥ፡ ከሚገኙት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ደቅ ፡ እስጢፋኖስን፤ ናርጋ፡ ሥላሴን፡ ክብራን ፡ ገብርኤልን ፤ ዘጌን ፡ አየን ። በደቅ ፡ እስጢፋኖስ ፡ የነአፄ ፡ ፋሲል ፡ ዓፅም ፡ ያረፈበትን ፡ ተመለከትን። በደቅ፡ እስጢፋኖስ፡ገዳም፡ ሴት ፡ አይገባም ፡ በመባሉ ፡ የተሰማን ፡ ኀዘን፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሆኖ፡ ነበር። ሴት ፡ እንዳይገባ ፡ የተደረገበትን ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ ለማወቅ ፡ ላቀረብነው ፡ ጥያቄ ፤ ልባችንን ፡ የሚያረካ ፡ መልስ ፡ በሥፍራው፡ ካሉት ፡ አባቶች ፡ ልናገኝ ፡ አልቻልንም ።

እንዲያውም ፡ ጠለቅ ፡ ብለን ፡ ስንመረምር ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ያለ ፡ ዘር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በልደት ፡ የተገኘው ፡ ከሴት ፡ አይደለምን ? እንዴት ፡ ሴት ፡ ትከልከል ? እያለች ፡ ፀሐይ ፡ በመገረም ፡ ለምታደርገው ፡ ጥያቄ፡ አጥጋቢ፡ መልስ ፡ሰላጣች ፤ ይሆን፡ ድንጋጌ ፡ ያደረጉ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ የሰው ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ጊዜም፡ ትክክል ፡ አይደለምና ፡ ርሱ ፡ የቀደሳትንና ፡ ያከበራትን ፡ ሰዎች ፡ ለማዋረድ ፡ ቢሞክሩ ፡ አልደነቅበትም ፡ ብላ ፡ ቅሬታዋን ፡ በቁጭት ፡ በገለጠችበት ፡ ሰዓት ፤ ለኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ሴት ፡ ወደዚህ ፡ ቅዱስ ፡ ሥፍራ ፡ እንዳትገባ ፡ የተከለከለው ፡ ሴት፡ ሆና፡ በመፈጠሯ ፡ ሳይሆን፡ ገዳሙን ፡ በምትጐበኝበት ፡ ጊዜ ፡ ወንዶች፡ እርሷን፡ በማየት ፡ምኞት፡ እንዳያድርባቸውና ፡ እንዳይሰነካከሉ ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል፡ የተደረገ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርምና ፡ ኀዘን ፡ አይሰማሽ ፡ ብዬ ፡ አጽናናኋት ።

ባየነው ፡ ስንደሰት፤ በተሠሩት፡ ስንደነቅ፤ ያላየናቸውን፡ ለማየት፡ ጓጓን፤ ጉዞዋችንን፡ ወደ፡ አክሱም፡ ቀጥለን፤ አክሱም፡ እንደደረስን፡ጥንታዊቷን፡ የጽዮንን፡ ቤተ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሳለም፡ ብንሔድ ፤ በዚያም፡



ሴት ፡ ባለመግባትዋ ፡ ፀሐይ ፡ የበለጠ ፡ ኀዘን ፡ ስለተሰማት ፤ ከርስዋ ፡ ተለይተን ፡ ልንገባ፡ ባለመውደዳችን ፡ በሩቅ ፡ ተሳልመን ፡ ተመለስን ።

ታሪካዊ ፡ የሆኑትን ፡ ሐውልቶች ፡ የነገሥታቱን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶችና ፡ መቃብራቸውን ፡ ተዘዋውረን ፡ ከተመለከትን ፡ በኋላ ፡ ታሪኩን ፡ በዝርዝር ፡ ለማወቅ ፡ ሞከርን ።

የአክሱም ፡ ታሪክ ፡ በሁለት ፡ ትልልቅ ፡ ክፍሎች ፡ የተከፈለ ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ። ይኸውም ፡ ከክርስትና ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ጊዜና ፡ ከክርስትና ፡ በኋላ ፡ የነበረው ፡ ታሪክ ፡ ተለይቶ ፡ የሚታይባቸው ፡ ምልክቶች ፡ ይገኛሉ ።

የአክሱም ፡ ስም ፡ አመጣጥና፡ በአክሱማውያን ፡ አባቶች ፡ ታሪክ፡ በተለይ ፡ የአክሱምን ፡ ታሪክ ፡ በሚነግረው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ተተርኮ ፡ እንደሚገኝ ፡ ተነገረን ።

አክሱምን ፡ ጥንታውያኑ ፡ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ የአክሱም ፡ ነገሥታት ፡ የግዛታቸው ፡ መዲና ፡ (ዋና ፡ ከተማ ፡ ) አድርገዋት ፡ ይኖሩ ፡ እንደነበርና ፡ በአክሱም ፡ ከነገሡት ፡ (ከመጀመሪያዎቹ ፡ ) ቀደምት ፡ ነገሥታት ፡ አንድዋ ፡ ንግሥተ ፡ ሳባ፡ መሆንዋን፡ ዐውቀን ፤ ሌሎችም፡ ለዘመናቸው ፡ ሥልጣኔ ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ የደንጊያ ፡ ላይ ፡ ጽሑፎችን ፡ የተዉ ፤ እንደነኢዛና ፡ ( አብርሃ ፡ አጽብሐ ፡ ) ያሉ ፡ ነገሥታት ፡ ያሳለፉት ፡ ከተማ ፡ መሆንዋን ፡ ተረዳን ።

ከአክሱም ፡ ወጣ ፡ ብሎ ፡ የስመ ፡ ጥሩዎቹ፡ የአፄ፡ ካሌብና፡ የልጁ፡ የገብረ ፡ መስቀል ፡ መቃብር ፡ በሰሜን፡ በኩል፡ ይገኛል ። መቃብሮቹ፡ እንደ ፡ ዋሻ ፡ ሆነው ፡ በትልልቅ፡ጥርብ ፡ ድንጊያዎች ፡ ግሩም፡ በሆነ ፡ ጥበብ ፡ የተገጠሙ ፡ ናቸው ። አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ ድንጊያዎቹን ፡ አንሥተው ፡ ወደተፈለገው ፡ ሥፍራ ፡ የሚያዘዋውሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሣሪያዎች ፡ ናቸው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህን፡ ወጥ ፡ የሆኑ፡ ድንጊያዎችን ፡ አንቀሳቅሰው ፡ አስደናቂ ፡ በሆነ ፡ ጥበብ ፡ እንዴት ፡ እንደገጠምዋቸው ፡ ተደነቅን ።

ከዚህም ፡ ቀጥለን ፡ ስመ ፡ ጥሩውን ፡ የደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገዳምን ፡ ዐየን ። ይህ ፡ ገዳም ፡ በአድዋ ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ታላላቅ ፡ ተብለው፡

ከሚጠሩትና ፡ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ ከሆኑት ፡ ከገዳሞች ፡ አንዱ ፡ ነው ። የገዳሙ ፡ መሥራች ፡ አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ናቸው ።

አራት ፡ መቶ ፡ ዓመታት ፡ የሞላው ፡ ገዳም ፡ ከታሪኩ ፡ በአጭሩ ፡ የሚከተለውን ፡ ተረድተናል ።

ስሙ ፡ ዘሚካኤል ፡ ይባል ፡ የነበረው ፡ አቡነ፡ አረጋዊ ፣ ረድኡን፡ ማትያስን ፡ ይዞ ፣ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ አቅጣጫ ፡ ዛሬ ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ወደ ፡ ሚገኝበት ፡ ቀበሌ ፡ ሄደ ።

በዚህ ፡ ተራራ ፡ አጠገብ ፡ ከደረሱ ፡ በኋላ ፣ « ጥቂትም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ምስንጉ ፡ ወደ ፡ ምትባል ፡ ዓለት ፡ ድንጊያ ፡ ደረሰ ። በዚያም ፡ ቁሞ ፡ የተመሰገነችውን ፡ ዳሞ ፡ የተባለችውን ፡ ቦታ ፡ አያት ። በላይዋም ፡ ለመቀመጥ ፡ ሁኔታዋ ፡ አማረው ። ልቡናው ፡ በዚችው ፡ ቦታ ፡ ፍቅር ፡ ተነደፈ ።

ይችን ፡ ተራራ ፡ ዙሮ ፡ የሚወጣበትን ፡ ቢመለከትም ፡ መውጫ፡ የሚሆነው፡ አጣ። በርሷ ፡ ላይ ፡ ወጥቼ ፡ ለመኖር ፡ የምፈልጋት ፡ ቦታ ፡ ይችው ፡ ነበረች ፡ አለ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገደሉ ፡ ከፍ ፡ ወዳለና ፡ ረጅም ፡ ወደሆነ ፡ ሰቋራ ፡ ወደተባለው ፡ ተራራ ፡ ሄደ ። ትንሽ ፡ መውጫ ፡ መንገድ ፡ አግኝቶ ፡ ወደላዩ ፡ ወጥቶ ፡ ጸሎት ፡ ሲያደርግ ፡ ቆይቶ ፣ የቀኑ ፡ ጊዜ ፡ ከተዋገደ ፡ በኋላ ፡ አንዲት ፡ ኅብስት ፡ አንሥቶ ፡ ባርኮ ፡ በላት። ከዚህች ፡ ዳቦ ፡ ምንም ፡ አልተረፈውም ።

አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ዳቦዋን ፡ ምንም ፡ ሳያተርፍ፡ በመጨረሱ ፡ በልቡ፡ አዘነ ። በተራራው ፡ ላይ ፡ ለመኖር ፡ ክፍሉ ፡ አለመሆኑንና ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቦታውን ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔርነት ፡ ያልፈቀደው ፡ መሆኑን ፡ ዐወቀው ።

በማግሥቱ ፡ ከተራራው ፡ ወርዶ፣ ወደሌላው ፡ በዚያው ፡ ጐረቤት፡ ወደሆነ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ጸለየ ፣ ተራራው ፡ ለገዳማት ፡ መመሥረቻ ፡ ያልተመቸ ፡ ቦታ ፡ መሆኑን ፡ ተረዳ። ወደሌላ፡ ሦስተኛ፡ ተራራ፡ ሄደ ፣ ከጸሎቱ ፡ በኋላ ፡ ዳቦዋን ፡ ባርኮ ፡ ሲበላ ፡ ሳይተርፈው ፡ ቀረ ። በእነዚህ ፡ ሦስት ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ ቦታነታቸውን ፡ ከጐበኘ፡ በኋላ ፣ ወደፊተኛው ፡ ዳሞ ፡ ወደተባለው ፡ ልቡ ፡ ወደደነገጠበት፡ ተራራ ፡ ተመለሰ ። ከዚያም ፡ ዛሬ ፡ ወደዳሞ ፡ የመውጫ ፡ ቦታ ፡ ወደሆነበት ፡ እግረ ፡ ሀብል ፡ ወደተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ሄዶ ፡ ሦስት፡ መዓልትና፡ ሦስት፡ ሌሊት ፡ ጸለየ ።



ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ መጥቶ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስጉን ፡ አገልጋይ ፡ ሆይ ፣ ምንድን ፡ ነው ፡ የሚያስጨንቅህ ፣ ብሎ ፡ ጠየቀው። አቡነ ፡ አረጋዊም ፡ ወደዚህ ፡ ተራራ ፡ ወጥቼ ፡ ስለስሕተቴና ፡ ስለኃጢአቴ ፡ መጸለይ ፡ እፈልጋለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አምባው ፡ ራስ ፡ ለመውጣት ፡ መንገድ ፡ አጣሁ ፡ አለው ።

ከመላኩ ፡ ጋር ፡ ከተነጋገረም ፡ በኋላ ፡ ጸሎቱን ፡ ቀጥሎ ፣ መላኩ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ላይ ፡ የሚያወጣህ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ርዝመት ፡ ያለው ፡ ዘንዶ ፡ ታዞልሃል፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ሁለት ፡ ሱባኤ ፡ በጾምና ፡ በጸሎት ፡ ከቆየ ፡ በኋላ ፣ መላኩ ፡ በነገረው ፡ መሠረት ፡ አርዌው ፡ ዘንዶ ፡ መጣ ። ቅዱስ ፡ ሚካኤልም ፡ የታዘዘልህ ፡ ዘንዶ፡ ይህ፡ ነውና ፡ ቅረብ ፡ ብሎ ፡ እንዳችም ፡ ጉዳት ፡ እንዳያደርስበት ፡ ይጠብቀው ፡ ነበር ።

ዘንዶ ፡ ጅራቱን ፡ እስከ ፡ ገደሉ ፡ ግማሽ ፡ ድረስ ፡ ሰዶ ፡ በሰው ፡ አነጋገር ፡ ቃል ፣ አቡነ ፡ አረጋዊን ፡ በዚህ ፡ አምባ ፡ (ተራራ) ላይ ፡ ከሚበሩ ፡ ወፎች ፡ በቀር ፣ እንጀራ ፡ ጋግሮ ፡ ውሃ ፡ ቀድቶ ፡ እንኳን ፡ ለመኖር ፡ ራስህ ፡ የምትጠለልበት ፡ ዛፍ ፡ የለበትም ፡ በዚህች ፡ ቦታ ፡ ቀን ፡ ሐሩር ፣ ሌሊት ፡ ውርጭ ፣ ብቻ ፡ ነው ፡ አለው ።

አቡነ ፡ አረጋዊ ፡ ያለመወላወል ፡ የምፈልገውን ፡ እግዚአብሔር ፡ አይነሳኝም ። አንተ ፡ የታዘዝከውን ፡ አድርግ ፣ ጅራትህን ፡ ሰደህ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ አናት ፡ መሐል ፡ አውጣኝ ፡ አለው። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ዘንዶው፡ ጅራቱን ፡ ሰዶ ፡ በአንዳፍታ ፡ ስቦ ፡ ወንጭፎ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ አናት ፡ አወጣው። አቡነ፡ አረጋዊም ፡ ከአምባው ፡ አናት ፡ ላይ ፡ከወጣ ፡በኋላ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፣ ሃሌ ፡ ሉያ ፣ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፣ ዓለምን ፡ አሳልፎ ፡ የሚኖር ፣ እግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፡ ብሎ ፡ አመሰገነ ። ስለዚህ ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ በሌላ፡ የክብር ፡ ስሙ፡ «ሃሌ ፡ ሉያ» ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ። ይህ፡ ታሪክ ፡ የተወሰደው፡ በሰፊው ፡ ከተጻፈው ፡ ከገድሉ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ወደ ፡ ደብረ ፡ ዳሞ ፡ ገዳም ፡ ለመውጣት ፡ ዛሬም ፡ ቢሆን ፣ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የለም ። ተራራው ፡ ዙሪያውን ፡ በበሀ ፡ ድንጋይ ፡ የተከበበ ፡ ገድል ፡ ነው ። አቡነ ፡ አረጋዊን ፡ ዘንዶው ፡ አወጣቸው ፡ በሚለው ፡ መሠረት ፡ የገደሉ ፡ ቁመት ፡ አጠር ፡ በሚልበት ፡ ቦታ ፡ በዘንዶው ፡ ምሳሌ ፡ ወፍራምና ፡ ድርብ ፡ ሆኖ ፡ የተሰፋ ፡ የጠፍር ፡ ገመድ ፡ ስላለ ፡

ወደ ፡ ደብሩ ፡ ለመውጣት ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ገመድ ፡ ይዞ ፡ ገደሉን ፡ እየተረጋገጠ ፡ አሁንም ፡ ይወጣል ።

ይህ ፡ እንዴት ፡ ይሆናል ? የሚል ፡ ተጠራጣሪ ፡ በዘመናችን ፡ ይኖር ፡ ይሆናል።ዳሩ ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ይሳነዋል ። በእግዚአብሔር ፡ የሚታመን ፡ ሰው ፡ የሚሠራውና ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ሰውን፡ ከጥርጣሬ ፡ ካለማመን ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ያደርሰዋል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በበጐ ፡ ፈቃድና ፡ በእምነት ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ዘወትር ፡ ድልን ፡ ያጐናጽፋል ።የጥንት ፡ ሰዎች ፡ ብርታት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከአሰቡት ፡ ግብ ፡ የሚያደርሳቸው ፡ እምነታቸውም ፡ ነው ።

በዚህ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ጉብኝታችንን ፡ ካጠናቀቅን ፡ በኋላ ፡ ከቤታችን ፡ ከወጣን ፡ ወር ፡ ስለሆነ ፤ የቀሩትን ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ እንደምናያቸው ፡ ተስፋ ፡ አድርገን ፡ ወደቤታችን ፡ ተመለስን ።ቤተሰቦቻችንና ፡ የቅርብና ፡ የሩቅ ፡ ወዳጆቻችንም ፡ በናፍቆት ፡ ተቀበሉን ።

የቅርብና ፡ የሩቅ ፡ ወዳጆቻችንን ፡ ከአንድ ፡ ሳምንት፡ ያላነሰ፡ ባለማቋረጥ ፡ ተቀበልን ። ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፀሐይ ፤ እየተዘዋወርን ፡ ያየናቸው ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራዎችና ፡ በጠቅላላው ፡ በሀገራችን ፡ አየርና ፡ አቀማመጥ ፡ ሁሉ ፡ ልቤ ፡ ስለተነካ ፤ ትዝታው ፡ ከፊቴ ፡ አሁንም ፡ አለ፣ ቢሆንም ፡ የኛ ፡ ማየት ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይደለም ፡ ያየነውን ፡ ላላዩት ፡ የምናስተላልፍበት ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ አለብን። ይህን ፡ ካላደረግን ፡ ግዴታችንን ፡ አልፈጸምን ፡ ማለት፡ ነው። ከሀገራችን ፡ ውጭ ፡ ወደሌላው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ሄደው ፡ የጐበኙ ፤ የተማሩ ፤ በሌላም፡ ምክንያት ፡ የኖሩ ፤ የኋላ ፡ ኋላ ፡ ወደሀገራቸው ፡ ሲመለሱ ፡ ከዚያ ፡ ያገኙትን ፡ የመንፈስ ፡ ሀብት ፤ በሀገራቸው ፡ ለሚገኙ ፡ ወገኖቻችን ፡ ያላካፈሉ ፡ ብዙዎች ፡ አሉ ። እነርሱ ፡ ያዩትን ፡ ሌላው ፡ ቢያይ ፡ እንደማይወዱ ፡ ይነገርባቸዋል ። በአጭሩ ፡ እኛም ፡ በሀገራችን ፡ ውስጥ ፡ ተዘዋውረን ፡ ባየነው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ እንዳለንና ፡ ሀገራችንን ፡ በመጠኑ ፡ ለማወቅ ፡ ስለቻልን ፤ ለማያውቁት ፡ ማስረዳትና ፡ መንገር ፡ አለብን ። በሀገራችን ፡ ውስጥ ፡ ሕዝቡ ፡ ሀገሩንና ፡ ጥንታውያን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደምን ፡ ያሉ ፡ ጠቢባን ፡ እንደነበሩ ፡ እንዲያውቃቸው ፡ መገፋፋት ፡ አለብን ፡ ብላ ፡ አሳሰበችኝ ።

ሴቶች ፡ ሐሳብ ፡ ለማቅረብ ፡ ፍጥነት ፡ አላቸው ። ፀሐይ ፡ ይህን ፡ ሐሳብ ፡ ስታቀርብልኝ ፡ አመሰገንኳትና፡ ሐሳብዋን ፡ እንዳለ ፡ መቀበሉን ፡ ገልጬ ፤ ባደረግነው ፡ መዘዋወር ፡ ያገኘውን ፡ ደስታ ፤ ሌላውም ፡



እንደኛ ፡ ሄዶ ፡ ዐይቶ ፡ የደስታው ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ ግብዣ ፡ አዘጋጅተን ፤ በቅርብና ፡ በሩቅ ፡ የምናውቃቸውንና ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተደማጭነት ፡ ያላቸውን ፡ ሁሉ ፡ ጠርተን ፡ ሐሳባችንን ፡ ብንገልጽላቸው ፡ ብዬ ፡ መለስኩላት ።

ሐሳብህን ፡ በደስታ ፡ ተቀብየዋለሁ ፤ ግን ፡ ለመሰናዶ ፡ ዕቅድ ፡ ይኑረን ፡ አለችኝ ።

እነቡርክትን ፡ ጠርተን ፡ በዝግጅቱ ፡ ላይ ፡ ልንነጋገርበት ፡ መልክተኛ ፡ ላክን ። ምንም ፡ እንኳን ፡ እኛ ፡ ብንስማማም ፡ የነቡርክትን ፡ አስተያየት ፡ ለማወቅ ፡ ያህል ፡ ሐሳባችንን ፡ ገልጠን፡ የበኩላቸውን ፡ ጠየቅናቸው ። እንዳጋጣሚ ፤ ቡርክት፡ በቅድሚያ ፡ ተናጋሪ ፡ ሆና፡ በዘወትር ፡ አስተሳሰባችሁ ፡ እኮራባችኋለሁና ፡ በዝግጅቱ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ እንነጋገር ፡ ብላ ፡ በአጭር ፡ መልስ ፡ ስለሰጠች ፤ ጊዜውን ፡ ወሰን ።

በድካማችን ፡ ያፈራነው ፡ ሀብት ፡ ያሰብነውን፡ የሚያስፈጽመን፡ ከመሆኑም ፡ ይልቅ ፤ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ሀብት ፡ ካልተሠራበት ፤ ከሕይወት ፡ በኋላ ፡ የማያገለግል፡ መሆኑን ፡ ዘወትር፡ የምንነጋገርበት ፡ነው ። ፀሐይ፡ በታወቀው፡ የቤት ፡ ባልትናዋ፡ ዝግጅቱን ፡ ቀጠለች። ቡርክት፡ የሚያስፈልገውን ፡ ከከተማ ፡ እያቀረበች ፡ አሟላች። በግብዣው፡ላይ፡ የምናደርገውን ፡ ገለጣ ፡ ከክነፈ ፡ ርግብ ፡ ጋር ፡ አዘጋጀን ።

በቅድሚያ ፡ የኔ ፤ ቀጥሎ ፡ የክነፈ ፡ ርግብ ፡ በንባብ ፡ ተሰማ ። ከባልዋ ፡ ይልቅ ፡ ያስተማሪዋን ፡ በይሉኝታ፡ መረጠች ፡ አትበሉኝ፡እንጂ፡ ክነፈ ፡ ርግብ ፡ ያዘጋጀውን ፡ እመርጣለሁ። በመሠረተ ፡ ሐሳቡ ፡ ሁሉቱም ፡ አልተራራቁም ። ግን ፡ አቀራረቡና ፡ አገላለጡ ፡ ሰምና፡ ወርቅ፡ ሆኖ ፡ የቀረበው ፡ የክነፈ ፡ ርግብ ፡ ነው ። ስለሆነም ፡ መክብብ ፡ ባዘጋጀው ፡ የሚወሰድ ፡ አንዳንድ ፡ ሐሳብ ፡ ይኖራል። በቅድሚያ፡ የናንተ፡ ምርጫ ፡ እንዴት ፡ ነው ? በሁላችንም ፡ ሐሳብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ እማማ ፡ ተናግረዋለችና ፡ አባባ ፡ ካዘጋጀው ፡ የሚወረስ ፡ ሐሳብ ፡ካለ፡ አባባና ፡ ክነፈ ፡ ርግብ ፡ ያስተባብሩት ፡ አለች ፡ ቡርክት ።

ለግብዣው ፡ የሚያስፈልገው ፡ መሰናዶ ፡ ቀጠለ ። የግብዣው ፡ ቀን ፡ ከፋሲካው ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ነበር ። ቀኑ ፡ ደርሶ ፡ ከተጠራው ፡ ሰው ፡ አንድም ፡ ሳይቀር፡ በግብዣው ፡ ላይ፡ ተገኘ ። የተዘጋጀውን ፡ መግለጫ ፡ አሰማሁ ። ከኔ ፡ ቀጠል ፡ አድርጋ ፡

እንኳን፡ በመቶ ፡ በአምሳ፡ በሚቈጠር፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ተናግሬ ፡ አላውቅምና ፡ ብሳሳት ፡ ይቅርታ ፡ ይደረግልኝ ፡ አለችና ፡ ፀሐይ ፤ ማየትና ፡ መስማት ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ። መስማት ፡ በእርግጥ ፡ የሰሙትን ፡ለማየት ፡ ያህል ፡ ያጓጓል ። ማየት ፡ ግን ፡ ማንነትንና ፡ ማን ፡ ማን፡ እንደ፡ ሆነ ፡ ይነግራል ። ሰው ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፤ ከሰውም ፡ ለካ ፡ ሰው ፡ አለ ? የሚያሰኘው ፡ በሠሪውና ፡ በሚሠራው ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ በሆነው ፡ ሥራ ፡ ነው ። ከሰውም ፡ ሰው ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ሰዎች ፡ የሠሩትን ፡ ማየት ፡ ከሁሉም ፡ ቅድሚያ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።

እኛ ፡ ከማየታችን ፡ በፊት ፡ ከናንተ ፡ የተለየ ፡ አስተሳሰብ ፡ አልነበረንም ፡ ነበር ። ከማየታችን ፡ የተነሣ ፤ ያየነውን ፡ ለናንተ ፡ ሳናካፍል ፡ ብንቀር ፡ ሕሊናችን ፡ ይወቅሰናል። የምታዩት፡ እንደኛ ፡ ሰዎች፡ የሆኑ ፡ ወገኖቻችን ፡ በዘመናቸው ፡ የሠርዋቸውን ፡ እጅግ፡ አስደናቂና፡ ታሪካዊ ፡ ሥራዎች ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ በወገኖቻችን ፡ የተሠሩ ፡ ሥራዎች ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ መሣሪያ ፤ እንደሠርዋቸውና ፡ ሰዎቹም ፡ መንፈሰ ፡ ጠንካራ ፡ ሰዎች ፡ እንደነበሩ ፡ በአድናቆት ፡ የሚታወሱ ፡ ናቸው ። እነዚህንና ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉት ፡ በዓይን ፡ከማየት ፡ በቀር ፡ በማስረዳት ፤ አድናቆታቸውን ፡ በሰው ፡ ሕሊና ፡ ለመቅረፅ ፡ ያዳግታል ።

ወንድሜ ፡ መክብብ ፡ በጽሕፈት ፡ ካነበበላችሁ ፡ የተለየ ፡ ላስረዳችሁ ፡ ሳይሆን ፤ ስሜቱን ፡ ለመክፈል ፡ ያህል ፡ ልናገር ፡ ወደድሁ ። እኛ ፡ በማየታችን ፡ እናንተም ፡ እየሄዳችሁ ፡ እንድትጐበኙ ፡ ስናደፋፍር ፤ እናንተ ፡ ካያችሁ ፡ በኋላ ፤ ሌላውንም ፡ እንደዚሁ ፡ ስለምታደፋፍሩ ፤ ሁሉም ፡ የሀገሩን ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራዎች ፡ ለማየት ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ተጓዥ ፡ ይሆናል ።

የራስን ፡ ሀገር ፡ ታሪኳን ፤ ተራራዋን ፤ ሸንተረርዋን ፤ የአየር ፡ ጠባይዋን ፤ በምሥራቅ ፤ በምዕራብ፤ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ ከማን ፡ጋር፡ እንደምትዋሰን ፤ ወሰንዋን ፡ ይህንና ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ሁሉ ፡ ማወቅ ፡ አለብን ።

የራሳችንን ፡ ሀገር ፡ ጠለቅ ፡ ብለን ፡ ካወቅን ፡ በኋላ ፤ የሌላውን ፡ ሀገር ፡ ስናውቅ ፡ ሀገራችንና ፡ ሌላውን ፡ እያነጻጸርን ፤ በሀገራችን፡ ላይ፡ ያለንን፡የመውደድ፡ ስሜት ፡ የበለጠ፡ እናጠነክራለን፡ ብላ ፡ ተናገረች ።



አዳማጩ ፡ ሁሉ ፡ ደስታውን ፡ በጭብጨባ ፡ ገለጠ ። ከተጋባዥዎቹ ፡ ትልቅ ፡ አዛውንት ፡ ስሜት ፡ ቀሰቀስዋቸው ፤ ሀገራችን ፡ ጥንታዊ ፡ ሥልጣኔ ፡ ያላት ፡ ሀገር ፡ እንደሆነችና ፡ ለሥልጣኔዋ ፡ ምስክር፡ የሚሆኑ ፡ ጥንታዊ ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራዎች ፡ እንዳልዋት ፤ አንዳንድ ፡ ሊቃውንት ፡ እየተረኩ ፡ ሲናገሩ ፡ እሰማ ፡ ነበር ። ቀደም ፡ ብለን ፡ የሰማን ፡ እኛ ፡ ለማየት ፡ ዕድል ፡ ሳናገኝ ፤ ከኛ ፡ በኋላ ፡ ተፈጥራችሁ ፡በማየታችሁ ፡ ዕድለኞች ፡ ናችሁ ፤ ማወቁም ፡ ሆነ ፡ ደስታው ፡ ለራሳችሁ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ እኛም ፡ እንድናይ ፡ ያደረጋችሁልን ፡ ገለጣ፡ ከልባችን፡ አይጠፋም ።

በሐሳባችሁና ፡ በንግግራችሁ ፡ ተመስጬ ፤ ልናገር፡ የወደድሁት፡ ለናንተ ፡ ምስጋና ፡ ለማቅረብ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ አዳማጭዎችን ፡ አጥብቄ ፡ አደራ ፡ የምለው ፤ የሰማነውን ፡ በልቦናችን ፡ አሳድረን፤ ያዩትን፡ ዐይተንና ፡ ታሪኩን ፡ አጥንተን ፡ እኛም ፡ ላላዩት ፡ ተናግረን ፡ ታሪክ ፡ አስተላላፊ ፡ እንሁን ፡ ሲሉ ፡ አሳሰቡ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የግብዣው ፡ ፍጻሜ ፡ ሆኖ ፤ ከምግቡም ፡ ይልቅ ፤ መንፈሳችን ፡ በማናውቀው ፡ እጅግ ፡ በሚያጓጓው ፡ ታሪክ ፡ ስለረካ ፡ ደስታችን ፡ እጥፍ ፡ ሆንዋል ። እናንተ ፡ ባታዩ ፡ ማን ፡ ይህን፡ ይነግረን፡ ነበር ። ያዩት ፡ ሁሉ ፡ ላላዩት ፡ እንደዚሁ ፡ ያዩትንና ፡ ያወቁትን ፡ ቢያካፍሉ ፡ ኖሮ ፡ ሁሉም ፡ እኩል ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ ይሰለፍ ፡ ነበር ፡ እንጂ፤ አንዱ ፡ ወደፊት ፡ እንራመድ ፡ ሲል ፡ ሌላው ፡ ባለንበት ፡ እንርገጥ ፡ አይልም ፡ ነበር ።

ይህች ፡ ዓለም ፡ የሩጫ ፡ ዓለም ፡ ናት ። ሰው ፡ እየተዘዋወረ ፡ ካላየ፡ በዓለም ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ውስጥ ፡ ለመኖሩ ፡ ምልክት ፡ የለውም ፡ እያሉ ፡ ተጋባዥዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ የቤታቸው ፡ ሄዱ ።

እንግዶቻችንን ፡ ከሸኘን ፡ በኋላ ፡ ከቤተ ፡ ዘመዱ ፡ ጋር ፡ ረጋ ፡ ብለን ፡ ስንነጋገር ፡ አድራጐታችን ፡ በቤተ ፡ ዘመዱ ፡ የተደገፈ ፡ ሆኖ ፤ ከሁሉም ፡ ምስጋና ፡ ተቀበልን ። በተለይ ፡ ክንፈ ፡ ርግብ ፡ በአስተማሪነት ፡ ምክንያት ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ የተገናኘሁባት ፡ ቀን ፡ የተባረከች ፡ ናት ። በገንዘቡ ፡ ራሱን ፡ አስደስቶ ፤ ሌላውንም ፡ ለማስደሰት ፡ የሚጥር ፤ እስካሁን ፡ ባለው ፡ ዕድሜዬ ፡ ለመጀመሪያ፡ እናንተን፡ ስለአየሁ፡ ደስታዬ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ልል ፡ አልችልም ፡ በማለት ፡ አድናቆቱን ፡ ገለጸልን ።

# ዕ ን ወ ቅ ፡

እንመርምር ፡ ዕንወቅ ፡ ያለፈውን ፡ ሥራ ፤
ዝናና ፡ ጥቅም ፡ አለው ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራ ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ልፋቱ ፡ ድካሙ ፡ ጥረቱ ፤
ሥራን ፡ መልካም ፡ ሠርቶ ፡ ታሪክ ፡ ማቆየቱ ።

ታሪክ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ለታሪክ ፡ ያልባረ ፤
ምንም ፡ ሥራ ፡ አልተወ ፡ መካን ፡ ሆኖ ፡ ቀረ ።
ተወልዶ ፡ ነበረ ፡ ሞተ ፡ ተቀበረ ።

ተብሎ ፡ መታማት ፡ ስለሆነ ፡ ትርፉ ፤
ለመማር ፡ ለማወቅ ፡ ሰዎች ፡ አትስነፉ ።

ለማወቅ ፡ ታሪክን ፡ የማይመራመር ፤
ለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ የለውም ፡ ምስክር ።

ምን ፡ ሠርቶልን ፡ ሄደ ፡ ያለፈው ፡ ትውልድ ፤
ብሎ ፡ ለመተቸት ፡ በሐቁ ፡ መንገድ ፤
ሐቀኛ ፡ ፍላጐት ፡ ይኑረን ፡ ፈቃድ ።

የሰው ፡ አስተሳሰብ ፡ አጭር ፡ ነው ፡ ሩቅ ፤
ንቆ ፡ ያለፈውን ፡ በራስ ፡ መራቀቅ ።

ሌላውም ፤ ሌላውም ፤ ይህን ፡ ይከተላል ፤
ተረስቶ ፡ ያለፈው ፡ የራሱን ፡ ያገናል ።

ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ሁሉም ፡ ያልፋል ፡ በተራው ፤
ተወው ፡ ያለፈውን ፡ ሆንዋል ፡ እንዳሻው ።

እያሉ ፡ ከማማት ፡ ሰውን ፡ ከማብጠልጠል ፤
መከበር ፡ የሚወድ ፡ ማክበር ፡ ይገባዋል ።
ሠርቶ ፡ ያለፈውን ፡ ታሪክ ፡ ያነሣዋል ።

ዓለም ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ የሚሯሯጥ ፡ ብዙ ፤
ድካሙ ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ልፋቱ ፡ መዘዙ ፤
ከቶ ፡ እነማን ፡ አሉ ፡ በዚህ ፡ ያልተጓዙ ! ! !

ታሪክና ፡ እውነት ፡ ባይቀበሩም ፤
እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ አላቸው ፡ ሕመም ።

እውነትና ፡ ታሪክ ፡ ጠፍተውም ፡ አይጠፉ ፤
ስታችሁ ፡ መንገዱን ፡ በከንቱ ፡ እንዳትለፉ ።

እውነትና ፡ ታሪክ ፡ ቁመው ፡ በጉባኤ ፤
በድል ፡ አድራጊነት ፡ አገኙ ፡ ትንሣኤ ።



ክፍል ፡ ፲፪ ፡

# ወደ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ጉብኝት ፡

ከነበረን ፡ ሐሳብ ፡ አንዱን ፡ ፈጽመን ፡ የሚቀጥለው ፡ ለአራት ፡ ወራት ፡ ያህል ፡ ያቆየናል ።

ብዙ ፡ ቤተሰብ ፡ የሚተዳደርበትን ፡ የደረጀ ፡ ቤት ፡ ለአራት ፡ ወራት ፡ መለየት ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። ጉዞዎችን ፡ በየብስ ፤ በባሕርና ፡ በአየር ፡ ስለሆነ ፤ ማን ፡ ያውቃል ፡ አደጋ ፡ ቢደርስ፤ የንብረት፡ ጥቅሙ፡ በሕይወት ፡ ዘመን ፡ ተጠቅሞ ፡ መጥቀሚያ ፤ ከሕይወት ፡ በኋላ ፡ ከአ ብራክ ፡ ለተከፈሉ ፡ ልጆችና ፡ ለአገለገሉ ፡ ትቶ ፡ መሄድ ፡ ነው ።

ቀጠሮ ፡ አያስፈልግም ፤ ማን ፡ ያውቃል ፡ እንደ ፡ ወጣን፡ ብንቀር፡ በውጭም ፡ ሆነ ፡ በውስጥ ፡ ያለንን ፡ ንብረታችንን ፡ በኑዛዜ ፡ ማካፈል ፡ አለብን ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ሰው ፡ ለሕይወቱ ፡ ዋስትና ፡ የለውም ፤ ኑሮው ፡ ሁሉ ፡ በተስፋ ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ። አስተሳሰብሽ ፡ ልቤን ፡ ነካው ። የሰው ፡ ምኞት ፡ ከመኖር ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ሆኖ ፡ በረኸርሙ ፡ ያስባል። በእጁ፡ የጨበጠውን ፡ ሳያስቀምጥ ፡ ይቀራል ። ማን ፡ ያውቃል ፡ አደጋ ፡ ቢደ ርስ ፡ ባልሽ ፡ ጊዜ ፡ ዕንባዬ ፡ ተናንቆኝ ፡ ካንቺ ፡ በፊት ፡ እንዲጠራኝ ፡ ተመኘሁ ።

ንብረታችንን ፡ ለልጆቻችን ፡ የምናካፍላቸው ፡ እንደምን ፡ አድር ገን ፡ እንደሆነ ፡ አብራሪልኝ ፡ አልኳት ።

ሰው ፡ ምን ፡ ቢዋደድ ፡ ካለ ፡ ድረስ ፡ አብሮ ፡ ይኖራል ፤ አንድ፡ ቀን ፡ አንዱ ፡ ቀድሞ ፡ የሚለይበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። በልደት ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ በተራ ፡ እንደመጣ ፤ በሞትም ፡ በተራው ፡ ይሄዳል ።

ወደተነሣንበት ፡ ስንመለስ ፡ የንብረታችንን ፡ልኩንና ፡ ዓይነቱን፡ ዘርዝረን ፡ ልጆቻችን ፡ በዕጣ ፡ ይካፈሉ ፡ እንጂ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ መደ ልደል ፡ የለብንም ።

ከማይንቀሳቀሰው ፡ ንብረታችን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም፤ መካከለኛ፡ ጥቅም ፤ አነስተኛ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጥ ፡ አለ ። በዕጣ ፡ ከተካፈሉ ፡ በዕድ ላቸው ፡ እንጂ ፡ በኛ ፡ አያዝኑም ። የንብረቱን ፡ ዝርዝር ፡ ጽፈን ፡ በፍ

ርድ ፡ ቤት ፡ ካስመዘገብን ፡ በኋላ ፡ አንዱን ፡ ለአቶ ፡ አንተነህ ፡ ሰው ፣ ሁለተኛውን ፡ ለአቶ ፡ ሰው ፡ በቃኝ ፣ ሦስተኛውን ፡ ለመምህር ፡ ሁሉንም ፡ አየነው ፡ እንሰጣለን ፡ አለችኝ ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ንብረታችንን ፡ በዝርዝር ፡ ጽፌን ፣ በፍርድ ፡ ቤት ፡ አስመዘገብን ። ይህ ፡ በዚህ ፡ እንዳለቀ ፣ ቤታችንን ፡ የሚያስተዳድርና ፡ የሚጠብቅ ፡ ማንን ፡ እናድርግ ፡ ብለን ፡ ተነጋገርን ። ጀግና ፡ ብዙ፡ ዘመን ፡ ከኛ ፡ ጋር ፡ የኖረ ፣ ባሳለፈው ፡ ዘመን ፣ ለትዝብት ፡ ያህል፡ ይህን ፡ አደረገ ፡ የማንለው ፣ ለሀብት ፡ የማይጓጓ ፣ ራሱን ፡ በሚመለከት ፡ ጥቅም ፡ የማይታለል ፡ ሰው ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ዓለም፡ ትልቁ፡ ሀብት፡ ጤንነት ፡ ነው ። ብዙ ፡ ከመፈለግ ፡ የተነሣ ፡ የማይገባ ፡ ሥራ፡ ሠርቶ፡ በራስ ፡ ሕሊና ፡ እየተወቀሱ ፡ እንቅልፍ ፡ ከማጣት ፣ በፀጥታ ፡ በነፃ ፣ ከመኖር ፡ የተሻለ ፡ የለም ፡ የሚል ፡ ነው ።

በተጨማሪ ፡ እነቡርክት ፡ በየሳምንቱ ፡ እየመጡ ፡ ይመለከታሉ። ጠቅላላውን ፡ ኃላፊነት ፡ ለርሱ ፡ እንስጥ ። መቼም ፡ በንብረታችንም ፡ ድልድል ፡ ባለመብት ፡ ሆንዋል ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

ቅዳሜንና ፡ እሑድን ፡ ደገፍ ፡ አድርገን፡ እነቡርክትን ፡ ጠራን ። ስለጉዟችን ፡ ውይይቱን ፡ ስናደርግ ፣ ገንዘብ ፡ በርከት ፡ አድርገን፡ እንድንይዝ ፣ ጉብኝታችንን ፡ ከምሥራቅ፡ አፍሪካ ፡ እንድንጀምር፡ ቡርክት ፡ ያቀረበችውን ፡ ሐሳብ ፡ ተቀበልን ።

ከሀገራችን ፡ ምድር ፡ ወጥተን ፡ ባለማወቃችን ፡ ቀኑ ፡ ሲቃረብ ፡ ባባን ። ማን፡ ያውቃል፡ አደጋ፡ ቢደርስብን ፡ ብለን፡ ያደረግነው ፡ ኑዛዜ፡ ከፊታችን ፡ ድቅን ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፣ በርግጥ ፡ እንደወጣን ፡ የምንቀር ፡ እየመሰለን ፡ ስለተሸበርን ፡ በዓይናችን ፡ እንቅልፍ ፡ ሳይኳል ፡ ነጋ ። በማለዳ፡ ተነሥተን ፡ ጉዞ ፡ ልንጀምር ፡ ስንዘጋጅ ፣ ልጆቻችን ፡ አልቅሰው፡ አስለቀሱን ። ሆኖም ፡ የመጀመሪያ ፡ ጉዟችን ፡ የተቃና ፡ ሆኖ ፡ ኬንያ ፡ ናይሮቢ ፡ ከተማ ፡ ደረስን ። ከልዩ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ ከመጡ ፡ ጎብኝዎች፡ ጋር ፡ ጉብኝታችንን ፡ ቀጠልን ። በአንድ ፡ አቶቡስ ፡ የምንጓዘው ፣ በመልክ ፣ በአለባበስ ፣ በቋንቋ ፡ የተለያየን ፡ ነበርንና፡ ራሳችንና፡ ሀገራችንን ፡ አስተዋወቅን ።

በከተማው ፡ ባሉት ፡ ሱቆች ፡ ንግዱ ፡ የሚካሄደው ፡ በልዩ ፡ ልዩ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ነው ። በለንደን ፡ በኦክስፎርድ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ትምህርቱን ፡ ያጠናቀቀ ፣ አንድ ፡ ወጣት ፡ መጥቶ ፡ ሰላምታ ፡ ከሰጠን፡



በኋላ ፣ ለንደን ፡ በምማርበት ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጓደኞች ፡ ስለነበሩኝ ፣ ደምግባታችሁ ፡ እነዚያን ፡ ስለመሰለኝ ፡ ልተዋወቃችሁ ፡ መጣሁ ፡ ሲል ፡ ሐሳቡን ፡ በግልጥ ፡ ነገረን ። እኛም ፡ ትክክለኛ ፡ መሆኑን ፡ ከገለጥንለት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሀገሬ ፡ የመጣችሁ ፡ እንግዶች ፡ ስለሆናችሁ ፡ መጋበዝ ፡ አለብኝ ፣ ብሎ ፡ ፍላጎታችንን ፡ ጠየቀ ።

ወደኬንያ ፡ ለምን ፡ እንደመጣን ፡ ላደረገልን ፡ ጥያቄ ፣ በኬንያ ፡ ብቻ ፡ ሳንወሰን ፣ ብዙ ፡ ሀገሮች ፡ እንደምንጐበኝና ፣ መነሻ ፡ ኬንያን፡ ማድረጋችንን ፡ ነገርነው ። የት ፡ እንደተማርን ፣ በምን ፡ ትምህርት ፡ እንደተመረቅን ፡ ማወቅ ፡ ፈለገ ። በማንኛውም ፡ ሞያ ፡ ሳንመረቅ ፡ ትምህርታችንን ፡ እንዳቋረጥን ፣ ሥራችን ፡ ግብርና ፡ እንደሆነ ፡ ገለጽንለት ።

በዚህ ፡ ሞያ ፡ ተመርቄያለሁ ፡ እያለ ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ከሚያደርግ ፡ ይልቅ ፣ መካከለኛውን ፡ ደረጃ ፡ የያዙ ፡ ናቸው ፡ ከፍተኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ ያላቸው ። አሁን ፡ በምታዩት ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ትማራላችሁ። ሥራችሁን ፡ ለማሻሻል ፡ የሚያስችል ፡ ዕውቀት ፡ ትገቢያላችሁ ። ሥራችሁ ፡ ግብርና ፡ ሲሆን ፣ በብዙ ፡ ሀገሮች ፡ የግብርና ፡ ሥራ ፡ የሚካሄደው ፡ በኅብረት ፡ ነው ። በኅብረት ፡ ሥራቸውን፡ የሚያካሂዱ ፡ ከምን፡ ላይ ፡ እንደደረሱ ፡ ታያላችሁ ። ከአዕምሮ ፡ የማይጠፋ ፡ ትምህርት ፡ ገብይታችሁ ፡ ወደሀገራችሁ ፡ ስትመለሱ ፣ ራሳችሁንና፡ ኅብረተሰቡን፡ ትጠቅማላችሁ ፡ አለን ።

የሚያበረታታ ፡ መልካም ፡ ቃል ፡ ስለነገረን ፡ አመሰገነው ፣ እየተዘዋወርን ፡ ስናይ ፡ ከተማው ፡ የደስ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ልንረዳ፡ ቻልን ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከተማዋን ፡ የሞልዋትና ፡ ቁልፍ ፡ በሆኑ ፡ የንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ በብዛት ፡ የሚታዩት ፡ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ መሆናቸውን ፡ ዐወቅን ። ስለዚህም፡ ምክንያቱን፡ ብትገልጥልን ፡ እንወዳለን፡ አልነው ።

ኧረ ፡ ገና ፡ የባሰ ፡ ታያላችሁ ። እንደምታውቁት ፡ አገሪቱ ፡ ለረዥም ፡ ዘመናት ፡ የነጮች ፡ የቅኝ ፡ ሀገር ፡ ሆና ፡ የኖረች ፡ ሀገር ፡ ናት። ተወላጆቹ ፡ ሀገራቸውን ፡ ከቅኝ ፡ ገዥዎች፡ እጅ ፡ አላቀው ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ ባደረጉት ፡ ተጋድሎ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሷል ። በነዚያ ፡ ደም ፡ ነፃነት ፡ ተመሠረተ ። በብዛት ፡ የምታይዋቸው ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ አያሌ ፡ ዘመናት ፡ የኖሩ ፡ ናቸው ።

እነዚህን ፡ እያስወጡ ፤ የሀገሪቱን ፡ ተወላጆች ፡ በፍጥነት ፡ ለመተካት ፡ ይቻል ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የፖለቲካን ፡ መንፈስ ፡ መከተል ፡ ስለሚያስፈልግ ፡ ቀስ፡ በቀስ ፡ መለወጡ ፡ ይቀጥላል ። በቅኝ ፡ ገዥዎች፡ በምትተዳደርበት ፡ በረዥሙ ፡ ዘመን ፤ የሀገሪቱ ፡ ተወላጆች ፡ አልተማሩም ። ሀገሪቱን ፡ ለቀው ፡ በውጭ ፡ የተማሩት ፤ ሀገሪቱን ፡ ነፃ ፡ ለማውጣት ፡ በቀሰቀሱት ፡ ንቅናቄ ፡ እየታሠሩ ፡ ሲሞቱ ፤ ያልሞቱት ፡ የትግላቸውን ፡ ፍሬ ፡ ዐይተው ፡ ዛሬ ፡ ሀገሪቱን ፡ ይመራሉ ።

የሀገሪቱ ፡ ተወላጆች ፡ በሀገር ፡ ውስጥና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገሮች ፡ በመማር ፡ ላይ ፡ ናቸው ። በትምህርት ፡ ዓለም ፡ ያሉት ፡ ትምህርታቸውን ፡ ሲያጠናቅቁ ፤ እንደሚተኩ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

በከፍተኛ ፡ ደመወዝ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰው ፡ ይሠራው ፡ የነበረውን ፡ የሕግ ፡ አማካሪነት ፡ ሥራ ፡ ተረክቤ ፡ በመሥራት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፤ ለርሱ ፡ ይከፈል ፡ የነበረው ፡ ደመወዝ ፡ አይከፈለኝ ፡ እንጂ ፤ ሥራው ፡ አላሸነፈኝም ።

የሀገሪቱ ፡ ተወላጆች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ሲሠለጥኑ ፤ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ በያዟቸው ፡ ሥፍራዎች ፡ ይተካሉ ። የሚተካ ፡ ሳይኖር ፤ ጥርግ ፡ አድርጎ ፡ ማስወጣት ፡ ጉዳት ፡ ያስከትላል ፤ በማለት ፡ ላገሩ ፡ ከፍተኛ፡ ፍቅር ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ በሁኔታው ፡ በማስረዳት ፡ ገለጠልን ።

ንግግሩንም ፡ በመቀጠል ፡ ይህን ፡ የነፃነት ፡ ደስታ ፡ ሳያዩ ፡ ነፃነትን ፡ እንደተጠሙ ፡ የሞቱትን ፡ በማስታወስ ፡ አሁን ፡ ያለው ፡ ትውልድ ፡ በሥራ ፡ ተባብረዋል ። ቅኝ ፡ ገዥዎች ፡ ከጥረታቸው ፡ አንዱ ፡ የሀገሩን ፡ ተወላጅ ፡ ማለያየት ፡ ነው ። በቅኝ ፡ ገዥዎች ፡ የነበረው ፡ የግፍ ፡ አገዛዝ ፡ ተረስቶ ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ ሁከት ፡ መፈጠሩ ፡ አልቀረም ። ለሀገሪቱ ፡ እድገት ፡ ትልቅ ፡ እንቅፋት ፡ ሆኗል ። «የገበያ ፡ ግርግር ፡ ለቀጣፊ ፡ ይመቻል ፡ » በቅኝ ፡ ገዥነት ፡ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ የኖሩት፡ ሥራቸው ፡ ሳይነቀል ፡ እያቆጠቆጠ ፡ ይቆያል ። ከሥሩ ፡ ተነቅሎ ፡ እስኪጠፋ ፡ ኃይላችን ፡ ተባብሮ ፡ እንዳይሠራ ፡ እያዳከሙ ፡ ያለያዩናል።

ለንደን ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ በኖርኩበት ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ አንብቤያለሁ። አፍሪካዊ፡ እንደመሆኔ፡ አፍሪካን ፡ እወዳለሁ ፤ አፍሪካን ፡ እንደመውደዴ ፤ ስለአፍሪካ ፡ የተጻፈውን ፡ ማንበብ ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር ። ከአፍሪካ ፡ ሀገር፡ በነፃነት ፡ ታፍራ፡ የኖረች፡



ትልቅ ፡ ታሪክ ፡ ያላት ፡ አገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ መሆንዋን ፡ በታሪክ ፡ አጥንቻለሁ ። የዚህች ፡ ሀገር ፡ በነፃነት ፡ መኖር ፡ ነፃነት ፡ ላጡ ፡ አፍሪካውያን ፡ ኵራትና ፡ መመኪያ ፡ ሆናለች ።

ጥንታዊ ፡ ታሪክ ፡ ያላትን ፡ ይህችን ፡ ውድ ፡ ሀገር ፤ ነፃነትዋን ፡ አጥፍታ ፤ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ለማድረግ ፡ ኢጣልያ ፡ በወረረቻት ፡ ጊዜ ፡ በአድዋ ፡ ላይ ፡ አውሮፓዊ፡ ጠላትን፡ ድል ፡ አድርጋ ፤ የሀገርዋን ፡ ነፃነት ፡ ማስከበርዋ ፤ በነበራት ፡ ታሪክ ፡ ላይ ፡ ታሪክ ፡ ጨምራ ፡ ታፍራና ፡ ተፈርታ፡ የኖረች ፤ የጀግኖች ፡ አፍሪካዊት ፡ ሀገር ፡ መሆኗን ፡ ታሪክ ፡ መስክሮላታል ።

ቅኝ ፡ ገዥዎች ፡ አፍሪካውያንን ፡ በባርነት ፡ አገዛዝ ፡ ረግጠው ፤ በሀገሪቱ ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ሲጠቀሙ ፤ የኢትዮጵያ ፡ በነፃነት ፡ መኖር ፡ ለሌሎች ፡ የነፃነት ፡ ንቅናቄ ፡ ምሳሌ ፡ ሆናለች ። በቀይ ፡ ባሕር ፡ በኩል ፡ ጐረቤት ፡ የሆነች ፡ ኢጣልያ ፡ ብትወራት ፡ ነፃነት ፡ ፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ አፍሪካውያን ፡ ተስፋ ፡ ይቆርጣሉ ፡ ተብሎ ፡ የተመከረው ፡ በብዙዎች ፡ ነበር ።

ኢትዮጵያውያን ፡ ደማቸውን ፡ አፍሰው ፤ የተቀዳጁት ፡ የድል ፡ አክሊል ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለአፍሪካውያን ፡ ኵራትን ፡ ሰጠ ። ቅስሙ ፡ ተሰብሮ ፡ በውርደት ፡ ድል ፡ የሆነው ፡ ጠላት፡ ቂሙን፡ ሳይረሳ ፡ እንደገና ፡ ከአርባ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጀግኖች ፡ በመርዝና ፡ በቦንብ ፡ አጥቅቶ ፡ ወረረ ። የሀገራቸውን ፡ ነፃነት፡ እስከ፡ መጨረሻው ፡ ላለማስደፈር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጀግኖች ፤ በዓለም ፡ ፊት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ጠላት ፡ እንዳልገዛት ፡ አድርገው ፡ ተከላክለዋል ።

ኢትዮጵያ ፡ የዓለም ፡ ማኅበር፡ አባል ፡ የሆነችው ፡ ከሁለተኛው፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ በፊት ፡ ነበር ። የኢጣልያ ፡ ፋሽስት ፡ ባልተፈቀደ ፡ መሣሪያ ፡ ያደረገችውን ፡ የግፍ ፡ ወረራ ፡ ዠኔቭ ፡ ለዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ ሲያቀርቡ ፤ አርበኞቿ ፡ በዱር ፡ በገደል፡ ሆነው ፡ መከላከላቸውን ፡ አላቋረጡም፡ ነበር ። ያልተቋረጠው፡ ትግል ፡ ድልን ፡ አጐናጸፈ ። የኢጣልያ ፡ ፋሽስት ፡ ጦር ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ጦር ፡ አርበኞች ፡ እጅ ፡ ወደቀ ። ዓለም ፡ እንደመቀራረቡ ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ጣልቃ ፡ እየገባ ፡ የውስጥ ፡ አንድነቱን ፡ ያናጋል ።

ከፋፍለህ ፡ ግዛ፡ የሚለው ፡ በብዙ ፡ ሀገሮች ፡ እየተሰራጨ ፡ ሄድዋል ። የረዥም ፡ ዘመን ፡ የነፃነት ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ይህን ፡

በመሰለ ፡ አይደለልም ። በዓለም ፡ ያለው ፡ ችግር ፡ ተመሳሳይ ፡ ስለ ሆነ ፤ የናንተ ፡ ሐሳብ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ይሆን ?

የሰው ፡ ዕውቀቱም ፡ ሆነ ፡ ኃይሉ ፡ የሚለካው ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ ነው ። የዚያን ፡ ዘመን ፡ ጀግንነት ፡ ካሁኑ ፡ ጋር፡ ሲመዛዘን ፤ የተለያየ፡ ጠባይ ፡ ይኖረዋል ። የቀድሞ ፡ ጀግኖች ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ገጥመው ፡ በጀግንነታቸው ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ ይመታሉ ፤ ጀግንነት፡ በማንኛውም፡ ሥፍራ ፡ ተፈላጊ ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ የዛሬው ፡ ጀግንነት ፡ ከጥበብ፡ ጋር፡ የተያያዘ ፡ ነው ።

የጥንት ፡ ሰዎች ፡ ውረድ ፡ እንውረድ ፡ ይባባሉና ፤ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይጋጠማሉ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በነበረው ፡ የጦር፡ ብልሀት፡ (ታክቲክ ፡) በጋሻና ፡ በዘንግ ፡ እየመከቱ ፡ ጠላታቸውን ፡ ድል ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ ስንመረምር ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በተድላ ፡ ገነት ፡ ያለ ፡ ድካም ፡ እንዲኖር ፡ ነበር ፡ የተፈጠረው ። ያልተፈቀደለትን ፡ በመሥራቱ ፡ ተፈረደበት ። ከነፍስ ፡ ሞት ፡ እንዲድን ፡ ኃጢአቱን ፡ የሚሸከም ፡ አገኘ ። አሁንስ ፡ በደሉን ፡ የሚሸከም ፡ ያገኛል ? ዓለምን ፡ እስቲ ፡ እንያት ። ደም ፡ ሳይፈስ ፡ ይውላል ? የዓመፅ ፡ ተግባር ፡ እየበዛ፡ ዓለም ፡ ደኅና ፡ ውላ ፡ ከምታድር ፤ የምትታመምበት ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ነው ። በአንዱ ፡ ሀገር ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ወደሌላው ፡ ይተላለፋል ። በሽታዎች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መድኃኒት ፡ ከምድር ፡ ገጽ፡ ሲጠፉ ፤ ከሰው፡ አዕምሮ ፡ እየተፈጠሩ ፤ በዓለም ፡ ለሚኖሩ ፡ ሕዝቦች ፡ ጥፋት ፡ ጠንቅ ፡ ለሚሆኑት ፡ መድኃኒት ፡ አልተገኘም ።

ሀገራችን ፡ የረዥም ፡ ዘመን ፡ የነፃነት፡ ታሪክ ፡ አላት ። በረዥሙ፡ የነፃነት ፡ ዘመን ፡ የተላለፉት ፡ በዕለት ፡ ደስታ ፡ ሳይደለሉ ፤ ሀገራቸውን ፡ ጠብቀው ፡ ለትውልድ ፡ አቆይተዋል ።

የአሁኑ ፡ ትውልድ ፡ ወንድነቱን ፡ ከአባት ፡ ወርሷል ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ዘመኑ ፡ የወለደው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ስሜቱን ፡ ስለሚያማታበት ፡ የሚይዘውን ፡ አላወቀም ። «አንድ ፡ አገልጋይ ፡ ለሁለት ፡ ጌታ ፡ አይገዛም፤ » ለምቾት ፡ መገዛት ፤ በወሬ ፡ መፈታት ፤ ባህልን ፡ ከሰውነት ፡ አውልቆ፡ የሌሎችን ፡ ባህል ፡ መያዝ ፡ መሠረት ፡ ሳይኖር ፡ ለውጥ ፡ መፈለግ ፤ የውስጥን ፡ ኅብረት ፡ ይከፋፍላል ።



ሀገር ፡ የሚከበረው ፡ የራሱን ፡ ባህል ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ከሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የሚጠቅመውን ፡ ሲከተል ፡ ነው ። ምዕራባውያን ፡ ከማንም ፡ የማይሻሉ ፡ ነበሩ ። በተፋጠነ ፡ እርምጃ ፡ ከዚህ ፡ መድረሳቸውና ፡ ኃይላቸውን ፡ እያጠነከሩ ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በጨረቃ ፡ ዓለም፡ ሊኖር ፡ የሚችልበትን ፡ አሁንም ፡ ማጥናታቸው ፡ ነው ።

የዘር ፡ ልዩነት ፡ ተደረገ ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ አይበቃም ። በአንድ ፡ አምሳል ፡ በተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የዘር ፡ ልዩነት ፡ ሊያደርጉ ፡ የደፈሩት ፤ በመላቃቸው ፡ ነው ። በአንድ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ብንገኝ ፤ የዘርም ፡ ልዩነት ፡ እንኳን ፡ በግብር ፡ ሊውል ፡ ስሙም ፡ አይሰማም ፡ ነበር ፡ አልኩት ።

እስከዚህ ፡ አልገምትም ፡ ነበር ። እውነት ፡ ነው ። የቀለም ፡ ልዩነትን ፡ መቃወም ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ። በአንድ ፡ ነገር ፡ ከበለጠ ፡ ከበታቹ ፡ ያለውን ፡ ይጐዳል ።

የሁለተኛው ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከመጀመሩ ፡ በፊት፡ ስለፖለቲካ፡ ውዝግብ ፡ የተጻፈ ፡ እንብቤ ፡ ነበር ። በመንግሥታት ፡ መካከል ፡ ጠብ እንዳይነሣ ፡ የዓለም ፡ ማኅበር ፡ ተቋቁሞ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ። ቃል ፡ ኪዳን ፡ ፈርሶ ፡ ጦርነት ፡ ቢነሣ ፤ መንግሥታቱ ፡ ተባብረው ፡ ጦርነቱን ፡ ያስቀራሉ ። አንዱ ፡ አሻፈረኝ ፡ ቢል ፡ ተጠቂው ፡ በማኅበሩ ፡ ዓላማ ፡ መሠረት ፡ ድጋፍ ፡ ያገኛል ።

ኢትዮጵያ ፡ በኢጣልያ ፡ ፋሽስት ፡ ስትወረር ፤ በተከለከለው ፡ የመርዝ ፡ ጢስ ፡ የደረሰባትን ፡ አሠቃቂ ፡ ግፍ ፡ ጀግናው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡ ለማኅበሩ ፡ አስታውቀው ፡ ነበር ። አንዲት ፡ የሣር ፡ ጎጆ ፡ ብትቃጠል ፤ የዓለምን ፡ ሰላም ፡ አናደፈርስም ፡ ተብሎ ፤ የኢትዮጵያ ፡ የግፍ፡ ወረራ ፡ በቀላል ፡ ታየ ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ «አውሮፓም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ እንዳለቀ ፡ አድርጎ ፡ ቢቈጥረው ፡ በራሱ ፡ የሚደርስበትን ፡ የሚጠብቀውን ፡ ይህን ፡ ዕድል፡ ማሰብ ፡ ይገባዋል ። እግዚአብሔርና ፡ ታሪክ ፡ ለምትሰጡት ፡ ፍርድ ፡ ምስክር ፡ ሆነው ፡ ይመለከታሉ ፡ » ተብሎ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ፡ የተነገረው ፡ ደርሶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የግፍ ፡ ወረራ ፡ እንዳለቀ ፡ አድርጎ ፡ የቈጠረው ፡ ዓለም ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ እሳት ፡ ተማገደ ።

ታሪክ ፡ ያስተምራል ፤ ወዳጅ ፡ ከዘመኑ ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የሚጓዝ፡ የማይጨበጥ ፡ ነፋስ ፡ ሆነ ። ለመኖር ፡ ራስን ፡ መቻል ፡ ነው ፡ አለና ፡ ያላያችሁትን ፡ ላስጎብኛችሁ ፡ ብሎ ፡ ይዞን ፡ ሄደ ።

የሀገሩ ፡ ተወላጆችና ፡ የውጭ ፡ ሰዎች ፡ የሚኖሩበትን ፡ ዐሳየን ። ባማረው ፡ የሕዝብ ፡ መናፈሻ ፡ በብዛት ፡ የሚደሰቱት ፡ የውጭ፡ ሀገር፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ አያችሁ ? ሲል ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ኀዘን ፡ ይነበብ ፡ ነበር ። በፊታችሁ ፡ የተደቀነው ፡ ጉዞ ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። ከዚህም ፡ የባሰ ፡ ታዩ፡ ይሆናል ። አሁን ፡ ወደማረፊያችሁ ፡ ላድርሳችሁ ፡ ብሎ፡ ከሸኘን፡ በኋላ ፤ ተሰነባበትን ። ኬንያን ፡ ጐብኝተን ፡ ስንጨርስ ፡ ነፃ ፡ ካልወጡት ፡ የአፍሪካ ፡ ሀገሮች ፡ አንዷ ፡ ወደሆነችው ፡ ወደ፡ ሮዲዥያ ፡ ለመግባት ፡ እንዲያመቸን ፡ በቅድሚያ ፡ ወደ ፡ ዛምቢያ ፡ ሄድን ።

ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ ከመጡ ፡ ቱሪስቶች ፡ ጋር ፡ ተቀላቅለን ፡ ዛምቢያን ፡ ጐበኘን ። አተኩሮ ፡ ካዩት ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ይለያል ። የአፍሪካን ፡ የተፈጥሮ ፡ ሀብት ፡ ምዕራባውያን ፡ ግጠውታል ። አፍሪካውያን ፡ በዕውቀት ፡ ሲዳብሩ ፤ በሥራ ፡ ሲጐለምሱ ፤ የጠነከረና ፡ የተባበረ ፡ አንድነት ፡ ሲኖራቸው ፤ አፍሪካ ፤ የአፍሪካውያን ፡ ብቻ ፡ ትሆናለች ፡ እያልን ፤ ሐሳብ ፡ ተለዋወጥን ።

ነፃ ፡ የሆኑ ፡ የአፍሪካ ፡ ሀገሮች ፡ ከሌላው ፡ ጋር፡ ተወዳዳሪ ፡ የሆነ፡ አቅዋም ፡ እንዲኖራቸው ፡ እየታገሉ ፤ ነፃ ፡ ያልወጡት ፡ እንዲወጡ ፡ ይጥራሉ ። አፍሪካውያን ፡ ሲገናኙ ፡ የቀደመ፡ ዕውቀት፡ ባይኖራቸውም፡ በፈገግታ ፡ ይነጋገራሉ ። የሀገሩ ፡ ተወላጅ ፡ የሆነ ፡ ዛምቢያዊ ፡ እንግዶች ፡ ትመስሉኛላችሁ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀን ።

በአፍሪካውያን ፡ መካከል ፡ እንግድነት ፡ የለም ፤ ሀገሩ ፡ ሀገራችን፡ ነው ። ለወግ ፡ ያህል ፡ ግን ፡ እንግዶች ፡ ነን ፡ ባልነው ፡ ጊዜ ፤ እየሳቀ ፡ ትክክል ፡ ነው ፡ አለን ።

ወደ ፡ ሮዴዥያ ፡ ለመግባት ፡ እንደምን ፡ እንደምንችል ፡ ጠየቅነው ፤ ሀገር ፡ ጐብኝዎች ፡ ስለሆናችሁ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ ከመጡ ፡ ሀገር ፡ ጐብኝዎች ፡ ጋር ፡ ተቀላቅላችሁ ፡ ትገባላችሁ ፡ አለን ። ይህን ፡ በዚህ ፡ እንዳቆምን ፤ ስለአፍሪካውያን ፡ አንድነት ፡ ብናወጋስ ? የአፍሪካውያን ፡ ጉዳይ ፡ የራሳችን ፡ ስለሆነ ፤ ደስ ፡ ይለናል ፡ አልነው ።

ነፃ ፡ ያልወጡ ፤ ስለነፃነታቸው ፡ በሚያደርጉት ፡ ትግል ፤ እየተደበደቡ ፡ ያልቃሉ ። ነፃነት ፡ የሚመሠረተው ፡ በደም ፡ ነው ። ስለሀገራቸው ፡ ነፃነት ፡ ደማቸው ፡ የፈሰሰ ፡ የክብር ፡ አክሊል ፡ ይጠብቃቸዋል ። ግፉ፡ በዓለም ፡ ቁና ፡ ይሠፈራል ። ድርጊቱን ፡ ብቻ ፡ ከማውገዝ፡ በቀር ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ግፍ ፡ የሚዋልባቸውን ፡ ነፃ ፡ ያወጣ ፡ የለም ።



በጐረቤታችን ፡ ሮዴዥያ ፡ ቍጥራቸው ፡ እጅግ ፡ አነስተኛ ፡ የሆኑ ፡ ነጮች ፡ በዘር ፡ ልዩነት ፡ የሚፈጽሙት ፡ ግፍ፤ከመሥፈሪያው ፡ አልፍዋል ። ሮዴዥያን ፡ እንደሀገራቸው ፡ አድርገው ፡ የያዙ ፡ ነጮች ፡ ከሚለቁ ፤ ተናንቀው ፡ ቢሞቱ ፡ ይመርጣሉ ፡ አለን ።

ዘመን ፡ ያነሣቸውን ፡ ኃያላን ፡ ዘመን ፡ ይጥላቸዋል ። ዘመን ፡ የጣላቸው ፡ ደካማዎች ፡ በዘመን ፡ ይነሣሉ ። አፍሪካውያን ፡ አንድነታቸውን ፡ መሥርተው ፡ መሥራት ፡ የጀመሩት ፡ መቼነው ? አንድ ፡ ትውልድ ፡ አላለፈም ። የሚቀጥለው ፡ ትውልድ ፡ በትምህርት ፡ ተወልዶ ፡ በትምህርት ፡ የሚያድግ ፡ ስለሆነ ፤ ያሁኑ ፡ ትውልድ ፡ ያቆየውን ፡ በዕውቀት ፡ አስፋፍቶ ፡ አፍሪካ ፡ የአፍሪካውያን ፡ ብቻ ፡ የምትሆንበት ፡ ጊዜ ፡ አጭር ፡ ነው ፡ አልነው ።

አፍሪካን ፡ በማስታውስበት ፡ ጊዜ ፡ ራሴን ፡ እረሳዋለሁ ። ስለሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ስንማር ፤ ፍጡር ፡ ፍጡር ፡ ነው ። ከፍጡራንም ፡ ሰው ፡ በፈጣሪው ፡ አምሳል ፡ እንደመፈጠሩ ፡ የፍጡራን ፡ ገዥ ፡ ነው ። በሰው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለም ። የመጀመሪያው ፡ ሰው ፡ ሕግን ፡ በመጣሱ ፡ ሞትን ፡ አመጣ ። ከሕግ ፡ አፍራሽ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፡ አሁንም ፡ ሕግ ፡ አፍራሽ ፡እየሆነ ፡ በመካከሉ ፡ ልዩነትን ፡ በመፍጠር ፡ ሰውን ፡ ሰው ፡ ይገድለዋል ።

የሌላው ፡ ፍጡራን ፡ ባሕርይ ፡ ሲመረመር ፡ ከሰው ፡ የተሻለ ፡ሆኖ፡ ይገኛል ። ማናቸውም ፡ ፍጥረት ፡ ወገኑን ፡ ይፈልጋል ። በወገን ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለም ። አብረው ፡ ይኖራሉ ፡ ያገኙትን ፡ ይካፈላሉ ፡ አለ ።

በዘር፡ ልዩነት፡ በሚፈጸመው፡ ግፍ፤ ሰውን፡ ከሌላው ፡ ፍጥረታት፡ ምነው ፡ አሳነስከው ? አዬ ፡ «ያልተነካ፡ ግልግል ፡ ያውቃል፡ » የሚፈጸመውን ፡ ግፍ ፡ የምትሰሙት ፡ በወሬ ፡ ነው ። እኔ ፡ ቍስሉ ፡ ያልሻረልኝ ፡ ገመምተኛ ፡ ነኝ ። አሁን ፡ ባገግም ፡ ነፃ ፡ ለመውጣት ፡ በትግል ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ አፍሪካውያን ፡ ሳስታውስ ፤ ቍስሉ ፡ እንደገና ፡ እያመረቀዘ ፡ ያመኛል ። ዋ ፤ ነፃ ፡ ሆኖ ፡ በሀገር ፡ መኖር ፡ ቀላል ፡ ይመስላችሁ ፡ ይሆናል ? በነፃነትም ፡ የሚኖሩ ፡ ይበሳጩ ፡ ይሆናል ።

እንኳን ፡ ጠይቀውኝ ፡ እንደዚሁ ፡ መናገር ፡ እወዳለሁ ። የምናገረው ፡ ስለማያልቅ ፡ ጊዜያችሁን ፡ አባክናለሁና ፤ ወደሮዴዥያ ፡ ለመ

ግባት ፡ እንድትችሉ ፡ ልርዳችሁ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ጐብኝዎች ፡ አስተናጋጅ ፡ ድርጅት ፡ ወሰደን ። ድርጅቱ ፡ ፓስፖርታችንን፡ ዐይቶ ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ሀገር ፡ ከመጡ ፡ ጐብኝዎች ፡ ጋር ፡ እንደምናልፍ ፡ ነገረን ።

አቶቡስን ፡ የሞሉት ፡ ምዕራባውያን ፡ ነበሩ ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ መዝሙር ፡ እየዘመሩ፡ ስንጓዝ ፤ በሐሳብ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ስትዋኝ ፡ አየኋት፡ ፀሐይን ፡ ስጠራት ፡ ደንገጥ ፡ ብላ ፡ አቤት ፡ አለች ። ወዴት ፡ ሄደሽ ፡ ነበር ? ምን ፡ ማለትህ ፡ ነው ፤ ከአጠገብህ ፡ ሆኜ ፡ ወዴት ፡ የሄድኩ ፡ መስሎህ ፡ ነው ፡ አለችኝ ።

በሐሳብ ፡ በመመሰጥሽ ፡ ነዋ ፤ ብዬ ፡ ንግግሬን ፡ እቀጥላለሁ ፡ ስል፤ ነው ? ገባኝ ፡ በርግጥ ፡ በሐሳብ፡ ርቄ ፡ ሄጄ ፡ ነበር ። አብረውን ፡ ያሉት ፡ በፊታቸው ፡ ደስታ ፡ ይነበባል ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ባጋጠመኝ ፡ ጊዜ ፤ በሐሳብ ፡ መንጽር ፡ ሀገሬንና ፡ የሀገሬን ፡ ሕዝብ ፡ ዐያለሁ ።

ከአንዱ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ሀገር ፡ ተዘዋውሮ ፡ ማየት ፡ ደስታ ፡ ይፈጥራል ። እየሩና ፡ ምግቡ ፡ ለውጥ ፡ ነው ። ዓይን ፡ በሚያየው ፡ አዕምሮ ፡ በሚያስበው ፡ ደስታ ፡ ይገኛል ፡ እያለች ፡ ስታጫውተኝ ፡ ሁለቱን ፡ ሀገሮች ፡ ከሚያዋስነው ፡ ደረስን ።

በሮዴሽያ ፡ ግዛት ፡ ለምናደርገው ፡ ጉብኝት ፡ የተመደበው ፡ አስተናጋጅ ፡ ተረከበን ። ፓስፖርት ፡ እያሳየን ፡ አለፍንና ፡ በአቶቡስ ፡ ውስጥ ፡ ገብተን ፡ ወደ ፡ ሳልስበሪ ፡ ተጓዝን ። በሳልስበሪ ፡ አፍሪካውያን ፡ የሚኖሩበትን ፡ ዐየን ። «ኑሮ ፡ ካሉት ፡ መቃብር ፡ ይሞቃል ፡ » ነውና ፡ አውሮፓውያን ፡ ነጮች ፡ ወደሚኖሩበት ፡ ሠፈር ፡ ጥቁሮች ፡ ድርሽ ፡ አይሉም ።

የመኖር ፡ ተስፋውን ፡ የቈረጠ ፡ ሰው ፤ ለሕይወታዊ ፡ ኑሮው ፡ ደንታ ፡ የለውም ። በፍጡራን ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ሲሠራ ፤ ፈጣሪ ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ አለ ፡ እያለች ፡ ዕንባዋ ፡ እስኪንዠቀዠቅ ፡ ድረስ ፡ አዘነች ፡ ፀሐይ ።

ሰው ፡ ከግፍ ፡ ሥራ ፡ ቢርቅማ ፡ ዓለም ፡ በውሃ ፡ አይጠፋም ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ የሀገራቸው ፡ ባለቤት ፡ የሆኑት ፡ አፍሪካውያን ፡ ግፍ ፡ ተቀብለዋል ። ሥልጣኔ ፡ ከወዴት ፡ እንደተነሣ ፡ ወዴት ፡ እንዳለ ፡ ብንመረምር ፡



ወደፊት ፡ የነበሩት ፡ ወደኋላ ፤ ወደኋላ ፡ የነበሩት ፡ ወደፊት ፡ ቀድመዋል ፡ ስል ፡ መለስኩላት ።

የሰው ፡ የመኖር ፡ ዘመኑ ፡ አጭር ፡ ነው። አፍሪካውያን ፡ ወዴት፡ እንደነበሩና ፡ ከምን ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ እንደደረሱ ፤ ያለፈውን ፡ ከታሪካቸው ፤ የዘመኑን ፡ በእድገታቸው ፡ ለማየት ፡ ዕድል ፡ የሚገጥማቸው ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

በተመደበልን ፡ ሆቴል ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ ካደረግን ፡ በኋላ፡ ራት፡ ተጋበዝን ፤ በጉዞው ፡ ከተዋወቅናቸው ፡ መካከል፡ ጥቂቶቹ ፡ እኛ ፡ ወዳለንበት ፡ መጥተው ፡ ጫወታ ፡ ጀመርንና ፤ አንዱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ዓይናችንን ፡ ጣል ፡ አድርገን ፡ በማተኰር ፡ የምንመለከታችሁ ፤ ከምናውቃቸው ፡ አፍሪካውያን ፡ የተለየ ፡ ከደም ፡ግባት ፡ ጋር ፡ ውበት፡ አዋሕዳችሁ ፡ የያዛችሁ ፡ በመሆናችሁ ፡ ነው ። የእናንተን ፡ ቊንጅናና ፡ ውበት፡ ስናደንቅ ፤ ጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ እንደናንተ ፡ የተዋበ ፡ ይሆን ?።

ሀገራችሁ ፡ በነፃነት ፡ የኖረች ፡ የተባረከችና ፡ የተቀደሰች ፡ ሀገር ፡ መሆኗን ፡ በዝና ፡ ስለምናውቅ ፡ ነው ። በዘመናት ፡ መካከል ፡ ወራሪ ፡ ጠላት ፡ ቢነሣ ፡ በአላት ፡ የክርስትና ፡ እምነት ፡ በጀግንነት ፡ ድል ፡ ተቀዳጅታለች ። በአፍሪካ ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ የነፃነት ፡ መሸጋገሪያ ፡ የሆነች ፡ ኢትዮጵያ ፤ ለአፍሪካውያን ፡ አለኝታ ፡ ስለሆነች ፤ ለዘለዓለም ፡ እንድትኖር ፡ ጽዋችንን ፡ እናንሣ ፡ ብሎ ፡ ከመናገሩ ፡ ሁሉም ፡ በደስታ ፡ ስሜት ፡ ተፈንቅለው ፡ ጽዋቸውን ፡ ይዘው ፡ ተነሡ ።

የነፃነት ፡ ንቅናቂያቸው ፡ እስከ ፡ ምን ፡ ድረስ ፡ እንደሆነ ፡ ላቀረብሁት ፡ ጥያቄ ፡ በየጊዜው ፡ የሚፈጸምብንን ፡ ግፍ ፡ ሳሰሙት ፡ አልቀራችሁም ። ሰው ፡ በተስፋ ፡ ይኖራል ። የሀገራችን ፡ ወራሪ ፡ ኃይሉን ፡ እያጠነከረ ፡ አቅዋሙን ፡ እያስፋፋ ፡ በነፃነት ፡ የተቃጠለ ፡ ስሜት ፡ ያላቸውን ፡ እየረሸነ ፡ ሀገራችንን ፤ ሀገሩ ፡ አድርጎ ፡ ይዟል ።

አፍሪካውያን ፡ ወንድሞቻችን ፡ ከባርነት ፡ ወደአርነት ፡ ነፃ ፡ እንድንወጣ ፡ የሚያደርጉልን ፡ ጥረት ፡ አልተቋረጠም ። ወደ ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ ብትሄዱ ፡ የአፍሪካውያንን ፡ ሥቃይ ፡ ታያላችሁ ። የሀገራችንን ፡ እድገት ፡ እመምራት ፡ ደረጃ ፡ እስክንደርስ ፤ በግፍ ፡ ብንደበደብ ፤ ብንታሠር ፤ የሚሠነዘርብንን ፡ ሁሉ ፡ እንቀበላለን ።

ለአፍሪካውያን ፡ መመኪያ ፡ የሆነችው ፡ ኢትዮጵያ ፤ በኢጣልያ ፡ ፋሽስት ፡ ተወርራ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፤ ጀግኖችዋ ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ሆነው ፡ ያደርጉት ፡ የነበረውን ፡ ጀግንነት ፡ ስንሰማ ፡ ወኔያችን ፡ ይቀሰቀሳል ። ጀግንዎችዋ ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ሆነው ፡ ነፃነታቸውን ፡ ላለማስደፈር ፡ ሲከላከሉ ፤ ሕፃናትና ፡ ሽማግሌዎች ፤ በዶማና ፡ በአካፋ ፡ ተደብድበው ፡ በእሳት ፡ ተቃጥለው ፡ ንጹሕ ፡ ደማቸውን ፡ አፍስሰዋል ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ በራሱ ፡ መልክ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ይሠራል ። «ባልንጀራህን ፡ እንደራስህ ፡ ውደደው፡ » « በራስህ ፡ ላይ ፡ ሊያደርጉብህ ፡ የማትወደውን ፤ አንተም ፡ በሌላው ፡ አታድርግ ፡» «ሁለት ፡ ቢኖርህ ፤ ለሌለው ፡ አንዱን ፡ ስጥ ፡» የተባለውን ፡ ማነው ፡ የፈጸመው ? ። ይህ ፡ ከተነማማ ፤ ምዕራባውያን ፡ ወደአፍሪካ ፡ የገቡት ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ሳይሆን ፡ የወንጌል ፡ መልእክተኞች ፡ ሆነው ፡ ነበር ። ሰው ፡ ሰው ፡ ነው ፤ በሰው ፡ መካከል ፡ ትልቅና ፡ ትንሽ ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ ይሰብኩ ፡ ነበር ። በአንደበታቸው ፡ ወንጌልን ፡ እየሰበኩ ፡ ወገኖቻቸውን ፡ ወደሀገሪቱ ፡ በብዛት ፡ አግብተው ፡ ሀገሪቱን ፡ ሊወሯት ፡ በቁ ፡ በማለት ፡ አንደኛው ፡ ንግግሩን ፡ እንዳቆመ ፤ በቍጥር ፡ እንደመብዛታችሁ ፡ በአስተሳሰብ ፡ ተባብራችኋል ፤ ትግሉን ፡ የቀጠሉትስ ፡ የነፃነት ፡ ስሜት ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

ብዛት ፡ አይሠራም ፡ እንጂ ፡ በቍጥርማ ፡ ከእጥፍ ፡ በላይ ፡ ነን ፤ ወኔ ፡ ካለ ፡ ግን ፡ ጥቂቱም ፡ ቢሆን ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ።

ስለነፃነቱ ፡ የሚሠራ ፡ አለ ። በዕለት ፡ ደስታ ፡ እየተሸነፈ ፡ የጠላት ፡ መሣሪያ ፡ የሚሆን ፡ አለ ። ጠላት ፡ የደረጀው ፡ የተባበረ ፡ ሐሳብና ፡ አንድነት ፡ እንደሌለን ፡ ገምቶ ፡ ነው ። ተጠቅተው ፡ የሚያስጠቁ ፤ ምሥጢራችንን ፡ እያወጡ ፡ እቅዳችን ፡ ፈርሶ ፡ እየታደንን ፡ የምንያዘው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ደካማ ፡ ሐሳብ ፡ ባላቸው ፡ አይደለምን ?

የጠላት ፡ መሣሪያ ፡ ከሆነ ፡ ወገን ፡ ይልቅ ፡ ጐራዴ ፡ መዞ ፤ ጦር ፡ ነቅንቆ ፤ የሚወጋ ፡ ጠላት ፡ ይሻላል ። ለመሆኑ ፡ ከዓለም ፡ ምን ፡ ድጋፍ ፡ አግኝታችኋል ? በነጮችስ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ጭቆና ፡ ተደርግዋል ?

ዓለም ፡ በድምፅ ፡ ደግፎናል ፤ በነጮቹ ፡ ላይ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ጭቆና ፡ እንዲደረግ ፡ አውጀዋል ። አፍሪካውያን ፡ አዋጁን ፡ ቢቀበሉት ፡ ሌላው ፡ አልተቀበለውም ። አፍሪካውያን ፡ ጦርነት ፡ ያደርጉ ፡ ይሆናል ፡ እያለ ፡ ጠላታችን ፡ ኃይሉን ፡ በበለጠ ፡ አጠንክሯል ። ቤቱ ፡ ሲቃጠል ፡



ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ የማያሰማ ፡ የለም ። ጩኸቱን ፡ የሰማ ፡ ካልረዳ ፡ ንብረቱ ፡ ጋይቶ ፡ ይቀራል ።

የኛም ፡ አቅዋም ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ የሚፈጸምብንን ፡ ግፍ ፡ አሰማን ። ዓለም ፡ ጆሮውን ፡ ከፍቶ ፡ አዳመጠን ፤ ጋዜጠኞችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባለሞያዎች ፡ እየመጡ ፡ የዓይን ፡ ምስክር ፡ ሆነው፡ ዐዩ ፤ ሁሉም፡ ንግግር ፡ ብቻ ፡ ሆነ ።

በነፃነት ፡ የጋለ ፡ ስሜት ፡ ያላቸው ፡ ዘመናቸውን ፡ በእሥር ፡ ቤት ፡ እንዲያሳልፉ ፡ ተደርጓል ። ከግፉ ፡ ጽናት ፡ ሞትን ፡ የመረጡ ፡ ደፍረው ፡ ሲናገሩ ፡ በሞት ፡ ይቀጣሉ ።

ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ እርምጃ ፡ ወስዶዋል ። ዋ ! «ሆድ ፡ ሲያውቅ ፡ ዶሮ፡ ማታ ፡ » የሚደረገውን ፡ ግፍ፡ ከዓለም፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ያወግዛል። መንግሥቱንም፡ አላውቅም ፡ ይላል ። ለአፍሪካውያን ፡ ነፃነት ፡ ሳይሆን ፡ በመካከላቸው ፡ ስላለው ፡ የሥልጣንና ፡ የጥቅም ፡ ግንኙነት ፡ ይነጋገራሉ ። ከልብ ፡ ቢደግፍማ ፤ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ያሳለፈው ፡ ውሳኔ ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ ይቀር ፡ ነበር !

ሀገራችንን ፡ ሀገራቸው ፡ አድርገው ፡ ግፍ ፡ በመፈጸም ፡ ደም ፡ ስለተቃባን ፤ ከምድሪቱ ፡ ጠፍተን ፡ ሀገሪቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ የነርሱ ፡ ካልሆነች ፤ በኛና ፡ በነርሱ ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡ አይኖርም ። «የወጋ ፡ ቢረሳ ፡ የተወጋ ፡ አይረሳም ፡ » ስንት ፡ ወንድሞቻችን ፡ በበሽታ ፡ አለቁ ። አሁንስ ፡ እሥር ፡ ቤቱን ፡ የሞሉት ፡ አፍሪካውያን ፡ አይደሉም ?

ሰው ፡ ራሱን ፡ ብቻ ፡ ወዶ ፡ ሕሊናው ፡ የሚወቅሰውን ፡ ቢሠራ ፡ መፀፀቱ ፡ አይቀርም ። እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ሰዎች ፡ የሉባቸውም ?

ጉድ ፡ ነው ፡ እኮ ፤ «በጥባጭ ፡ ካለ ፡ ማን ፡ ጥሩ ፡ ይጠጣል ፡ » በሰው ፡ ላይ ፡ ችግር ፡ ሲያዩ ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ አሉ ። እንኳን ፡ ለሰው ለእንስሳት ፡ የሚራሩም ፡ አሉ ።

በተለይ ፡ በክርስትና ፡ እምነት ፡ ጥልቀት ፡ ያላቸው ፡ ድርጊቱን ፡ በይፋ ፡ እየተቃወሙ ፡ ታሥረዋል ። ከሕዝብ ፡ ወገን ፡ የሐሳባቸው ፡ ተባባሪ ፡ ያልሆኑት ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ሀገራቸው ፡ ይመለሳሉ ።

መርዝ ፡ እንድዋ ፡ ጠብታ ፡ ታጠፋለች ። ታሪክ ፡ በማይረሳው ፡ በሁለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፤ በሚሊዮን ፡ የሚቈጠር ፡ ሕዝብና ፡ ንብረት ፡ የጠፋው ፡ በነሂትለር ፡ አይደለም ?

በዓለም ፣ የደረሰውን ፣ ስንመረምር ፣ እንጽናናለን ። በተለይ ፣ አሠቃቂ፣ በሆነ፣ አሟሟት ፣ የሞቱትን ፣ ስድስት ፣ ሚሊዮን፣ እሥራኤላውያንን ፣ አስበን ፤ የእሥራኤላውያንን ፣ የዛሬ ፣ አቅዋም ፣ ስንመለከት ፤ ጊዜ ፣ ሁሉን ፣ ይለውጣል ፣ ካሉን ፣ በኋላ ፤ ጥቁሮች ፣ የምንዘዋወርበት ፣ ሰዓት ፣ የተወሰነ ፣ ስለሆነ ወደ ፣ ማረፊያችሁ ፣ በጊዜ ፣ ሂዱ ፣ ብለው ፣ ተለያየን ።

ከከተማው፣ ወጣ ፣ ብለን ፣ የአፍሪካውያንን ፣ የኑሮ ፣ አቅዋም ፣ ስንጐበኝ ፤ ብዙዎቹ ፣ እንደብርቅ ፣ ተመለከቱን ።

በባላጋራ ፣ ፊት ፣ ራስን ፣ መጣል ፣ ማንን ፣ ነው ፣ የሚጐዳው ? ማለፍ ፣ እያለ ፣ ምን ፣ ያበሳጫል ። ጠላትን ፣ መቋቋም ፣ ቀላል ፣ ነገር ፣ አይደለም ። ቢቾነፍም፣ ቢያቾንፍም ፤ እስከ ፣ መጨረሻ፣ ደቂቃ ፣ ድረስ፣ በጠላት ፣ ፊት ፣ የጠነከረ ፣ አቅዋም ፣ ማሳየት ፣ ወንድነት ፣ ነው ። እግራችን ፣ ይህችን ፣ አገር፣ ከረገጠ ፣ ጀምሮ ፣ የምናያቸው ፣ አፍሪካውያን፣ ወኔያቸው ፣ ደክሟል ፤ ባላቸው ፣ አልተግደረደሩም ። ነጮችን ፣ ሲያዩ ፣ የበታችነታቸውን ፣ ያሳያሉ ።

የሰው ፣ ልጅ ፣ የተስፋ ፣ ብልጭታ ፣ በቶሎ ፣ ማግኘት፣ ይፈልጋል። ተስፋው ፣ እየጨለመ ፣ ሲሄድ ፣ የሚጠብቀውን ፣ እንዳጣ ፣ ይቈጥረዋል ። ተስፋ ፣ ከቆረጠ ፣ ለሕይወቱ ፣ አይሳሳም ።

የአፍሪካውያን ፣ ስሜት ፣ በዚህ ፣ ላይ ፣ ተመሥርትዋል ። በሞዛቢክና ፣ በደቡብ ፣ አፍሪካ ፣ የሚፈጸመው ፣ ግፍ ፣ ተመሳሳይ ፣ ነው ። ለጥፍራቸው ፣ መቁረጫ ፣ ስንጢ ፣ የሌላቸው ፣ ከነጮች ፣ ጋር ፣ የሚያደርጉት ፣ ትግል ፣ እየተራዘመ ፣ በሄደ ፣ መጠን ፣ ተስፋ ፣ ይቆርጣሉ ።

ስለሆነም ፣ የክርስትና ፣ እምነት ፣ ያለው ፣ ልበ ፣ ሙሉ ፣ ጀግና ፣ ተስፋ ፣ አይቆርጥም ። ደም ፣ ሳይፈስ፣ ሥርየትና ፣ ነፃነት ፣ የለም ። የሰው፣ ልጅ ፣ ነፃ ፣ የወጣው ፣ በደም ፣ ነው ። በእምነት ፣ እየተራመዱ ፣ ትግላቸውን ፣ እንዲቀጥሉ ፣ የሚያበረታታቸው ፣ ያስፈልጋቸዋል ።

በሮዴዥያ ፣ የምናደርገውን ፣ ጉብኝት ፣ ስለፈጸምን ፣ ወደአሜሪካን ፣ ከመሄዳችን ፣ በፊት ፣ ወደለንደን ፣ በረርን ። አየሩ ፣ ጥሩ ፣ አልነበረም ። መውጣት ፣ መውረድ ፣ በዝቶ ፣ አውሮፕላን ፣ ላይ ፣ መውጣት ፣ ከጀመርን ፣ ጀምሮ ፣ ያላጋጠመን ፣ ስለደረሰ ፣ ፀሐይ ፣ መደንገጥዋ ፣ አልቀረም ።



የአየሩ ፣ ንቅናቄ ፣ ስለተባባሰ ፤ በወንበራችን ፣ በሚገኘው ፣ ቀበቶ ፣ ወገባችንን ፣ አበት ፣ እንድናደርግ ፣ ታዘዝን ። ንዛዜያችንን ፣ አሳምረን ፣ መምጣታችን ፣ ደኅና ፣ ሆነ ፣ እንጂ ፤ ሌላውስ ፣ እንዳሻው ፣ ብላ ፣ የተስፋ ፣ መቁረጥ ፣ ጭላንጭል ፣ ተናገረች ፣ ፀሐይ ።

በአውሮፕላን ፣ መሄድ ፣ ልማድ ፣ ስለሌለን ፣ ከፍርሀት ፣ ላይ ፣ ጣለን ፣ እንጂ ፤ ልማድ ፣ ያላቸው ፣ ሳይሰማቸው ፣ በእንቅልፍ ፣ ተውጠዋል ፣ እያቸው ፣ አልኳት ። ወደዚያው ፣ አየሩ ፣ ተለወጠና ፣ ፍርሃታችን ፣ ጠፍቶ ፣ ለንደን ፣ ደረስን ።

አስፈላጊውን ፣ የመግቢያ ፣ ፈቃድ ፣ ጨርሰን ፤ ለሀገሩ ፣ እንግዳ ፤ ለሰዉ ፣ ባዕድ ፤ ስለሆነ ፣ ወደሚያስረዳው ፣ ክፍል ፣ ሄደን ፣ የሆቴሎችን ፣ ደረጃ ፣ ጠየቅን ። የሚመጥነንን ፣ መርጠን ፣ በታክሲ ፣ ተጓዝን ።

የማረፊያ ፣ ክፍላችንን ፣ ከያዝን፣በኋላ፤ ሀገር፣ አስጐብኝ ፤ ከሆቴሉ ፣ ድረስ ፣ መጥቶ ፣ ወሰደን ። ኋይት ፣ ታዎር ፣ የተባለውን ፣ ጐበኘን ። የለንደን ፣ ታዎር ፣ የተሠራው ፣ በሂንሪ፣ ስምንተኛ ፣ ጊዜ ፣ ነው ። ከየአገሩ ፣ የተሰበሰቡትን ፣ ልዩ ፣ ልዩ፣ ብረት ፣ ለበስ፣ የጦር ፣ መሣሪያዎች ፣ ዐየን ። የእሳት ፣ አደጋ ፣ መከላከያ፣ ባልነበረበት ፣ ዘመን ፤ ከአንድ ፣ ዳቦ ፣ ጋጋሪ ፣ ቤት ፣ በተነሣው ፣ እሳት ፣ ለንደን ፣ ተቃጥላ ፣ ለማስታወስ ፣ የተሠራ ፣ ሐውልት ፤ በሁለተኛው ፣ የዓለም ፣ ጦርነት ፣ ሕይወታቸውን ፣ ለሰው ፣ የተቋቋመውንና ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ሐውልቶችን ፣ ተመለከትን ። የእንግሊዝ ፣ ነገሥታት፣ የሚነግሡበትን ፣ የቅዱስ ጳውሎስን ፣ ቤተ፣ ክርስቲያን ፣ ጐበኘን ። የነገሥታቱን ፣ መቃብር ፣ በዚሁ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ አየን ።

ውድ ፣ ከሆኑ ፣ ማዕድኖች ፣ የተሠሩ ፣ እያንዳንዳቸው ፣ እስከ ፣ አምስት ፣ መቶ ፣ ሺህ ፣ ፓውንድ ፣ ግምት ፣ ያላቸው ፣ መብራቶች ፣ በቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ ውስጥ ፣ ይገኛሉ ። ከግድግዳው ፣ ላይ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ጽሑፎች ፣ ሲነበቡ ፤ በግዕዝ ፣ የተጻፈ ፤

« ንዑ ፣ ንብኪ ፣ ምስለ ፣ ክቡር፣ ሞታ ፤
ለእንተ ፣ አዕረፈት ፣ እንዘ ፣ በክርስቶስ ትውክልታ ።
ዛቲ ፣ እግዝእት ፣ ርትዕት ፣ ወጽንዕት ፣ በሃይማኖታ ፤
የዋሂት ፣ ወንጽሕት ፣ እንዘ ፣ ሀለወት ፣ በሕይወታ ፤
ውድስት ፣ ውብፅዕት ፣ ኮነት ፣ በሞታ ። »

« ሃይማኖቷ ፡ የጸና ፡ የቀና ፡ በክርስቶስ ፡ ታምና ፡ ላረፈች ፡ እመ ቤት ፡ ስለክቡር ፡ ሞቷ ፡ እናልቅስ ፤ በሕይወቷ፡ ሳለች ፡ ደግና ፡ ንጽሕት ፤ በሞቷም ፡ ፈጽማ ፡ የተመሰገነች ፡ ሆነች » የሚል ፡ ነው ።

ከለንደን ፡ ከተማ፡ ኻያ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር፡ ርቆ ፡ የሚገኘውን፡ ዋንስር፡ ካስትል ፡ የጥንት ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ጐበኘን ። የእንግሊዝን ፡ ታሪክ፡ የመሠረተው ፡ዊሊያም ፡ዘኰንከረር (ድል፡አድራጊው) የተባለው፡ንጉሥ፡ የሠራው፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። በቤተ፡ መንግሥቱ ፡ የእንግሊዝ ፡ ነገሥታት ፡ የዕረፍት፡ ጊዜ ፡ የሚያሳልፉበትና ፡ ታላላቅ ፡ የመንግሥቱ ፡ እንግዶች ፡ የሚያርፉበት፡ ንጉሣውያን፡ ቤተሰቦች ፡ የሚዳሩበት ፡ ነው ። ለታወቁ ፡ ታላላቅ ፡ ነገሥታትና ፡ መሪዎች ፡ የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ « ፖይንት ፡ ጋርተን ፡» የሚባለውን ፡ የመጨረሻ ፡ የማዕርግ ፡ ሽልማት ፡ የሚሸልመው ፡ በዚህ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። የተሸለሙት ፡ የየሀ ገሩ ፡ ነገሥታትና ፡ መሪዎች ፡ የሀገራቸው ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ አጊጦ ፡ ስማቸው ፡ ይገኛል ።

በቤተ፡ መንግሥቱ ፡ ግቢ ፡ በሚገኘው ፡ የቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የየሀገሩ ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማዎች ፡ ተሰ ቅለዋል ። በሠላሳ ፡ ሰባተኛ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰንደቅ፡ ዓላማ፡ ይውለበለባል ። የእንግሊዝ ፡ መሪዎችን ፡ መቃብር ፡ ስንጐበኝ ፡ የአፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ልጅ ፤ ልጅ ፡ ዓለማየሁ ፡ ቴዎድሮስ ፡ በፈረንጆች ፡ ዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ ሚያዝያ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፲፩ ፡ ዓ. ም. ተወልዶ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፰፻፺፫ ፡ ዓ.ም. ሞተ ። ይህን፡ መቃብር ፡ ያሠሩት ፡ ንግሥት፡ ቪክቶሪያ ፡ ናቸው ። » የሚል ፡ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ አነበብን ።

የእንግሊዝ ፡ ሕዝብ ፡ በሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ የሚወደድ ፡ ነው ። ለሰው ፡ አክብሮት ፡ ያሳያል ። ለሚጠይቁት ፡ ያልተጠበቀ ፡ አገልግሎት ፡ ይሰ ጣል ። የአልኮል ፡ መጠጦች ፡ ቀን ፡ አይሸጡም ። ትሕትናቸውን ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ ከመመስከራችን ፡ በፊት ፤ ከሰው ፡ ጋር ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ ለመለዋወጥ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ መናፈሻ ፡ ሄድን ።

ሕዝቡ ፡ በሥራ ፡ ተጠምዶ ፡ ውሎ ፡ የሚዝናናው ፡ ከሥራ ፡ በኋላ ፡ በመሆኑ ፡ በጣም ፡ ሥፍራውን፡ አጣቦት ፡ ነበር ። ሁለት ፡ ሰዎች፡ በተቀ መጡበት ፡ ባለው ፡ ትርፍ ፡ ወንበር ፡ ተቀመጥን ። መጠጥ ፡ ያልያዙ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ ይምጣላችሁ ፡ ብለው ፡ ጠየቁን ። አዘዝን ፤ ኢትዮጵያው



ያን ፡ መሆናችንን ፡ ሲያውቁ ፡ የወዳጅነት ፡ አስተያየታቸውን ፡ ገለጡ ልን ። በጐብኝታችን ፡ ምን ፡ አስተያየት ፡ እንዳለን ፡ ጠየቁን ። በታሪ ካዊ ፡ ሥፍራዎች ፡ ያለንን ፡ አድናቆት ፡ ገለጥንላቸው ።

ከለንደን ፡ በፊት፡ የጐበኘናቸውን ፡ ሀገሮች ፡ ጠየቁን ። ነገርናቸው፤ የእንግሊዝ ፡ ቅኝ ፡ ሀገር ፡ የነበሩ ፡ ናቸው ። ሮዴዥያ ፡ ግን ፡ ገና ፡ ነፃ ፡ አልወጣም ። የሮዴዥያ ፡ ነፃ ፡ መውጣት ፡ ሕልም ፡ ነው ፡ አሉን ። በሮዴዥያ ፡ የሚገኙት ፡ ጥቂት ፡ ነጮች ፡ የናንተ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ። በአቀባበላችሁና ፡ በትሕትናችሁ ፡ ተወዳጅነት ፡ ታተርፋላችሁ ። በሮዴ ዥያ ፡ አፍሪካውያን ፡ ላይ ፡ ወገኖቻችሁ ፡ የሚፈጽሙት ፡ ግፍ ፡ የአረመ ኔነት ፡ ሥራ ፡ ስለሆነ ፤ ዝም ፡ ብላችሁ ፡ እንዴት ፡ ታያላችሁ ፡ አልና ቸው ።

የሮዴዥያ ፡ የደቡብ ፡ አፍሪካና ፡ የሞዛቢክ፡ ጉዳይ ፡ ራስ ፡ ምታት ፡ ሆናል ። ፍርድ ፡ ለመስጠት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ሀገሪቷ ፡ በተ ፈጥሮ ፡ ሀብታም ፡ ናት ። በማዕድናትዋ ፡ ተጠቅመው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሀብት ፡ አቋቁመዋል ። የተሟላ ፡ ኑሮ ፡ መሥርተው ፡ የሚኖሩባትን ፡ ሀገር ፡ ጥላችሁ፡ ውጡ ፡ የሚላቸው ፡ ጉሮሮዋቸውን ፡ አንቆ ፡ ጉድጓድ ፡ እንደሚጨምራቸው ፡ ይቈጥሩታል ።

በአፍሪካውያን ፡ በኩል ፡ የሀገራቸው ፡ ባለመብት ፡ ሆነው ፡ እን ደሌሎቹ ፡ ሀገራቸውን ፡ ራሳቸው ፡ መምራት ፡ አለባቸው ። ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ደም ፡ ሳይፈስ ፡ ተስማምተው ፡ ለመኖር ፡ ይችሉ ፡ ነበር ። አፍ ሪካውያን፡ ትዕግሥታቸው ፡ አልቆ፡ ከሰውነት ፡ ባሕርይ ፡ ወደ፡ አውሬ ነት ፡ ተለውጠው ፡ በኃይል ፡ መጠቀም ፡ ጀምረዋል ። ነጮቹም ፡ ኃይ ላቸውን ፡ እያጠነከሩ ፡ ስለሚከላከሉ ፡ ደም ፡ ሳይፈስ ፡ አይውልም ። ነገሩ ፡ እየተባባሰ ፤ አፍሪካውያንንም ፡ በበለጠ ፡ አስቆጥትዋል ። የሁ ሉም ፡ ኃይል ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የተባበረ ፡ እንደሆነ ፡ ወዮላቸው ፡ ነጮች ፤ ከዓለም ፡ የሚበልጠው ፡ ወገን ፡ አፍሪካውያንን ፡ ይደግፋል ። የሰው ፡ ኃይል ፡ የሚሠራበትና ፡ የማይሠራበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ያጠቃ ፡ የሚጠቃበት ፡ የተጠቃ ፡ የሚያጠቃበት ፡ ይደርሳል ። ዳዊት ፡ ጎልያ ድን ፡ ሊገጥመው ፡ ሲነሣ ፤ ኃይሉን ፡ የተማመነው ፡ ጎልያድ ፡ ዳዊትን ፡ እንደጨርቅ ፡ እንደሚጠቀልለው ፡ ተመክቶ ፡ ነበር ። አምላኩን ፡ የያዘ ፡ ዳዊት፡ በወንጭፍ ፡ድንጋይ፡ ዘርሮ፤ አንገቱን ፡ በገዛ—ሠይፉ፡ ቈረጠው።

ምድር ፡ ሰፊ ፡ ናት ፤ ሰዎች ፡ ተስማምተው ፡ ቢኖሩ ፡ ሁሉንም ፡ ትመግባቸው ፡ ነበር ። ምን ፡ ይሆናል ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ፍቅርን ፡ ሊገዛ ፡ ባለመቻሉ ፡ ሰላምን ፡ እያራቀ ፡ ሁከትን ፡ እየፈጠረ ፡ የራሱን ፡ መልክ ፡ ያጠፋል ።

በሮዴዥያ ፡ የሚኖሩ ፡ ወገኖቻችን ፡ በኃይላቸው ፡ አፍሪካውያንን ፡ ጨቁነው ፡ ቢይዙም ፡ ዘለቄታ ፡ ስለማይኖረው ፡ የራሳቸውን ፡ የመኖር ፡ መብት ፡ አስከብረው ፤ አፍሪካውያኑ ፡ ነፃ ፡ እንዲወጡ ፡ ሐሳባችንን ፡ ማካፈላችን ፡ አልቀረም ፡ ነበር ። ብዙዎች ፡ ሐሳቡን ፡ የመቀበል ፡ ፈቃድ ሲኖራቸው ፤ የሚበልጠው ፡ ወገን ፡ ባለመቀበሉ ፤ በዓለም ፡ ፊት ፡ የሚነበበው ፡ ነጮች ፡ በአፍሪካውያን ፡ ላይ ፡ የሚፈጽሙት ፡ ግፍ ፡ ነው ። የእንግሊዝ ፡ ቅኝ ፡ ሀገር ፡ የነበሩ ፡ ነፃነታቸውን ፡ በጠየቁ ፡ ጊዜ ፤ ይህ ፡ ትግል ፡ ተፈርቶ ፡ ነበር ። የአፍሪካውያኑ ፡ የነፃነት ፡ ፍላጎት ፡ ከቀን ፡ ወደቀን ፡ እየጨመረ ፡ ስለነፃነታቸው ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለመሠዋት ፡ የሚሰለፉት ፡ እየበዙ ፡ ሄዱ ። መሪዎቹ ፡ ቢታሠሩም ፡ ሌሎች ፡ እየተፈጠሩ ፡ የነጮቹ ፡ ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ፈጽሞ ፡ ከጥፋት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፡ ሰላማውያን ፡ የሆኑ ፡ ሕፃናትና ፡ ሽማግሌዎች ፡ በቤታቸው ፡ አደጋ ፡ እየተጣለባቸው ፡ የብዙ ፡ ነጮች ፡ ሕይወት ፡ አለፈ ።

ይህ ፡ ድርጊት ፡ እየተባባሰ ፡ በመሄዱ ፡ ለአፍሪካውያን ፡ ነፃነት ፡ ተሰጠ ። አፍሪካውያን ፡ ነፃነታቸውን ፡ አግኝተው ፡ ሀገራቸውን ፡ ለመምራት ፡ ሲበቁ ፡ በውስጣቸው ፡ ለሚኖሩ ፡ የመኖር ፡ መብታቸውን ፡ አልነፈግዋቸውም ። የሮዴዥያ ፡ ነጮች ፡ ትግልም ፡ ውሎ ፡ ከማደሩ ፡ በቀር ፡ ዘለቄታ ፡ የለውም ። የአፍሪካውያን ፡ ንቅናቄ ፡ እየጐለመሰ ፡ መሄዱ ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ከሁለቱም ፡ ወገን ፡ ደም ፡ ከሚፈስ ፡ ነጮች ፡ የመኖር ፡ መብታቸውን ፡ አስከብረው ፤ የአፍሪካውያኑን ፡ ነፃነት ፡ ቢያውቁ ፤ በዓለም ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ ያገኙ ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ተረኩልን ።

በዚህ ፡ ሐሳብ ፡ እንዴት ፡ አልተጠቀሙም ? ጽኑ ፡ የክርስትና ፡ እምነት ፡ ያላቸው ፡ ሐሳቡን ፡ ተቀብለውታል ። ሰላማዊ ፡ ኑሮ ፡ ካጡና ፡ ዘወትር ፡ ተሰልፈው ፡ የሚኖሩ ፡ ከሆነ ፡ የኑሮ ፡ ጣዕሙ ፡ ከምን ፡ ላይ ፡ ነው ? የሚያድጉ ፡ ሕፃናት ፤ የሚጦሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከተደበደቡ ፡ የመኖር ፡ ተስፋው ፡ ወዴት ፡ ላይ ፡ ነው ? ለነጮቹ ፡ የሚበጃቸው ፡ በፈሊጥ ፡ መተዳደሩ ፡ ነበር ፡ አሉን ።



የሕዝቡን ፡ አስተያየት ፡ ተነጋገርን ፤ የመንግሥታችሁ ፡ አስተሳሰብ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ይሆን ?

መንግሥት ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፤ ሕዝብ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። መንግሥቱ ፡ ከሕዝቡ ፡ የሚሰነዘረውን ፡ አስተያየት ፡ አያቃልለውም ። በሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ የማይጠቀም ፡ መንግሥት ፡ እድሜው ፡ አጭር ፡ ነው ። መንግሥታችን ፡ የዓለምን ፡ ዝንባሌ ፡ አተኩሮ ፡ ይመለከታል ። በዘር ፡ ልዩነት ፡ የሚደረገውን ፡ አድልዎ ፡ ዓለም ፡ ዕንደጠላው ፡ መንግሥታችንም ፡ ይጠላዋል። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ሰፊ ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ምኞት ፤ ከኛም ፡ ከነርሱም ፡ ቢኖር ፡ ለመቆየት ፡ ጊዜ ፡ ስላጠረን ፡ በሉ ፡ ጉዞዋችሁ ፡ የተቃና ፡ ይሁን ፡ ብለውን ፡ ተሰነባበትን ።

ልጃችን ፡ በአሜሪካን ፡ እንዲቀበለን ፡ ቴሌግራም ፡ አደረግን ፤ ከለንደን ፡ ወደ ፡ አሜሪካን ፡ በጃምቦ ፡ ጄት ፡ አውሮፕላን ፡ በረርን ። በአየር ፡ ላይ ፡ እንዳለን ፡ ጥበብን ፡ ለገለጸ ፡ ፈጣሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ ምስጋና ፡ ይድረሰው ፡ በጥበብ ፡ የተራቀቀው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ እንዴት ፡ በሰላምና ፡ በፍቅር ፡ ተሳስቦ ፡ መኖር ፡ አቃተው ? አለች ፡ ፀሐይ ።

ፍቅር ፡ የፈጣሬ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ መገናኛ ፡ መሰላል ፡ ናት ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቢጠቀምባት ፡ ዓለም ፡ እሾኽና ፡ አሜከላ ፡ አታበቅልም ፡ ነበር ፡ ብዬ ፡ ስመልስላት ፤ አውሮፕላኑ ፡ ፎቅና ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ በመሆኑ ፤ ከምድር ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ ወደፎቅ ፡ ከፎቁ ፡ ያለው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ቤቱ ፡ ሲዝናና ፡ ካለንበት ፡ በመንቀሳቀስ ፡ ተዝናናን ።

የአየሩ ፡ ጉዞ ፡ ተቋረጠ ፡ ቦስቶን ፡ አውሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ደረስን ። ሻንጣችንን ፡ ወደምንረከብበት ፡ ስናመራ ፡ ልጃችን ፡ ከባልንጀሮቹ ፡ ጋር ፡ ሆኖ ፡ ተቀብሎን ፡ ወደ ፡ ሆቴል ፡ ወሰደን ።

ከልጃችን ፡ ጋር ፡ ለጥቂት ፡ ደቂቃዎች ፡ የናፍቆት ፡ ጭውውት ፡ አደረግን ። ያዘጋጀልንን ፡ የጉብኝት ፡ መግለጫ ፡ አነበበልን ። የቦስቶንን ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ ጐበኘን ። ልጃችን ፡ በብራንዳይ ፡ ዩኒቨርስቲ ፡ የሚማር ፡ ስለሆነ ፤ ከመምህራኑና ፡ ከተማሪዎቹ ፡ ጋር ፡ በዩኒቨርስቲው ፡ ምሳ ፡ ተጋበዝን ። ከተማውንና ፡ የከተማውን ፡ አካባቢ ፡ ከጐበኘን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኒውዮርክ ፡ ጉዞዋችንን ፡ በመኪና ፡ ቀጠልን ።

የሕዝቡን ፡ ኑሮና ፡ የሀገሩን ፡ አቀማመጥ ፡ እንስሳቱ ፡ የሚውሉበትንና ፡ ይዞታቸውን ፡ እየተመለከትን ፡ ኒውዮርክ ፡ ከተማ ፡ ደረስን ። በከተማው ፡ የሚታየው ፡ የሕዝብ ፡ ንቅናቄ ፡ የተሽከርካሪው ፡ ትርም

ስምስ ፤ የሕንፃዎቹ ፣ መቀራረብና ፣ ርዝመታቸው ፣ አየሩን ፣ የዘጉት፣ ስለሆነ ፤ ደካማ ፣ ሰው ፣ ትንፋሽ ፣ ያጥረዋል ።

ፀሐይ፣ በአየችውና፣ በምታየው፣ ከመደነቋ ፣ የተነሣ ፣ ቀስ ፣ በቀስ፣ የመፍዘዝና ፣ የመድከም፣ ምልክት ፣ ማሳየት፣ ጀመረች ። ሞገሴ ፣ እማማ ፣ አመመሽ ፣ እንዴ ፣ እያለ ፣ ተጨነቀ ። ሳቅ ፣ እያለች ፣ አጥጋቢ ፣ መልስ ፣ አለመስጠትዋ ፣ ቢደክማት ፣ ይሆናል ፣ ብሎ ፣ ወደ ፣ ሆቴል ፣ ተመለስን ። በሚቀጥለው ፣ ቀን ፣ ከተማውን ፣ እየተዘዋወርን ፣ ስንመለከት ፣ ከጥቁሮች ፣ ሰፈር ፣ ስንደርስ ፣ ይዞታው ፣ ተለወጠብን ። አለባበሳቸውና ፣ የጠጉራቸው ፣ ሁኔታ ፣ ለእንግዳ ፣ ደራሽ ፣ የሚያስፈራ ፣ ነው ።

አፍሪካውያን ፣ ሁሉ ፣ በአለባበስና ፣ በጠጉራቸው ፣ ስለተመሳሰሉ ፣ መለየት ፣ ያስቸግራል ። ልጃችን ፣ ኢትዮጵያውያንን ፣ እየለየ ፣ አሳየን ። በሀገር ፣ ልጅነት ፣ ልናነጋግራቸው ፣ ስንፈልግ ፣ በቸልተኝነት ፣ አለፉን ።

ኢትዮጵያውያን ፣ በውጭ ፣ ሀገር ፣ ሲገናኙ ፣ ተፈላልገው ፣ ይነጋገራሉ ፤ ይግባበዛሉ ፣ ይባል ፣ ነበር ።ከሌሎች ፣ የሚለዩበት ፣ ባይኖርም ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ መሆናቸውን ፣ ስትነግረን ፣ ልናነጋግራቸው ፣ ፈገግታ፣ ስናሳያቸው ፣ ዝም ፣ እያሉን ፣ አለፉ ። ምን ፣ ይሆን ? ከናንተ ፣ ጋር ፣ የተያያችሁት ፣ ዛሬ ፣ ነው ፣ አልነው ? ብዙ ፣ ጊዜ ፣ እየተያየን ፣ እንተላለፋለን ፣ እንጂ ፣ ተነጋግረን ፣ አናውቅም ። ይልቁንም ፣ የዓለም ፣ መንግሥታት ፣ እየተሰበሰቡ ፣ ስለዓለም ፣ ሰላም ፣ የሚነጋገሩበትን ፣ ሕንፃ ፣ ታያላችሁ ፤ የዓመቱ ፣ የስብሰባ ፣ ጊዜ ፣ ስለሆነ ፤ በአዳራሹ ፣ ተገኝተን ፣ እናዳምጣለን ፣ አለን ።

በዓለም ፣ መንግሥታት ፣ ማኅበር ፣ አዳራሽ ፣ በደረስን ፣ ጊዜ ፤ ከኮሚኒስት ፣ ሀገሮች ፣ የአንዱ ፣ ተናጋሪ ፣ ተራ ፣ ነበር ። መልእክተኛው ፣ ወደ ፣ መናገሪያው ፣ ሲያመራ ፣ ጭብጨባው ፣ አስተጋባ ። ስለቅኝ ፣ ገዥዎችና ፣ ነፃ ፣ ስላልወጡ ፣ አፍሪካውያን ፤ ይልቁንም ፣ በሮዴዥያና ፣ በደቡብ ፣ አፍሪካ ፣ በሞዛቢክ ፣ የሚፈጸመውን ፣ የዘር ፣ ልዩነት ፣ ሲናገር ፤ ጉዳዩ ፣ የሚመለከታቸው ፣ ከአዳራሹ ፣ ወጡ ።

በንግግሩ ፣ ዘይቤ ፣ አዳማጩ ፣ ሳይሰለች ፣ ንግግሩን ፣ ደመደመ ። የሚቀጥለው ፣ ከታናናሾች ፣ መንግሥታት ፣ አንዱ ፣ መሆኑ ፣ ተነግሮ ፣



ዕረፍት ፣ ሆነ። ንግግሩ ፣ ሲቀጥል ፣ ያድማጩ ፣ ብዛት ፣ ተቀነሰ። ንግግሩ ፣ ሳያልቅ ፣ እየወጣም ፣ የሚሄድ ፣ ነበር ። ንግግሩ ፣ ተፈጽሞ ፣ ስንዝናና ፣ ከአንድ ፣ አፍሪካዊ ፣ ጋር ፣ ወግ ፣ ጀመርን ። የኮሚኒስት ፣ ሀገሮች ፣ በተለይ ፣ ታላላቆቹ ፣ በሚናገሩበት ፣ ወቅት ፣ አዳማጩ ፣ አዳራሹን ፣ ሞልቶት ፣ ነበር ። ለምን ፣ ይሆን ? ብለን ፣ ጠየቅን ።

የቅኝ ፣ አገዛዝ ፣ ያልበቃቸውን ፣ ኢምፔርያሊዝም ፣ በዓለም ፣ ፊት ፣ አጋልጠው ፣ ስለሚናገሩ ፤ ንግግራቸው ፣ ተደማጭነት ፣ አለው ፣ አለን ። በቅኝ ፣ አገዛዝ ፣ የኖሩ ፣ ኢምፔሪያሊዝም ፣ በንግግር ፣ ኃይለ ፣ ቃል ፣ የያዙትን ፣ ለቀው ፣ የሚወጡ ፣ ይመስልኻል ?

አዬ ፤ በሰብአዊ ፣ ፍጡራን ፣ ላይ ፣ በዘር ፣ ልዩነት ፣ ግፍ ፣ የሚሠሩ ፣ የያዙትን ፣ ሀገር ፣ ለቀው ፣ የሚወጡ ፣ በደም ፣ ነው ። በውርደቱና ፣ በግፉ ፣ የተመረሩ ፣ አፍሪካውያን ፣ ደማቸውን ፣ ለማፍሰስ ፣ ቆርጠው ፣ ከተነሡ ፣ የዘር ፣ ልዩነትንና ፣ የቅኝ ፣ ግዛትን ፣ ማጥፋት ፣ ይችላሉ ።

ብዙ ፣ የአፍሪካ ፣ ሀገሮች ፣ ነፃ ፣ ወጥተዋል ። ሀገራቸውን ፣ ነፃ ፣ ያወጡት ፣ በደማቸው ፣ ስለሆነ ፤ ነፃ ፣ ያልወጡ ፣ ሀገሮች ፣ የነሱን ፣ ዓላማ ፣ ከተከተሉ ፣ ነፃ ፣ ይወጣሉ ፣ አለን ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ የማኅበሩን ፣ የውስጥ ፣ ድርጅትና ፣ አካባቢውን ፣ ሁሉ ፣ ዐይተን ፣ ወደማረፊያችን ፣ ተመለስን ፤ ከልጃችን ፣ ጋር ፣ ራታችንን ፣ እየተመገብን ፣ ስንነጋገር ፣ በትምህርትና ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ምክንያት ፣ በዚሁ ፣ ሀገር ፣ ከሚታዩት ፣ አፍሪካውያን ፣ የሚበልጡት ፣ አለባበሳቸው ፣ ጠጉራቸውና ፣ ጠቅላላ ፣ ሁኔታቸው፣ አልገባኝም። ሴትና ፣ ወንዱን ፣ መለየት ፣ ያቅታል ። በሠለጠነ ፣ ከተማና ፣ በሠለጠነ፣ ሕዝብ፣ መካከል ፣ እንደዚህ ፣ መሆኑ ፣ ትክክል ፣ አይመስለኝም፣ አለች ፣ ፀሐይ፣ ለልጅዋ ፣ በመስጋት ።

አዬ ፣ እማማ ፤ ያየሽው ፣ ጥቂቱን ፣ ነው ። ኧረ ፣ ወደ ፣ ውስጥ ፣ ጠለቅ ፣ ብለሽ ፣ ብታዪ ፤ የባሰ ፣ አለ ። ሰው ፣ ለራሱ ፣ ደስ ፣ ካለው ፣ የፈለገውን ፣ ቢያደርግ ፣ ነፃ ፣ ነው ። ከሀገራችን ፣ ጋር ፣ ስታስተያዩት ፣ መልካም ፣ ነው ፣ ብላችሁ ፣ የምትቀበሉት ፣ አይገኝም። የሰው ፣ ልጅ፣ ተመራምሮ ፣ የሠራቸው ፣ ሲታዩ ፣ ትልቅነቱን ፣ ይመሰክራሉ ። በሌላው ፣ በኩል ፣ ደግሞ ፣ ከሰው ፣ ባሕርይ ፣ ወደ ፣ እንስሳነት ፣ ተለውጠዋል ፣ ከሚያሰኝ ፣ ደረጃ ፣ ላይ ፣ ደርሰዋል ፣ አለ ፣ ሞገሴ ።

በኒውዮርክ ፡ የምናደርገውን ፡ ጉብኝት ፡ ጨርሰን ፡ ወደዋሽንግተን ፡ ሄድን ። ለሀገራቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ ለሠሩ ፡ የቆመውን ፡ የነ አብርሃም ፡ ሊንከንን ፡ መታሰቢያ ፡ ጐበኘን ። ተልእኳቸውን ፡ ለሀገራቸው ፡ ሲፈጽሙ ፡ የሞቱ ፡ የተቀበሩበትን ፡ የመቃብር ፡ ሥፍራ ፡ ተመለከትን ። ይልቁንም ፡ በከተማው ፡ አካባቢ ፡ የሚገኘውን ፡ ጫካ፡ ባየን፡ ጊዜ ፡ በይዞታው ፡ ተደነቅን ። ወደማረፊያችን ፡ ስንመለስ ፡ የሙታንን ፡ ከተማ ፡ መቃብር ፡ ጐበኘን ።

አፈር ፡ የተመለሰባቸውና ፡ ድንጋይ ፡ የተቆለለባቸው ፡ ትላንት ፡ እንደእኛ ፡ ነበሩ ። እኛም ፡ ነገ ፡ እንደነሱ ፡ ነን ። ይህን ፡ በማመዛዘን ፡ ለሙታን ፡ ከተማ ፡ ክብር ፡ የሰጡ ፡ ሊመሰገኑ ፡ ይገባል ፡ እንዳለች ፡ ፀሐይ ፡ እማማ ፡ በቁሙ ፡ ያላማረበት ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ያምርበታል ፡ ብለሽ ፡ አትጓጊ ። ለሕይወታዊ ፡ ኑሮ ፡ መልካም ፡ አስተሳሰብ ፡ ካለ ፡ ለሙታን ፡ ከተማ ፡ ይዞታ፡ ማሰብ ፡ ይኖራል ፡ የሁሉም ፡ መተላለፊያ ፡ መንገድ ፡ ነውና ፡ አለ ፡ ሞገሴ ።

የተደነቃችሁት ፡ በሙታን ፡ ከተማ ፡ ይዞታ ፡ ነው ። የጫካው ፡ ይዞታ ፡ በበለጠ ፡ አያስደንቅም ? ለሕዝቡ ፡ የዕረፍት ፡ ጊዜ ፡ ማሳለፊያ፡ እንዲሆን፡ ውስጡ ፡ አምሮ ፡ የተደላደለ ፡ ነው ። መንግሥቱ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሲያስብ ፤ ሕዝቡም ፡ ጥቅሙን ፡ በማወቁ ፡ አንድዋን፡ ቅጠል ፡ እንኳን ፡ ቅንጥብ ፡ አያደርግም ። በተባበረው ፡ ሐሳባቸው ፡ ቀናሁ ፡ እያልኩ ፡ ስሜቴን ፡ ገለጽኩላቸው ።

ቀጥለን ፡ «ኦ ፡ ኢ.ይ ፡ ሲ ፡» የተባለውን ፡ ድርጅት ፡ ጐበኘን ፡ «ኦ ፡ ኢ.ይ ፡ ሲ ፡» ማለት ፡ ምን ፡ ይሆን ? በቀለም ፡ ልዩነት ፡ በጥቁሮች ፡ ላይ ፡ በሚደርሰው ፡ ጭቆና ፡ ድርጅቱን ፡ የመሠረቱት ፡ ለጭቆናው ፡ ማቃለያ ፡ ይሆናል ፡ ብለው ፡ ያቋቋሙት ፡ ድርጅት ፡ ነው ፡ አሉን ። በመደነቅ ፡ ወይም ፡ በመገረም ፡ የተቋቋመው ፡ ድርጅት ፡ በቀለም ፡ ልዩነት ፡ ጭቆና ፡ የሚደርስባቸውን ፡ ጥቁሮች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሞያ ፡ እያሠለጠነ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ ያሠማራል ። በችሎታ ፡ ከነጮች ፡ ካላነሱ ፡ መብታቸው ፡ እንዲጠበቅ ፡ ይከራከራል ።

ከዚሁ ፡ አከታትለን ፡ ኰንግሬሱንና ፡ የሃይማኖት ፡ ድርጅቶችን ፡ ጐበኘን ። በተፈጥሮ ፡ ሁሉም ፡ ሰው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ከሰውም ፡ ሰው ፡ የሚለየው ፡ በሥራው ፡ ነው ፡ እየተባባልን ፤ ወደማረፊያችን ፡ ተመለስን ።



ዋሽንግተንን ፡ ለቀን ፡ ወደላንካስተር ፡ ሄደን ፡ አሚሽ ፡ የተባለውን፡ ድርጅት ፡ ጐበኘን ። በኤሌክትሪክ ፡ መብራት ፡ በቧንቧ ፡ ውሀ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘመናዊ ፡ መሣሪያዎች ፡ አንጠቀምም ፡ ብለው ፡ በፋኖስ፤ በጕድጓድ ፡ ውሀ ፤ በቀንድና ፡ በጋማ ፡ ከብት ፡ ብቻ ፡ እየተረዱ ፡ በቀላል ፡ ይኖራሉ። ገንዘብ ፡ ከማንም፡ አይሹም ። «ሠርተህ፡ በወዝህ፡ ብላ፡» የተባለውን ፡ ትእዛዝ ፡ በመፈጸም ፡ በጋማ ፡ ከብት ፡ እያረሱ ፡ ይኖራሉ። ልጆቻቸው ፡ ከስምንተኛ ፡ ክፍል ፡ በላይ ፡ አይማሩም ። የሰው፡ ልጅ፡ ብዙ፡ ከዐወቀና ፡ በሳይንስ ፡ ካመነ፡ በልማድ ፡ ይመሻል ፡ ይነጋል፡ ብሎ፡ ያምናል ፡ እንጂ ፡ ፈጣሪ ፡ አለኝ ፡ አይልም ፡ የማለት ፡ አስተሳሰብ ፡ አላቸው ። በዚሁ ፡ ድርጅት ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ የሚኖሩት ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ናቸው ።

የሀገሩን ፡ አቀማመጥና ፡ ልማቱን ፡ እያየን ፡ ስንጓዝ ፡ ልባችን ፡ አሁንም ፡ የተነካው ፡ በጫካው ፡ ይዞታ ፡ ነበር ። ዛፎቹን ፡ አተኩረን ፡ ስንመለከት ፡ ጠማማ ፡ ዛፍ ፡ በመካከላቸው ፡ የለም ። ይህን ፡ እያየን ፡ ፊሌዴልፊያ ፡ ከተማ ፡ ደረስን ። ከተማውን ፡ ከጐበኘን ፡ በኋላ ፡ ጉዞዋችንን ፡ ቀጥለን ፡ ችካጎ ፡ ከተማ ፡ ገባን ።

በችካጎ ፡ ከተማ ፡ ትልቁን፡ የሳይንስና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሙዚዬም፡ ጐብኝተን ፡ ከሙዚዬሙ ፡ ዲሬክተርና ፡ ከአባሎቹ ፡ ጋር ፡ ምሳ ፡ ተጋበዝን ። ሙዚዬሙ ፡ እጅግ ፡ ትልቅ ፡ ከመሆኑ ፡ ጋር ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሳይንስና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ መሣሪያዎች ፡ ሲታዩበት ፡ ወደጨረቃ ፡ የምትመጥቀውን ፡ አፖሎ ፡ ዓይነት ፡ አየን ። እንደዚሁም ፡ ቴክኒካል ፡ እንስቲቲውት ፡ ጐበኘን ። ከእንስቲቲውቱ ፡ በሦስት ፡ ወር ፤ በስድስት፡ወር፤ በዘጠኝ ፡ ወር ፡ እየተመረቁ ፡ የሚወጡት ፡ ያለችግር ፡ ሥራ ፡ መያዝ ፡ ይችላሉ ።

ጥቁር ፡ አሜሪካኖች ፡ በቤተ፡ ክርስቲያናቸው፡ ጸሎት፡ እያደረጉ ፤ ብሶታቸውን ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ቀን ፡ በመካከላቸው ፡ ተገኘን ። የመዝሙሩ ፡ ስሜት ፡ የንግግራቸው ፡ ጥልቀት ፡ ልባችንን ፡ ነካው ። ተናጋሪው ፡ የራሳቸውን ፡ ጉድለት ፡ ጭምር ፡ ገልጾ ፡ ኀብረታቸውን ፡ አጠንክረው ፡ ክብራቸውን ፡ መጠበቅ ፡ እንዳለባቸው ፡ ሲናገር ፡ ልብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ።

በጸሎታቸው ፡ ላይ ፡ «የእጅህ ፡ ፍጥረቶች፡ አይደለንም ? ሰዎች፡ አይደላችሁም ፡ ብለው ፡ ሲጠየቁን ፡ እንዴት ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ታያቸዋለህ ? » እያለ ፡ በመናገሩ ፡ የሚያለቅሱ ፡ ነበሩ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከችካጎ ፡ ወደ ፡ አይዋ ፡ ሄድን ፡፡ ከከተማው ፡ በኻያ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ አማና ፡ በተባለው ፡ ቀበሌ ፡ የሚካሄደውን፡ የርሻ ፡ ልማት ፡ ዐየን ፡፡ ይህ ፡ ከሥራችን ፡ ጋር ፡ የሚመሳሰለው፡ የርሻ፡ ሥራ ፡ በልማትም ፡ ሆነ፡ በይዞታ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ በመሆኑ ፡ የበለጠ ፡ ደስ ፡ አለን ፡፡

ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ በመኪና ፡ አዞሮ ፡ ሲያሳየን ፡ ሁለት ፡ ሰዓት ፡ ፈጀ ፡፡ በርሻው ፡ ልማት ፡ ድርጅት ፡ የሚካሄዱ ፡ የከብት ፡ ርባታ ፤ የመጠጥ ፡ ፋብሪካ ፤ የእንጨት ፡ ፋብሪካ ፤ የጨርቃ ፡ ጨርቅ ፡ ፋብሪካ ፤ ትምህርት ፡ ቤት ፤ ሆቴል ፤ ሆስፒታል ፡ ይገኛሉ ፡፡

ልማቱ ፡ በኅብረት ፡ የተቋቋመ ፡ ነው ፤ የመጀመሪያዎቹ ፡ መሥራቾች ፡ ጀርመኖች ፡ ሆነው ፡ የሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡፡ በጀርመን ፡ ሃይማኖትን ፡ ለማስፋፋት ፡ ባለመቻላቸው ፡ እንደአውሮፓ ፡ ዘመን ፡ አቈጣጠር ፡ በ፲፰፻፶፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ አሜሪካን ፡ መጥተው ፡ በኒውዮርክ ፡ አቅራቢያ ፡ ባፋሎ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ኤከርስ ፡ መሬት ፡ ከሬድ ፡ ኢንድያንስ ፡ ገዝተው ፡ ሥራውን ፡ አቋቁመው ፡ ነበር ፡፡

የኒውዮርክ ፡ ከተማ ፡ እየተስፋፋ ፡ ገበሬዎቹ ፡ አሉበት ፡ ከመድረሱም ፡ በላይ ፤ ወገኖቻቸውም ፡ በየጊዜው ፡ እየመጡ ፡ ቍጥራቸው ፡ በመብዛቱ ፡ የኒውዮርክ ፡ ከተማ ፡ አሁን ፡ ከሚታይበት፡ ደረጃ፡ ደረሰ ፡ ብሎ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጁ ፡ ነገረን ፡፡

ከተቋቋሙት ፡ የልማት ፡ ሥራዎች ፡ የበለጠ፡ ጥቅም፡ የሚገኘው፡ ከማንኛውም ፡ ነው ? ፡ ከእርሻ ፡ የሚገኘው ፡ አዝርዕትና ፡ ዕፀዋት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚጠበቅበትን ፡ ምርት ፡ አይሰጥም ፡፡

ከርሻ ፡ የሚገኝ ፡ ገቢ ፡ ሁሉንም ፡ አይሸፍንም ፡ ማለት ፡ ነው ? በኛ ፡ ዓይነት ፡ ለተቋቋመ ፡ የልማት ፡ ድርጅት ፡ አያወጣም ፡፡ ባለመብቶቹ ፡ ከአራት ፡ መቶ ፡ የማያንሱ ፡ ናቸው ፡ በአዝመራው ፡ ላይ ፡ ያልተጠበቀ ፡ ጥፋት ፡ ሲደርስ ፡ በሌላ ፡ ካልተደገፈ ፡ ድርጅቱ ፡ ይፈርሳል ፡ ብሎ ፡ ስለልማቱ ፡ በየጊዜው ፡ የተጻፉ ፡ መጽሔቶች ፡ ሰጥቶን ፡ ወደሚኒሶታ ፡ ሄድን ፡፡

ከከተማው ፡ በመቶ ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ ገበሬዎች ፡ በኅብረት ፡ ያቋቋሙትን ፡ ያይብ ፡ ፋብሪካ ፡ አየን ፡፡ ፋብሪካው ፡ በአማካይ ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በአካባቢው ፡ ከሚኖሩ ፡ ገበሬዎች ፡ ወተት ፡ እየሰበሰበ ፡



ይሠራል ፡፡ የፋብሪካው ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ምሳ ፡ ጋበዘን ፡፡ የወተቱ ፡ ያይቡና ፡ የቅቤው ፡ ጣዕም ፡ ሌላ ፡ ነው፡፡ በስድስት ፡ በስድስት ፡ ወር ፡ ለባለጥቅሞቹ ፡ ገበሬዎቹ ፡ የገቢና ፡ የወጪ ፡ ሂሣብ ፡ ይሰጣል ፡፡

የሚኒሶታ ፡ ጕብኝታችን ፡ ተጠቃሎ ፡ ወደሞንታና ፡ ሄድን ፡፡ ሞንታና ፡ የታወቀ ፡ የገበሬ ፡ ሀገር ፡ ነው ፡፡ ከከተማው ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ማይል ፡ ርቀት ፡ ወደሚገኘው ፡ ሐትራይት ፡ ኮሚኒቲ፡ ሄደን ፡ ጐበኘን፡፡ በዚህ ፡ የርሻ ፡ ድርጅት ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ቤተሰቦች ፡ ተባብረው ፡ ይሠራሉ ፡፡ የአሥራ ፡ ሁለት ፡ ቤተሰቦች ፡ መሪ ፡ በዕድሜ ፡ ከሁሉም ፡ የላቀ ፡ ነው ፡፡ እያዞረ ፡ አስጐበኘን ፡ በከብት ፡ ርባታም፡ ሆነ ፡ በሌላው የልማት ፡ ሥራቸው ፡ የተሟላ ፡ አቅዋም ፡ አላቸው ፡፡ የውስጥ ፡ አስተዳደራቸውን ፡ ሲያስረዳን ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ቤተሰቦች፡ በመኝታ፡ ብቻ፡ በእያንዳንዳቸው ፡ ቤት ፡ ከማደራጀታቸው፡ በቀር ፡ ባንድ ፡ ይሠራሉ፡፡ በአንድ ፡ ይመገባሉ ፤ ባንድ ፡ ይጸልያሉ ፤ ኑሮዋቸው ፡ በማኅበራዊ ፡ አቅዋም ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡፡ ጕብኝታችንን ፡ ስንጨርስ ፡ ከነርሱ ፡ ጋር ፡ ምሳ ፡ ተጋበዝን ፡፡ የምግቡ ፡ አቀራረብ ፡ በገፍ ፡ ነበር ፡፡ መጠጡም ፡ ወተት ፡ ነበር ፡፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ቤተሰቦች ፡ ከነልጆቻቸው ፡ አምሳ ፡ ስለሆኑ ፡ በፍቅር ፡ እየተሳሰቡ ፡ በገበታ ፡ ቤቱ ፡ የሚያሳዩት ፡ መዝናናት ፡ ደስ ፡ ይል ፡ ነበር ፡፡ ከምሳ ፡ በኋላ ፡ መኝታ ፡ ቤታቸውን ፡ ጐበኘን ፡፡ ጽዳቱ ፡ በሚገባ ፡ የተጠበቀ ፡ ነው ፡፡ በዘመናዊ ፡ ልዩ ልዩ ፡ የመኝታ ፡ ቤት ፡ ዕቃዎች ፡ የተዋበም ፡ ባይሆን ፡ በይዞታው ፡ የደስ ፡ ደስ ፡ አለው ፡፡

ለሰው ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ ያስፈልገዋል ፡፡ ተባብሮ ፡ ሠርቶ ፡ ያገኘውን ፡ አብሮ ፡ ከተመገበ ፤ ካልተራበና ፡ ካልታረዘ ፤ ጤናው ፡ ሲታወክ ፡ በሕክምና ፡ የሚረዳበት፡ ገንዘብ ፡ ካለው፤ የልጆቹን ፡ አበባ ፡ ካየ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እንስሳት ፡ አርብቶ ፡ ከተጠቀመባቸው ፤ ከነገር፡ ርቆ፡ በወዙ፡ ሠርቶ ፡ በሰላም ፡ ከኖረ ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ለሰው ፡ ምን ፡ ጸጋ ፡ ይሰጠዋል፤ እናመሰግነዋለን ፡፡ በከተማ ፡ የሚኖሩ ፡ ቤታቸውን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቁሳቁስ ፡ አስጊጠው ፡ እናያለን ፡፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አለው ? ይህን ፡ ያጡ ፡ ይኖራሉ ፡፡ በትርፍ ፡ ነገር ፡ ቤትን ፡ ከማጣበብ ፡ ምንም ፡ ለሌላቸው ፡ አካፍሎ ፡ መኖር ፡ ይገባል ፡ ብዬ ፡ የማምን ፡ ነኝ ፡፡ ይህ ፡ ልጅ ፡ ኻያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ሲኖረው ፤ ሴቶቹ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ አላቸው ፡፡ በእግራችን ፡ የሚተኩት ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ፡፡ በኛ ፡ እምነት ፡

ሂዱ ፣ እንላቸውም ። ሁሉንም ፣ እንዲያዩ ፣ ብለን ፣ ነፃ ፣ አድርገናቸው፣ ወደ ፣ ልዩ ፣ ልዩ ፣ ታላላቅ ፣ ከተማ ፣ እየሄዱ ፣ ያያሉ ፤ ከዓለም ፣ ጋር ፣ ዓለማውያን ፣ ሆነው ፣ ይሰናበታሉ ። በገንዘብም፣ በኩል፣ ችግር ፣ የለም፤ እንሰጣቸዋለን። ሁሉንም ፣ ካዩ ፣ በኋላ ፤ የኛ ፣ አስተሳሰብና ፣ አካሄድ፣ ትክክለኛ ፣ መስሎ፣ ቢታያቸው ፣ አምነው ፣ ይከተሉ ፤ ካልመሰላቸው፣ የሚመስላቸውን ፣ ለመያዝ ፣ ምርጫው ፣ የራሳቸው ፣ ነው ፣ አለ ፣ ሽማ ግሌው ።

ሁሉንም ፣ አይተህ፣ የወደፊት፣ ዕድልህን፣ እንድትወስን ፣ ሆኗል። ዝንባሌህ ፣ ወዴት ፣ ነው ? ብለን፣ ጠየቅነው፣ ልጁን ። በማየት ፣ ብቻ ፣ ሳይሆን ፣ በሥራም ፣ ሞክረነዋል ። ወላጆቻችን ፣ የተከታተሉትን ፣ ዓላማ ፣ የማንከታተልበት ፣ የተጨበጠ ፣ ነገር ፣ አላገኘንም ፣ አለን ። ቀጥሎ ፣ ያየነው ፣ ተመሳሳይ ፣ እየሆነ ፣ አዲስ ፣ ነገር ፣ ባለማየታችን ፣ የሀገሩን ፣ ልማት ፣ ብቻ ፣ እየተመለከትን ፣ ሳንፍራንሲስኮ ፣ ከተማ ፣ ገባን ። ከዚያም ፣ ወደሎስ ፣ አንጀለስ ፣ ተጉዘን ፣ ታሪካዊ ፣ የሆነውን ፣ ዲዝላንድን ፣ አየን ። በዲዝላንድ ፣ የሚታየው፣ ከማስደነቅ፣ አልፎ፣ የረ ቀቀ ፣ ነው ።

ከዚህ ፣ በኋላ ፣ በመጣንባቸው ፣ መንገዶች ፣ ሳይሆን ፣ ያላየናቸ ውን ፣ ዋና ፣ ዋናዎቹን ፣ ከተሞች ፣ አሪዞንና ፣ ቴክሳስን ፤ ሚሲሲፒን ፤ ጆርጅያን ፣ ሰሜናዊ ፣ ካሮሊኒን ፣ ዐየን ። ሰሜናዊ ፣ ካሮሊኒያ ፣ ዱክ ፣ ዩኒቨርስቲን ፣ በአየን ፣ ጊዜ ፣ ዩኒቨርስቲውን ፣ አቋቁሞ ፣ ንብረቱን ፣ ለዚህ ፣ ለተቀደሰ ፣ ዓላማ ፣ ያደረገውን ፣ ሰው ፣ አደነቅነው። በዩኒቨርስ ቲው ፣ ግቢ ፣ በአማካይ ፣ ሥፍራ ፣ ዘመናዊ ፣ ቤተ፣ ክርስቲያን፣ ይገኛል። በቤተ ፣ ክርስቲያኑ ፣ ውስጥ ፣ ዩኒቨርስቲውን ፣ ያቋቋመው ፣ መቃብር ፣ ከነቤተሰቦቹ ፣ ይታያል ። ታሪካዊ ፣ የሆነ ፣ ሥራ ፣ አቋቁሞ ፣ እስከ ፣ ዓለም ፣ ፍጻሜ ፣ ስሙን ፣ ለታሪክ ፣ አቆይቶ ፣ የሚያልፍ ፣ ብፁዕ ፣ ነው። ሰው ፣ ወጥቶ ፣ ወርዶ ፣ ያገኘውን ፣ ለልጁ ፣ ማስተላለፍ ፣ የቆየ ፣ ወግ ፣ ነው ። አንዱ ፣ ወዙን ፣ አፍስሶ ፣ በድካም ፣ ያቆየው ፤ ያለ ፣ ድካም ፣ ላገ ኘው ፣ ስለማይሰማው ፣ ይሸጠዋል ፤ ይለውጠዋል ፤ እያልን ፣ ዋሽን ግተን ፣ ዲ . ሲ . ገባን ።

በዋሽንግተን ፣ አምስት ፣ ቀናት ፣ ዕረፍት ፣ አደረግን ፤ በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ከልጃችን ፣ ጋር ፣ ረጋ ፣ ብለን ፣ ተነጋገርን ። ባየሁት ፣ ሁሉ ፣ የተ



ሰማኝን ፣ ደስታ ፣ የምገልጽበት ፣ ቃል ፣ ያጥረኛል ፤ ማየት ፣ ብርሃን ፣ ነው ፤ አለማየት ፣ ጨለማ ፣ ነው ፤ ሰው ፣ ካላየ ፣ ወዴት ፣ ላይ ፣ እንዳለ፣ ራሱን ፣ ሊያውቅ ፣ አይችልም ። እስካሁን ፣ ባየነው ፣ ልቤ ፣ ተነክቷል ። የቀረን ፣ የሚደሰቱበትን ፣ ማየት ፣ ብቻ ፣ ነው ፤ አለች ፣ ፀሐይ ።

እማማ ፣ ሳታዩ ፣ የምትሄዱ ፣ መሰለሽ ፣ እዩው ፣ በማስታወሻ ፣ ይዠዋለሁ ። ቁም ፣ ነገሩን ፣ ካያችሁ ፣ በኋላ ፤ ቀጥላችሁ ፣ ብታይውት ይሻላል ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ ወደኋላ ፣ ያስቀረሁት ። የምታዩትም ፣ በኒውዮ ርክ ፣ ከተማ ፣ ነው ።

እስካሁን ፣ ያያችሁት ፣ በጣም ፣ ትንሽ ፣ ነው ። በትምህርት ፣ ዓመ ታትን ፣ በማየት ፣ ወራትን ፣ የቈጠሩ ፣ የራሳቸውን ፣ ደስታ ፣ እንጂ ፤ ከዚህ ፣ ከገበዩት ፣ የመንፈስ ፣ ሀብት ፣ ወደ ፣ ሀገራቸው ፣ ሲመለሱ ፣ ላላዩ ፣ ያበረከቱ ፣ ያሉ ፣ አይመስለኝም ። እንዲያውም ፣ ራሳቸውን ፣ ወዳድ ፣ ሆነዋል ፣ ይባላል ። ከዚህ ፣ ያሉት ፣ ሲሰሙ ፣ ብንሄድ ፣ እንደ ነሱ ፣ ሆነን ፤ በወገን ፣ ትዝብት ፣ ከምናተርፍ ፣ ብንቆይ ፣ ይሻላል ፣ እያሉ ፣ የቀሩ ፣ አሉ ፣ አለ ፣ ሞገሴ ።

እናትና ፣ ልጅ ፣ በሐሳብ ፣ አገላለጣቸው ፣ ደስ ፣ አለኝ ። ስድስት፣ ወር ፣ ቆይተን ፣ አሜሪካንን ፣ በሙሉ ፣ ብናውቅ ፣ ደስ ፣ ባለኝ ፣ ነበር ። የሀገሩ ፣ የተፈጥሮ ፣ አቀማመጥ ፣ ልዩ ፣ ነው ። ከያገሩ ፣ መጥተው ፣ የተ ጠራቀሙት ፣ ሰዎች ፣ ሀገሪቱን ፣ ሀገረ ፣ ገነት ፣ ስለአደረግዋት፣ የሰው፣ ልክ ፣ የሚታወቅበት ፤ የሰው ፣ መብት ፣ የሚጠበቅበት ፣ ለሰው ፣ የሚያ ስፈልገው ፣ የሚገኝበት ፣ ጥበብ ፣ የሚፈልቅበት ፣ ሀገር ፣ በመሆኑ ፤ ከደ ረሱበት ፣ ለመድረስ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ዘመን ፣ ያስፈልግ፣ ይሆን ? ሰዎች፣ ናቸውና ፤ ሰዎች ፣ ከሆን ፤ ሰዎች ፣ ከደረሱበት ፣ ለመድረስ ፣ መሞከር ፣ አለብን ። አተኩረን ፣ ስናየው ፣ ተስፋ ፣ እንቈርጥ ፣ ይሆናል ፣ ግን ፣ ተስፋ፣ መቍረጥ ፣ የለም ። አንድ ፣ ቀን፣ ከዚህ ፣ ደረጃ ፣ እንደርሳለን ፣ እያልን ፣ ወደፊት ፣ መራመድ ፣ አለብን ፣ አልኳቸው ።

እንጃ ፣ አባባ ፤ እንጃ ፤ ብዙ ፣ እንቅፋት ፣ አለ ። ለእርምጃ ፣ መሰና ክል ፣ የሚሆነው ፣ እንቅፋት ፣ ሁሉ ፣ በመጥረጊያ ፣ ተጠርጎ ፣ ካልጠፋ፣ እንጃ ፣ አይመስለኝም ። ወደዚህ ፣ ደረጃ ፣ ከማምራት ፣ በፊት ፤ ለኔ ፣ የሚለው ፣ ለእኛ ፣ በሚል ፣ መለወጥ ፣ አለበት ። በየአቅጣጫው ፣ ለሚ ደረገው ፣ ጥረት ፣ እንቅፋት ፣ በመሆን ፣ ፋንታ ፣ በጎ ፣ ፈቃድ ፣ ማሳ የት ፣ ከሁሉ ፣ በፊት ፣ መቅደም ፣ ይኖርበታል ። ከዚህም ፣ ጋር፣ ሀገር፣



16*

ለተወሰኑ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ሳትሆን ፣ እትብታቸው ፡ የተቈረጠባት ፡ መሆንዋ ፡ በሁሉም ፡ በኩል ፡ ይታወቅ ። እትብቱ ፡ ለተቈረጠባት ፡ እያንዳንዱ ፡ ድርሻውን ፡ ሠርቶ ፡ ማለፍ ፡ ግዴታው ፡ መሆኑን ፡ እንዲያውቅ ፡ ማድረግ ፡ ቅድሚያ ፡ የሚሰጠው ፡ ነው ፡ አለ ፡ ሞገሴ ።

ስሜታዊ ፡ ገለጣችን ፡ በዚህ ፡ እንዳለ ፡ ወደኒውዮርክ ፡ ተጓዝን ። የገባን፡ ዕለት ፡ ማታ፡ ልዩ ፡ ልዩ፡ ትርኢት፡ ወደሚታይበት፡ የሌሊት፡ ክለብ ፡ ሄድን ። እንደፍላጐታችን ፡ ዋንጫችንን ፡ ጨብጠን ፡ ፉት ፡ እያልን ፡ ስንጠባበቅ ፡ በተወሰነው፡ ሰዓት ፡ ትርኢቱ ፡ ቀጠለ ። ሦስት፡ ዓይነት ፡ እንዳየን ፡ ፀሐይ ፡ ትዕግሥትዋ ፡ አልቆ ፣ እባካችሁ፡ ይብቃን፡ እንሂድ ፡ አለች ። እስከመጨረሻው ፡ እንይ ፡ አልናትና ፡ ዐየን ።

ወደሆቴላችን ፡ ስንሄድ ፡ ሰው ፡ ከማወቁ ፡ በፊት ፡ ከእንስሳ ፡ እንደማይሻል ፡ ይተረክ ፡ ነበር ። ያንን ፡ አሻሽሎ ፡ ከእንስሳ፡ የተለየ ፡ ኑሮ፡ ከመኖር ፡ ደረጃ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፣ ተመልሶ ፡ ከእንስሳ ፡ የማይሻል ፡ ሥራ ፡ ለካስ ፡ ይሠራል ፡ ጉድ ፡ ነው ፡ እያለች ፡ ፀሐይ ፡ ከሆቴላችን ፡ ደረስን ።

ጧት ፡ ቍርሳችንን ፡ እየተመገብን ፣ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቁም ፡ ነገሩን ፡ ሠርቶ ፣ ከቁም ፡ ነገሩ ፡ በኋላ ፡ በመራቀቅ ፡ የሠራውን ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ ይከተለዋል ፣ ያልተደሰተበት ፡ በአጠገቡ ፡ ድርሽ ፡ አይልም ። እያንዳንዱ ፡ ለሚያደርገውና ፡ ለሚሠራው ፡ ደስ ፡ ካለው ፡ ነፃ ፡ ነውና።

ይህም ፡ ከያንዳንዱ ፡ ሀገር ፡ ባህል ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ የሚጐዳኝ ፡ ነው ፣ ገና ፡ በማደግ ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ሀገሮች ፡ በፊታቸው ፡ የሚጠብቃቸው ፡ ከፍተኛ ፡ የሀገር ፡ ኃላፊነት ፡ ስላለ ፡ ከዚህ ፡ መራቅ፡ አለባቸው፡ ከባህልና ፡ ከታሪክ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ የሌለውን ፡ እየቀዱ ፡ ማጨብጨብ ፡ ውድቀትን ፡ ያስከትላል ፡ እያልን ፡ ተነጋገርን ።

ከዚህ ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ እንድናይ ፡ ሞገሴ ፡ አማከረን። አላደርገውም፡ ፈጽሞ ፡ አላደርገውም ፡ አለች ፡ ፀሐይ ። የፀሐይን፡ ሐሳብ ፡ ለመለወጥ፣ የኒውዮርክን ፡ ከተማ ፡ አጠቃሎ ፡ ወደሚያሳየው ፡ ማማ ፡ (ታዎር፡) ወጣን ፣ የከተማው ፡ እንቅስቃሴ ፡ ሲታይ ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ነበር ። ከዚያም ፡ ርዝመት ፡ ያለውን ፡ ድልድይ፡ አይተን ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ መናፈሻ፡ ጐራ ፡ አልን ። የጉብኝታችን ፡ ፍጻሜ ፡ ሆኖ ፣ ወደሀገራችን ፡ የመመለሻ ፡ ጊዜ ፡ በፊታችን ፡ ተደቀነ ። በቀጥታ ፡ ወደሀገራችን ፡ ከመምጣ



ታችን ፡ በፊት ፡ አንዳንድ ፡ ሀገር ፡ በኤሮፓ ፡ እንጐበኛለን ፡ ያለውን ፡ በሀገርና ፡ በቤተሰብ ፡ ናፍቆት ፡ ሠረዝነው ። ከኒውዮርክ ፡ ቀጥታ ፡ ወደ ሀገራችን ፡ ከመብረራችን ፡ በፊት ፡ ቦስቶን ፡ ጐራ ፡ ብለን ፡ ሁለት ፡ ቀናት ፡ ከልጃችን ፡ ጋር ፡ አደርን ። ሞገሴ ፡ ቴሌግራም ፡ አድርጎ ፡ ኖሮ፡ ቤተሰቦቻችንና ፡ ወዳጅ ፡ ዘመዶቻችን ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መጥተው ፡ ሲቀበሉን ፡ የበለጠ ፡ ደስ ፡ አለን ። በተቀባዮቻችን ፡ ታጅበን ፡ ከልጃችን ፡ ከቡርክት ፡ ቤት ፡ ስንደርስ ፡ ለተቀበሉን ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ፡ ግብዣ፡ ተደረገ ። ሦስት ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ ከልጃችን ፡ ቤት ፡ አርፈን ፡ ወደቤታችን ፡ ስንሄድ ፡ የቅርብና ፡ የሩቅ ፡ ጐረቤቶቻችን ፡ የበለጠ፡ ዝግጅት፡ አድርገው ፡ ተቀበሉን ።

# እ ን ይ !

እንሄዳለን ፡ እንጂ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ዳርቻ ፣
እንዴት ፡ እንወሰን ፡ ባንዲት ፡ ሀገር ፡ ብቻ !
ይኑር ፡ መንቀሳቀስ ፡ እንሂድ ፡ እንይ ፣
ለመቅሰም ፡ ዕውቀትን ፡ ከሌሎቹ ፡ ላይ ።
ተራቀው ፡ በጥበብ ፡ ዓለምን ፡ የሞሉ ፣
ከሰዎች ፡ መካከል ፡ የተመረጡ ፡ አሉ ።
ጠፍቶብን ፡ መንገዱ ፡ የምድሩን ፡ ስናይ ፣
ሰዎች ፡ መሄዳቸው ፡ በጨረቃ ፡ ላይ ።
ለምሳሌነት ፡ ነው ፡ ለሚመራመረው ፣
በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጥበብ ፡ የተራቀቀ ፡ ሰው ፣
የጥበቡን ፡ ያህል ፡ ሰላምም ፡ ቢኖረው ፣
በበዛ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ደስታው ።
ይልቁንም ፡ በጣም ፡ የሚያስገርመው ፣
በቀለም ፡ ልዩነት ፡ የሚሠራው ፡ ነው ።
ሰውን ፡ የፈጠረ ፡ አክብሮ ፡ ቀድሶ ፣
እንዲኖር ፡ ነበረ ፡ ዘላለም ፡ ታድሶ ፣
ካልተፈቀደለት ፡ ማዕድ ፡ ላይ ፡ ቆርሶ ፣
በሕግ ፡ አፍራሽነት ፡ ተቀጣ ፡ ተከሶ ።
ያየውን ፡ ለመንካት ፡ ሲጓጓ ፡ ሲመኝ ፣
ይኖራል ፡ ሲቃትት ፡ ሳይል ፡ ደከመኝ ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ጥንቱንም ፡ ያገኘው ፡ ድቀት ፤
ሳይፈጽም ፡ ቀርቶ ፡ ነው ፡ የጌታን ፡ ቃላት ።

በዓለም ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ፍጥረታት ፡ በሙሉ ፤
ያለመለያየት ፡ አብረው ፡ ይኖራሉ ።

የፍጥረታት ፡ በላይ ፤ የፍጥረታት ፡ ገዥ ፤
ተገልጾለት ፡ ጥበብ ፡ በዓለም ፡ ተገዥ ።

ስለሆነ ፡ ኮርቶ ፡ ባገኘው ፡ ዕውቀት ፤
ይታያል ፡ ሲያዳላ ፡ በዘር ፡ ልዩነት ።

በዕውቀታቸው ፡ ሰዎች ፡ በጥበባቸው ፤
አይታይ ፡ ሲጸና ፡ አንድነታቸው ።

አንድነት ፡ ካልጸና ፤ ካልተደላደለ ፤
ቢራቀቁ ፡ ምንም ፡ በዓለም ፡ ሰላም ፡ የለ ?

ፀጥታና ፡ ሰላም ፡ በዓለም ፡ ካልኖረ ፤
የሰው ፡ ልጆች ፡ ጥበብ ፡ እንደዋለ ፡ ቀረ ፤
በጥፋት ፡ ማዕበልም ፡ አብሮ ፡ ተቀበረ ።

ተብሎ ፡ እንዳይተች ፡ ይኑረው ፡ ማገጃ ፤
በሰው ፡ ልጅ ፡ ፍላጎት ፡ የክፋት ፡ እርምጃ ፤
እንዳትሆን ፡ ዓለም ፡ የጥፋት ፡ ምድጃ ።



ክፍል ፡ ፲፫ ፡

# ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅቶችን ፡ ማቋቋም ፡

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የንብረታችን ፡ መሠረታዊ ፡ አቋም፡ በበለጠ ፡ በመደርጀቱ ፡ ከሠራተኞቻችን ፡ ጋር ፡ ያለን ፡ የሥራ ፡ ግንኙነት ፡ በመተማመን ፡ ላይ ፡ ስለተመሠረተ ፡ እንኳን ፡ ለብዙ ፡ ቀናት፡ ለአንድ፡ ቀን፡ ከፊታቸው ፡ ሲያጡን ፡ ደስ ፡ አይላቸውም ፡ ነበር ።

ከአራት ፡ ወራት ፡ ላላነሰ ፡ ጊዜ፡ ተለይተናቸው፡ በመካከላቸው ፡ በመገኘታችን ፡ የተሰማቸው ፡ ደስታ ፡ ከመጠን ፡ በላይ፡ ሆን ። በጉብኝታችን ፡ ያየነውን ፡ ስናስረዳቸው ፡ ደግሞ ፡ ለመስማት ፡ ያላቸው ፡ ፍላጎት ፡ እጅግ ፡ የጋለ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ።

በኅብረተሰቡ ፡ የሚሠራውን ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ስናሰማቸው ፡ «እንደናንተ ፡ ያሉ ፡ ካልጀመሩት ፡ ማን፡ ይጀምረዋል ? » እያሉ፡ በኛ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ እምነትና ፡ ትምክህት ፡ ከፍተኛ ፡ መሆኑን ፡ ልንገነዘበው ፡ በመቻላችን ፡ ኃላፊነቱ ፡ የበለጠ ፡ አሳሰበን ። መቼም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያላቸው፡ ሐሳቦች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ካልተጠበቁ፡ ሰዎች ፡ ይመነጫሉ ።

ወደሥራቸው ፡ ከመሠማራታቸው ፡ በፊት፡ የንብረታችንን ፡ ጥበቃና ፡ ይዞታ ፡ እንድንጐበኝ ፡ አመለከቱን ። እየተዘዋወርን ፡ ስናይ ፡ በእጥፍ ፡ አድጎ ፡ አገኘነው ። ከምስጋና ፡ ጋር፡ ስጦታ፡ አደረግንላቸው።

መታመን ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ በዚህ፡ መማር ፡ ትችላላችሁ ። በጐበኘናቸው ፡ ሀገሮች ፡ ካገኘነው ፡ ትምህርት ፡ አንዱ፤ አሠሪና ፡ ሠሪ ፡ ተማምነው ፡ በመሥራታቸው ፡ ሥራቸው ፡ እያደገ ፡ ሀብታቸው ፡ እየሰፋ ፡ መሔዱን ፡ ዐይተናል ፡ አልናቸው ።

ጆሮአችሁ ፡ ደኅና ፡ ዜና ፡ እንዲሰማ ፤ ዓይናችሁ ፡ መልካሙን ፡ ሥራ ፡ እንዲመለከት ፡ ጥረት ፡ አድርገናል ። ሰው ፡ ፈቃዱን ፡ ካሳየ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ ከመሥራት ፡ ይቈጠራልና ፡ ብለው፡ መልስ፡ ሰጡ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ ወደአገራችን ፡ በደኅና ፡ ተመልሰን ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ደስታ ፡ ቢሰማንም ፡ ትዝታው ፡ ከሕሊናችን፡ ባለመወ

ገዱ ፡ የልቡናችን ፡ መከፈል ፡ ፀጥታን ፡ ያሳጣን ፡ መሆኑ ፡ በግልጥ ፡ ይታወቅ ፡ ነበር ።

የዛሬውን ፡ ሌሊት ፡ ወዴት ፡ ያሳለፍኩት፡ ይመስልሃል ? አለችኝ፡ ፀሐይ ፤ ከኔ ፡ ጋር ፡ ነዋ ፡ አልኳት ፤ ልክ ፡ አይደለህም ። ያሳለፍኩት ፡ አማና ፡ ከሠራተኞቹ ፡ ጋር ፡ ነው ። ጉድ ፡ ነው ፡ እኮ ፡ ብዬ ፡ ከነቃሁ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ሳንቀላፋ ፡ አሁንም ፡ አማና ፡ ሄጄ ፡ አደርኩ ።

በሐሳብ፡ የሚወጣና ፡ የሚወርድ ፤ ሕልም ፡ እየሆነ ፡ መታየቱ ፡ አይቀርም ። ተምሮ ፡ ያላስተማረ ፤ ዐይቶ ፡ ላላዩ ፡ በሥራ፡ ያላሳየ፡ የጋን፡ መብራት ፡ ነው ። በአየነው ፡ ልባችን ፡ ተነክቷል ። እንፋሎቱ ፡ ከሆዳችን ፡ ሳይወጣ ፡ መሥራት ፡ አለብን ።

ከዚያ ፡ ያለ ፡ መሬት ፡ ከዚህም ፡ አለ ። ምናልባት ፡ ከዚህ ፡ የማይገኘው፡ በቅን፡ልቡና፡ የሚተባበር፡ ነውና፤ ምን፡ ፈሊጥ፡ ይገኝ፡አልኳት።

ሆኖም ፡ በግብርና ፡ ሥራ ፡ የተሻለ ፡ አቅዋም ፡ ያላቸውን ፡ ማስተባበር ፡ ጀመርንና ፡ ከአራት ፡ መቶ ፡ የማያንሱ ፡ አስተባበርን ፤ ለምናቋቁመው ፡ ሥራ ፡ የሚያማክረን ፡ ባለሙያ ፡ እነቡርክት ፡ እንዲፈልጉልን ፡ አደረግንና ፡ ቀጠርን ። የተባበሩት ፡ ገበሬዎች ፡ ከግብርና ፡ ሥራቸው ፡ የከብት ፡ ርባታ፣ አንዱ ፡ ነበር። የአይብ ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ቢቋቋም፣ በአካባቢው ፡ የሚገኘው ፡ ወተት፡ ለኢንዱስትሪው ፡ በቂ ፡ ይሆናል ።

ከዚህም ፡ በቀር ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕፀዋት ፡ የወይን ፡ ጠጅ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ለማቋቋም ፡ ምቹት ፡ ስለአደረብን ፤ ለኢንዱስትሪዎቹ ፡ ማቋቋሚያ ፡ የወጪ ፡ ግምት ፡ እንዲያቀርብ ፡ ነገርነው፣ ለባለሞያው ።

ሐሳብ ፡ ያቀደውን ፡ በሥራ ፡ መግለጥ ፡ ቀላል፡ አይደለም ፤ መናገርና ፡ መሥራት ፡ የተለያየ ፡ ጠባይ ፡ አላቸው ። ተናጋሪ፡ ሁሉ ፡ ሠሪ፡ ቢሆን ፡ ሥራ ፡ ባልተዝረከረከ ፡ ነበር ።

ከዋናው ፡ ከተማ ፡ በሠላሳ ፡ ኪሎ ፡ ሜትር፤ ከዋናው ፡ መንገድ ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ኪሎ ፡ ሜትር ፡ ርቀት ፡ እንኖራለን ። ከዋናው ፡ መንገድ ፡ የሚያገናኘውን ፡ የራሳችንን ፡ መንገድ ፡ ለማሠራት ፡ የሚያስፈልገውንና ፡ ሌላውንም ፡ የሚያጠቃልል ፡ ወጪ ፡ ከባለሞያው ፡ ጥናቱ ፡ ቀረበልን ። ጥናቱ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ ፈጀ ። ሥራው፣ በጣም ፡ አድካሚ ፡ ነው ፤ እንዴት ፡ ነው ፡ የሚገፋው ፤ ወዘናን ፡ ጨርሶ፡ ፍሬ፡ ሲሰጥ ፡ ቀላል ፡ ይመስላል ፡ አልኩ ።



አዬ ፡ ምኑ ፡ ተያዘና ፡ ከዚህ ፡ አባባል ፡ ደረስክ ፤ ገና፡ ክብደትህን፡ እንኳ ፡ በብዙ ፡ ሳትቀንስ ፤ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ በዋዛ፡ አይቋቋምም ። ጉልበትንና ፡ ገንዘብን ፡ ጨርሶ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ አጽናናችኝ ፡ ፀሐይ ። በባለሞያው ፡ ተጠንቶ ፡ የቀረበውን ፡ ወጪ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የተመዘገቡት ፡ ድርሻቸውን ፡ እንዲከፍሉ ፡ ጠየቅናቸው ።

የሚበልጡት ፡ ሲከፍሉ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ተደናግጠው ፡ ራቁ ፤ ገንዘቡን ፡ ለመሰብሰብ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ፈጀብን ።

ቀድሞውን ፡ «ባልዘፈንሽ ፡ ከዘፈንሽም ፡ ባላሳፈርሽ ፡ » በአንድነታችን ፡ ተናግረን ፡ እጃችንን ፡ ጥልቅ ፡ አድርገን ፡ ሥራውን ፡ ጀምረናል ፡ ትንፋሻችን ፡ እስካለ ፡ ወደፊት ፡ ከመግፋት ፡ በቀር ፡ ወደኋላ ፡ አንመለስም ፡ ብለን ፡ ለመተባበር ፡ ቃል ፡ ከገቡት ፡ ከአጋማሽ ፡ የማያንሱት ፡ መሸሻቸውን ፡ ለተባባሪዎቻችን ፡ በነገርናቸው ፡ ጊዜ ፡ የመደናገጥ ፡ ምልክት ፡ ታየባቸው ።

ሆኖም ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጠቃሚ ፡ እንደሆነ ፡ ይልቁንም ፡ ብዙዎችን ፡ በሥራ ፡ በመቅጠርና ፡ በተፈጥሮ ፡ ሀብታም ፡ የሆነችውን ፡ ሀገራችንን ፡ በማልማት ፡ የሥራ ፡ ድርሻችንን፡ እንሠራለን፣ ብለን ፡ ተነሣሥተናልና ፡ ወደፊት ፡ እንጂ ፡ ወደኋላ፡ አንመለስም ። የበሰለን ፡ ለመመገብ ፡ ፈላጊው ፡ ይበዛል ። ድካምን ፡ ለመካፈል ፡ ከሚተባበረው ፡ የሚሸሸውና ፡ የሚያደናቅፈው ፡ እንደሚበልጥ ፡ ዐውቀን፤ ጅምራችንን ፡ መቀጠል ፡ አለብን ፡ በማለት፡ አደፋፈርናቸው ። አሁን፡ ካሉት ፡ ተባባሪዎቻችን ፡ አንዱ ፡ በሸሹት ፡ የሚተኩ ፡ እናምጣ ፡ ካልሆነም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ እኛው ፡ ራሳችን ፡ እናሟላ ፡ ብሎ ፡ ስለተናገረ ፡ ደስ ፡ አሰኘን ።

ከልብ ፡ ካሰቡ ፡ ከሰው ፡ አቅቶ፡ የሚቀር ፡ የለም ፤ የተጠየቁትን፡ ለማዋጣት ፡ የሚችሉ ፡ ይዘው ፡ በቀጠሮዋቸው ፡ መጡ ። ቀዝቅዞ ፡ የነበረው፡ የሐሳብ ፡ መዳከም ፡ እንደገና ፡ አንሠራራ ። ከተገመተው ፡ የሚበልጥ ፡ ገንዘብ ፡ ተዋጣ ።

በቅድሚያ ፡ የአይብ ፡ ፋብሪካና ፡ የርሻ ፡ መኪናዎች ፡ አስመጣን ፤ በባለሞያው ፡ ተገጣጠሙ ። የርሻው ፡ ሥራ ፡ ተፋጥኖ ፡ ሲጀመር ፡ የአይብ ፡ ፋብሪካው ፡ ዘግይቶ ፡ ቀጠለ ።

ያ ፡ ተስፋ ፡ መቍረጥ ፡ ቀረና ፤ የድካም፣ ፍሬ ፡ ከማየት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ደረስን ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ሥራውን ፡ የሚያካሂዱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ፣

ባለሞያ ፡ ሠራተኞች ፡ ቢኖሩ ፤ አዘውትረን ፡ ከአጠገባቸው ፡ ባለመለ የታችን ፡ ሥራውን ፡ በትጋትና ፡ በንቃት ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ።

የኅብረቱ ፡ ተካፋይዎች ፡ ተሰብስበው ፤ ሥራ ፡ አስኪያጅና ፡ ሥራ ውን ፡ በቅርብ ፡ የሚመለከቱ ፡ ከመካከላቸው ፡ መርጠው ፡ እኔን ፡ ሰብ ሳቢ ፡ አደረጉ ።

ሠራተኞች ፡ በአሠሪያቸው ፤ አሠሪ ፡ በሠራተኞቹ ፡ እምነትና ፡ ፍቅር ፡ ከሌለ ፡ በሥራው ፡ በኩል ፡ የሚገኘው ፡ ውጤት ፡ ደካማ ፡ መሆኑን ፡ አስቀድሜ፡ ስለማውቅ ፤ በሥራው ፡ የተሠማሩት ፡ በሥራቸ ውና ፡ በአሠሪዎቻቸው ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ እንዲኖራቸው ፡ ጣርኩ ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ሥጋ ፡ እየታረደ ፡ ይመገባሉ ። ማንም፡ እንደወንድም፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ እንዳይመለከታቸው ፡ አደረግሁ ። በዚህ፡ ይዞታ ፡ ሠራተኞቹ ፡ ያላቸው ፡ አስተሳሰብ ፡ የባለቤትነት ፡ ሆነ ።

ሰው ፡ ሥራውን ፡ እንደራሱ ፡ አድርጎ ፡ ካየው ፡ ልማቱን ፡ እንጂ፡ ጥፋቱን ፡ አይወድም ። ሠራተኞች ፡ ኅብረታቸውን ፡ አጠንክረው ፡ በመሥራታቸው ፡ ጥቅሙም ፡ ከተጠበቀው ፡ በላይ ፡ ሆነ ።

የኅብረቱ ፡ ተካፋይዎች ፡ ይህንኑ ፡ ባወቁት፡ ጊዜ ፤ ገቢው ፡ ለሥራ፡ ማቋቋሚያ ፡ እንዲውል ፡ በደስታ ፡ ፈቀዱ ።

ገቢው ፡ በየጊዜው ፡ እየተሻሻለ ፡ ስለሄደ ፤ በአማካይ ፡ ቦታ ፡ አንድ ፡ መጠነኛ ፡ ሆቴል ፡ አዘጋጀን ። በዚህም ፡ ያልታሰበ ፡ የገቢ ፡ ምንጭ ፡ ተፈጠረ ። ከገቢውም ፡ ይልቅ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ አስተዋወቀን ፡ የልማት ፡ ጣቢያችን ፡ የከተማን ፡ ጠባይ ፡ ያዘች ። ሥራችን ፡ በሀገ ርና ፡ በውጭ ፡ ሰዎች ፡ እየተጐበኘ ፡ የሞራል ፡ ድጋፍ ፡ አገኘን ። እቅ ዳችንን ፡ በየአቅጣጫው ፡ ከማሳወቃችን ፡ የተነሣ ፡ ከውጭ ፡ ርዳታ ፡ የምንጠይቅበት ፡ መምርያ ፡ ተሰጠን ። የመሣሪያና ፡ የገንዘብ፡ ርዳታም፡ አገኘን ።

እግዚአብሔር ፡ ለካስ ፡ ያለው ፡ ከሠራተኞች ፡ ጋር ፡ ነው ። ሰው ፡ መሞከር ፡ እንጂ ፤ የሚያሳካውማ ፡ ባለቤቱ ፡ ነው ፤ አለች ፡ ፀሐይ ፡ የሥ ራችን ፡ ውጤት ፡ እየሠመረ ፡ መሄዱ ፡ ለሕሊናዋ ፡ አድናቆት ፡ አሳድሮ ባት ።

በርዳታ ፡ ባገኘነው፡ ገንዘብ ፤ ከኅብረተሰቡ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ጋር፡ ተመጣጣኝ ፡ የሆነ ፡ የዘይትና ፡ የሳሙና ፡ ፋብሪካ ፡ አቋቋምን ።



ሠርቶ ፡ የሚኖረው ፡ ሰላማዊው ፡ ሕዝብ ፡ ቀን ፡ ሲሠራ ፡ ውሎ ፡ ድካሙን ፡ በዕረፍት ፡ በሚያሳልፍበት ፡ ሌሊት ፤ ሥራ ፡ ፈቱ፡ ጨለማ፡ ለብሶ ፡ እየዘመተ ፡ ከበረቱ ፡ ከብቱን ፤ ከጐተራ ፡ እህሉን ፡ እየሰረቀ ፡ ለኑሮው ፡ ጠንቅ ፡ በመሆኑ ፡ በወር ፡ ተራ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር። የልማት፡ ሥራችን ፡ እየተስፋፋ ፡ የሚበልጠው ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ሥራ ፡ በመያዙ ፡ አካባቢው ፡ ሰላም ፡ ሆነ ።

በውጭ ፡ ሀገር ፡ካየናቸው ፡ ከሚያስቀኑት ፡ ከብዙዎቹ ፡ አንዱ ፤ እያንዳንዱ ፡ ግለሰብ ፡ በሚኖርበት ፡ ቤት ፡ አጥር ፡ የለም ። ንብረቱ ፡ በአጥርና ፡ በዘበኛ ፡ አይጠበቅም ።

ሥራ ፡ ያልያዘ ፡ ሥራ ፡ እስኪይዝ ፡ ደመወዝ ፡ ይከፈለዋል ። በተ ጨማሪም ፡ ስርቆት ፡ ውርደት፡ መሆኑን ፡ ሕዝቡ፡ ስለሚያውቅ ፡ ራሱን፡ በራሱ ፡ ይቈጣጠራል ። በዓለም ፡ ጠቅላላ ፡ አስተሳሰብ ፡ አለ ። ሥራ ፡ ፈት ፡ እንዳይኖር ፡ ሥራ ፡ እየፈጠሩ ፡ ሥራ ፡ ማስያዝ ፡ ነው ። ብቸኛ ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ሠሪውን ፡ እንኳን ፡ ስለማያጠግብ ፤ ይህ ፡ እየ ተጣበበ ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ በመስፋፋቱ ፡ የሥራ ፡ ፈት፡ ቊጥር ፡ የተ መናመነ ፡ ሆኗል ። ሥራም ፡ ስለማይናቅ ፡ ማናቸውንም ፡ ሠርቶ ፡ ሠራተኛ ፡ የዕለት ፡ ፍላጎቱን ፡ የሚሸፍንበት ፡ ገንዘብ ፡ ያገኛል ።

እስካሁን ፡ ባቋቋምናቸው ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ፈቶች ፡ ተቀጥረው ፡ አካባቢያችን ፡ ከሌባ ፡ ጥበቃ ፡ እፎይ ፡ ብሎ ፡ በሰላም ፡ አንቀላፍቶ ፡ ያድራል ።

ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ደብዳቤ ፡ ደረሰን ። ስለ ሥራችን ፡ የተጻፈ ፡ አስተያየት ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ ብናነበው ፤ በጀመ ርነው ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ መደሰቱንና ፡ ጠንክረን ፡ እንድንሠራ ፡ አበረ ታቶ ፤ ወደሀገሩ ፡ የሚመለስበትን ፡ ቀን ፡ ቅርብ ፡ መሆኑን ፡ የሚያበ ስር ፡ የሞገሴ ፡ መክብብ ፡ ደብዳቤ ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ።

የልጃችንን ፡ ወደሀገሩ ፡ መመለስ ፤ ለቤተሰቡና ፡ ለኅብረቱ፡ ሥራ፡ ተካፋይዎች ፡ ነገርናቸው ። የተማረና ፡ ብዙ ፡ ያየ ፡ በመካከላችን ፡ ስናገኝ ፡ ሥራችን ፡ የበለጠ ፡ የተቃና ፡ ይሆናል ፡ እያሉ ፡ የደስታ ፡ ምኞ ታቸውን ፡ ገለጹልን ።

ሀገሩ ፡ ከሚገባበት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ሄደን ፡ ከነቡርክት፡ ቤት ፡ አደርን። የነቡርክትን ፡ ቤት፡ ማረፊያ፡አደረግ

ነው ። አንድ ፡ ቤት ፡ የሚሠራው ፡ ለአንድ ፡ ቤተሰብ ፡ ነው ፤ ቤተሰብ ባልና ፡ ሚስት ፡ ከነልጆቻቸው ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ ውጪ ፡ ሄዶ ፡ ማጣ በብ ፡ ትክክል ፡ አይደለምና ፡ ማረፊያ ፡ ቤት ፡ እንግዛ ፡ አለች ፡ ፀሐይ ።

እንዴት ፡ እስካሁን ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ከፊታችን ፡ ተሰወረ ፡ እባክ ሽን ፤ ካልሽማ ፡ «ኑሮና ፡ መቃብር ፡ ለብቻ ፡ ነው ፡ » ይባል ፡ የለ ፤ ሰው ፡ በጣም ፡ ከተቀራረበ ፡ በትዝብት ፡ የሚመለከተው ፡ እያጣም ። ትዝብት ፡ ሲበዛ ፡ መናናቅ ፡ መገማመት ፡ ይከተላል ፡ አልኳት ።

ሌሊቱ ፡ ወር ፡ ተራውን ፡ ለቀኑ ፡ ብርሃን ፡ ሲለቅ ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ አውሮፕላን ፡ ጣቢያ ፡ ሄድን ። ሞገሴ ፡ መክብብ ፡ በተወሰነው፡ ሰዓት፡ ገባ ፤ በመሳም ፡ ናፍቆታችንን ፡ ተወጣን ።

በቤታችን ፡ ወዳጆቻችን ፡ ተሰብስበው ፡ ተቀበሉን ። ያቋቋምነ ውን ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ እንድናስጐበኘው ፡ ጠየቀንና ፡ አንድ፡ በአንድ፡ ዐየ ። ሥራውን ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ በጣም ፡ የሚያኰራና ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሥራ ፡ አቋቁማችኋል ፤ በሚቈጠሩ ፡ ዘመናት ፡ በትምህርት ፡ የኖሩና ፡ የጐበኙ ፡ ያልሠሩትን ፤ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ባያችሁት ፡ መልካም፡ ቅናት፡ አድሮባችሁ፡ መሥራታችሁ ፡ ለኔ፡ ለልጃችሁ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሚያ ውቃችሁ ፡ ሁሉ ፡ ታኰራላችሁ ፡ ብሎ ፡ አመሰገነ ።

ሞገሴ ፡ በእንግድነት ፡ የሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ አለቀና፤ምን ፡ ሠርቶ፡ የመኖር ፡ ዓላማ ፡ እንዳለው ፡ ጠየቅነው ። የተማረው ፡ የትምህርት ፡ አመራር ፤ ሕግና ፡ ኢኮኖሚ ፡ ስለሆነ ፤ ለጊዜው ፡ በመንግሥት ፡ መሥ ሪያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ በግል ፡ ድርጅት ፡ ተቀጥሮ ፡ እንደሚሠራ ፡ ገለጠ ልን ።

ቀጥሎም ፡ የጽሕፈት ፡ ቤታችንን ፡ ይዞታ ፡ ተመለከተ ፤ የባለመ ብቶቹ፡ አቅዋም ፡ እንደምን ፡ ባለሁኔታ ፡ እንደተመሠረተ ፡ ጠየቀ ። በጽሑፍ ፡ ያደረግነው ፡ ውል ፡ የለም ። ውላችን ፡ የተመሠረተው ፡ በእ ምነት ፡ በቃል ፡ ነው ። የአባቶቻችንን ፡ ረድኤት ፡ ገና ፡ ያልራቀን ፡ ስለ ሆነ ፤ ከወረቀት ፡ ይልቅ ፡ የበለጠ ፡ በቃላችን ፡ እንተማመናለን ፡ አል ነው ።

የሚታመን ፡ ካለ ፡ መተማመን ፡ ይገባል ። ሥራ ፡ በመሥራቾች፡ ዕድሜ ፡ አይወሰንም ። ከትውልድ ፡ ወደትውልድ፡ የሚተላለፍ ፡ ነው ። በነገ ፡ ተተኪዎች ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ጠፍቶ ፡ ሥራው፡ እንዳይበላሽ፡



ከሥራ ፡ ጋር ፡ የሚወረስ ፡ በሕግ ፡ የተደገፈ፡ የመሥራቾችን ፡ መብት፡ የሚጠብቅ ፡ ውል ፡ ሊኖር ፡ ይገባል ፡ አለን ። እኛ ፡ በሐሳቡ ፡ ተስማም ተን ፡ ጠቅላላውን ፡ አጥንቶ ፡ እንዲያዘጋጅልን ፡ ነገርነው ።

የኅብረቱ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ ተመዝግበው ፡ ገንዘብ ፡ በተጠየቀበት ፡ ጊዜ ፡ ሸሽተው ፡ የነበሩት ፡ የሥራው ፡ ተካፋይዎች ፡ እንዲሆኑ ፡ ጠየቁ ። በዕቅድ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ ሥራዎች ፡ ሲቋቋሙ ፡ ተካ ፋይ ፡ እንደሚሆኑ ፡ ተነገራቸው ። ሆኖም ፡ ቀደም፡ ብሎ፡ በተቋቋመው፡ ባለመግባታቸው ፡ ጥላቻ ፡ እንዳደረባቸው ፡ ባስተያየታቸው ፡ አንዳ ንድ ፡ ጊዜም ፡ በሚሠነዝሯቸው ፡ ቃላት ፡ ልናውቅ ፡ አስቻለን ።

ከዚህ ፡ የተነሣም ፡ የሥራው ፡ መስፋፋትና ፡ የገቢው ፡ ምንጭ ፡ ሲታወቅ ፡ ሥራውን ፡ ለማደናቀፍ ፡ ሆን ፡ ብለው ፡ ጥረት ፡ ማድረግ ፡ ጀመሩ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ሥራ ፡ አቋቁመን ፡ ሥራ ፡ ፈቱን፡ በማስያዝ፡ ለቀበሌውና ፡ ለአካባቢው ፡ ሰላም ፡ ከማስገኘት ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ እን ዳልበደልን ፡ ስለምናውቅ ፡ እንደልቦናቸው ፡ ይስጣቸው ፡ ብለን ፡ ሥራ ችንን ፡ ቀጠልን ።

በተለይ ፡ ጥላቻቸው ፡ በኔና ፡ በፀሐይ፡ በርትቶ ፤ ለሕይወታችን ፡ ሳይሳሱ ፡ ሊያጠፉን ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ እንደሚፈልጉ ፡ የኅብረት ፡ ተካ ፋይዎች ፡ በቅድሚያ ፡ ዐውቀው ፡ ቅርብ፡ ሆነው ፡ ይጠብቁን ፡ ጀመር ። ለመልካም ፡ ሥራ ፡ ዋጋው ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ መገደል፡ ከሆነ፡ ብንሞትም፡ በመጠኑ ፡ ይደግ ፡ ይነስ ፡ እንጂ ፡ ታሪክ ፡ ያለው ፡ አይሞትምና ፡ በሥ ራችን ፡ የሚጠብቀንን ፡ ክብር ፡ እንወርሳለን ፡ እያልን ፡ ባለመሸበር ፡ በሥራችን ፡ ላይ ፡ ያለንን ፡ እምነት ፡ አጠንክረን ፡ ወደፊት ፡ ገፋን ።

ሥራችንን ፡ የሚበጠብጡት ፡ ሠራተኞቻችንን ፡ በገንዘብ ፡ አታ ለው ፡ ለሥስት ፡ ቀናት ፡ ሥራው ፡ እንዲቆም፡ አደረጉ ። በመካከላችን፡ የነበረው ፡ የአሠሪና ፡ የሠራተኞች ፡ እምነት ፡ ደፈረሰ ። ሆኖም ፡ ሠራ ተኞቹን ፡ ልብ ፡ በሚሰብር ፡ ምክር ፡ መመለስ ፡ ቻልን ። በምቀኝነት ፡ የተነሣሡ ፡ ጠላቶቻችን ፡ በሕግ ፡ እርምጃ ፡ እንዲወሰድባቸው፡ ከሰስና ቸው ። በደላችንን ፡ ስናሰማ ፡ ደጋፊያችን ፡ በዝቶ ፡ የማርያም ፡ ጠላት ፡ አላቸው ፤ ይህን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸውን ፡ ለማዳን፡ ተሯሯጡ ። እኛም፡ እውነትን ፡ በመያዛችን ፡ የመንፈስ ፡ ኵራት ፡ ተሰምቶን፡ እንደልባችን፡ ነበርን ። ነገር ፡ ግን ፡ ከልብ ፡ የሚደግፉን ፡ ወዳጆቻችን ፡ በየጊዜው ፡

ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ ከመስጠታቸውም ፡ ሌላ ፡ እኛ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ስንጋ ልብ ፡ ተቃዋሚዎቻችን ፡ ግን ፡ ውስጡን ፤ በእጃቸው ፡ ጭምር ፡ እን ደሚሄዱ ፡ ገለጹልን ።

በሕይወት ፡ ዘመናችን ፡ ከሥራ ፡ በቀር ፡ ከዳኛ ፡ ፊት ፡ ቀርበን ፡ አናውቅም ፤ እውነትን ፡ ይዘን ፡ ስለቀረብን ፡ ትክክለኛ ፡ ፍርድ ፡ እናገ ኛለን ፡ ብለን ፡ ጓጉተን ፡ ነበር ። በችሎቱ ፡ አዳራሽ ፡ ከዳኞቹ ፡ በስተ ኋላ ፡ ሚዛን ፡ ተሰቅሎ፡ ይታያል፤ ምንድን፡ ነው ፡ ብለን ፡ ብንጠይቅ ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ ማዳላት ፡ እንደሌለ ፡ የሚያስጠነቅቅ ፡ ትክክለኛ ፡ የፍ ርድ ፡ ሚዛን ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረባቸው ፡ ይከተሉታል ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ተሰጠን ።

ስለ ፡ እውነትና ፡ ሐሰት ፡ ሦስት ፡ ሆነን ፡ ሞቅ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ስናደርግ ፤ የሚያዋጣንን ፡ እውነትን ፡ ይዘን ፡ እንንገታገት ፡ እንጂ ፤ ሌላው ፡ አይጠቅመንም ። በዚህች ፡ ዓለም ፡ እውነትና ፡ ሐሰት ፡ እየተ ፈራረቁ ፡ የሚኖሩባት ፡ ስለሆነ ፤ ሰላም ፡ የምናገኝ ፡ ከሆነ ፡ በሐሰት ፡ እንጠቀምባትና ፡ እሮይ ፡ እንበል ፡ አለ ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፤ አሳሳች ፡ ባይኖር ፡ የሚሳሳት ፡ አይገኝም ፡ ነበር፤ መሳሳት ፡ ወይም ፡ መታለልና፡ መደለል ፡ ባይኖር ፡ በውድ ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ እውነት ፡ ተጠብቃ ፡ ትኖር ፡ ነበር ፤ ከእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ እንደጲላጦስ ፡ እጄን ፡ እታጠ ባለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚከተለውን ፡ ዘመረ ፡ ሦስተኛው ።

# እግዜር ፡ ያሳይዎ ፡

በደሌን ፡ ልናገር ፡ ልጩህ ፡ ላሰማዎ ፤
ይስሙኝ ፡ የኔ ፡ ጌታ ፡ እግዜር ፡ ያሳይዎ ።

ሰምተውኛል ፡ መስማት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ችላ ፡ አሉኝ ፤
እባክዎ ፡ አይናቁኝ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጡር ፡ ነኝ ።

ሰው ፡ እኮ ፡ መሆኔን ፡ ለይቼ ፡ የማውቀው ፤
ከሰዎች ፡ ጋር ፡ እኩል ፡ ትክክል ፡ ስታይ ፡ ነው ።

ተቸግረን ፡ እኩል ፡ እንኖራለን ፤
ደግሞም ፡ ታመን ፡ ታመን ፡ እንሞታለን ፤
በሦስት ፡ ክንድ ፡ መሬት ፡ እንወሰናለን ።

በዚያም ፡ በዚህ ፡ ሆነ ፡ ለዚህ ፡ አጭር ፡ ዕድሜ ፤
እንተያይ ፡ እኩል ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ።



አላገኘሁም ፡ ሰው ፡ በሰው ፡ አልመካም ፤
በደለኝ ፡ ብዬ ፡ ሰው ፡ አልጠላም ፡ አላማም ፤
ሰው ፡ መልእክተኛ ፡ ነው ፡ ለደጉም ፡ ለክፉም ።

የማዝንበት ፡ ሰውን ፡ የማማርረው ፤
ይፍረድብኝ ፡ ብሎ ፡ ሲፈርድበት ፡ ነው ።

እውነት ፡ ሠሪ ፡ ማነው ፡ እውነት ፡ ተናጋሪ ፤
ተቆርቋሪ ፡ ለእውነት ፡ በደልን ፡ መርማሪ ።

እንያዝ ፡ ቁናችንን ፡ ይሠፈር ፡ በደል ፤
እውነትን ፡ አጥፍቶ ፡ ይቅር ፡ መማማል ።

የዳኝነት ፡ ሚዛን ፡ ተሰቅሎ ፡ በሰማይ ፤
አወይ ፡ ተላላው ፡ ሰው ፡ ያዳላል ፡ መሬት ፡ ላይ ።

በአዳራሹ ፡ ሁሉ ፡ ተሰቅሏል ፡ ሚዛን ፤
ያያሉ ፡ ፍጥረታት ፡ አተኩረው ፡ በዓይን ፤
እጅግ ፡ ያስጨንቃል ፡ ውስጠ ፡ ሕሊናን ።

ይጨነቅ ፡ አዕምሮ ፡ ሕሊና ፡ ግን ፡ ይፍረድ ፤
ይቅር ፡ እባካችሁ ፡ እጅግ ፡ ራስ ፡ መውደድ ።

የወደደ ፡ ራሱን ፡ ብቻውን ፡ ይሞታል ፤
ሁለት ፡ ዓለማትን ፡ ጥሎ ፡ ይሰደዳል ፤
የግፉ ፡ ፍጻሜ ፡ ለዘሩም ፡ ይተርፋል ።

ላብጅ ፡ ወገን ፡ ብሎ ፡ መንገድ ፡ ከመሳት ፤
መልካም ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡ ወገን ፡ ማደርጀት ፤
ከሁሉም ፡ ይበልጣል ፡ በዚህ ፡ መመካት ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ከበደል ፡ ከሐኬት ፡ ካመፃ ፤
ከቶ ፡ መቼ ፡ ይሆን ፡ የሚሆነው ፡ ነፃ ።

ሐሳብ ፡ ተወርዋሪ ፡ አርቆ ፡ ተኳሽ ፤
እንዴት ፡ ያቅተዋል ፡ ከክፉ ፡ መሸሽ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ንግግራችንን ፡ አጠቃለን ፤ እውነትን ፡ ከእጃችን ፡ አውጥተን ፡ ሐሰትን ፡ እንተካም ። በሥራችን ፡ ላይ ፡ እንቅፋት ፡ የገጠ መን ፡ ለፈተና ፡ ይሆናልና ፡ እስኪያልፍ ፡ ቢያለፋም ፤ የተሳሳተ፡ ሥራ፡ መሥራት ፡ የለብንም ፡ በማለት ፡ ተስማማን ።

የተሳሳተ ፡ መንገድ ፡ ለመራን ፡ ከተሳሳተ፡ መንገድ፡ እንዲታረም፡ ሰው ፡ ወደፊቱ ፡ ይራመዳል ፡ እንጂ፡ ወደኋላው፡ አይመለስም ። የሰው፡ በር ፡ አንኳኩተን ፡ እውነት ፡ ትጥፋ ፤ ሐሰት ፡ ትዳብር፡ ብለን ፡ ማሳ ሳት ፡ ከኃጢአትም ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፤ እስቲ ፡ አንተም፡ በጽሞና ፡ አስ ተውለው ። አሳሳች ፡ ባይኖር ፡ ተሳሳች ፡ ሊኖር ፡ አይችልም፡ ነበር ። ሰጭዎች ፡ የጠነከረ ፡ ዓላማ ፡ ቢኖረን ፤ እውነት ፡ መንገድዋን ፡ ሳት ለቅ ፡ ትራመድ ፡ ነበር ። እውነት ፡ ትመንምን ፡ እንጂ፡ አትጠፋም ። ሰልፋችን ፡ ከእውነት ፡ ጋር ፡ ቢሆን ፡ ሐሰት ፡ መድረሻ፡ አጥቶ ፡ ይሰ ደድ ፡ ነበር ። ሐሰት ፡ ከተሰደደ ፡ በዚህ ፡ አደባባይ፡ የሚታየው፡ ሁሉ፡ ወደዕለት ፡ ተግባሩ ፡ ተሠማርቶ ፡ ሁሉም ፡ ሠርቶ ፡ በላ ፡ ይሆን፡ ነበር ፡ እያልን ፡ ሊያግባባን ፡ የሞከረውን ፡ ለማግባባት ፡ ሞከርን ።

ተቀባይ ፡ አታገኙም ፡ እንጂ ፤ አስተሳሰባችሁ ፡ ባልከፋ ። ሰው ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ባወጣና ፡ ባወረደ ፡ መጠን ፡ የሕሊና፡ ፍርድ፡ ከፊቱ፡ ይደቀናል ። የሕሊናን ፡ ዳኝነት ፡ ማንም ፡ ሊለውጠው ፡ ስለማይችል ፡ እውነትን ፡ ሽጦ ፡ ሐሰትን ፡ የገዛ ፡ ይጨነቃል ። የደላላነት፡ ሥራዬን ፡ መሥራት ፡ ከጀመርኩበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እንደእናንተ፡ ድርቅናን፡ መሣሪያ ፡ ያደረገ ፡ አላጋጠመኝም ፤ ቢያጋጥመኝም ፡ ወዲያውኑ ፡ እን ዲመለስ ፡ አደርገዋለሁ ። ሆኖም ፡ ስባክን ፡ ውዬ ፡ የማታ፡ ማታ ፡ በት ንሿ ፡ ጐጆዬ ፡ ሌሊቱን ፡ ለማሳለፍ ፡ ገደም ፡ ስል ፤ ቀን ፡ የሠራሁት፡ በፊቴ ፡ ይደቀንና ፡ ያስጨንቀኛል ። በቀረብኝ ፡ እያልኩ ፡ ስፀፀት ፡ አድ ርና ፡ ከጐጆዬ ፡ ወጣ ፡ ስል ፤ እቀጥላለሁ ። ማታ ፡ ከማን፡ ጋር ፡ ነው ፡ የማድረው ፤ ቀንስ ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ነው ፡ የምውለው፤ በዓይን ፡ የማይ ታይ ፡ በእጅ ፡ የማይዳሰስ ፡ ጓደኛ ፡ አለኝ ? እያልኩ ፡ ከራሴ ፡ ጋር ፡ አወ ጋለሁ ።

ሰዎች ፡ የእውነት ፡ መሣሪያ ፡ ሆነው፡ ቢሠለፉ ፤ ኃጢአቱን ፡ ተና ዝዤ ፡ አብሬ ፡ ለመሠለፍ ፡ ያለኝ ፡ ምኞት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ተገቢ ፡ ሆነው ፡ የሚቀርቡ ፡ ይኖሩ፡ ይሆን ? እንጃ፤ እንጃ፤ እንደእናንተ ፡ እውነት ፡ እያለ ፡ ድርቅናን ፡ ከጽድቅ ፡ ቈጥሮ ፡ የሚን ገታገት ፡ ለጊዜው ፡ ሥፍራ ፡ የለውም ። ትርፉ ፡ ውርደትና ፡ ድኅነት ፡ ስለሆነ፤ማሳቂያ ፡ ነው። «የአባትህ፡ ቤት ፡ ሲወረር ፡ አብረህ ፡ ውረር» ይባል ፡ የለ ፡ ከነተረቱ ።



«የማታ ፡ ማታ ፡ እውነት ፡ ይረታ ፡» የሚባለውንስ ፡ አታምን ምን ? « እኔ ፡ ከሞትኩ ፡ ሰርዶ ፡ አይብቀል ፡ » ያለቺውስ፡ ይዘነጋልን? መቼም ፡ ወደቁም ፡ ነገሩ ፡ ዘወር ፡ ስንል ፤ ድል፡ የናንተ፡ እንደሚሆን፡ የሚታመን ፡ ነው ። ይህች ፡ ዓለም ፡ ተበቃይ ፡ ናት። ዋጋውን፡ ወይም፡ ብድሩን ፡ ሳያገኝ ፡ እንደቀለደ ፡ የሚሔድ፡ የለም ። ለጊዜው ፡ እንኳ ፡ በዳዩን ፡ ራሱን ፡ ባትበቀለው ፡ በዘሩና ፡ በንብረቱ ፡ ትበቀለዋለች ። የታየው ፡ ለፍሬ ፡ ሳይደርስ ፡ ይቀራል ። ወይም ፡ ፍሬው፡ እንክርዳድ፡ ይሆናል ። ንብረቱ ፡ ከዘሩ ፡ ወጥቶ ፡ ሌሎች፡ ይጠቀሙበታል። ውሎ፡ ከማደሩ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ጽዋ ፡ አይቀርም ። የናንተን ፡ እውነት ፡ መከ ተል ፡ ስለምመርጥ ፤ አንዱን ፡ ከአንዱ ፡ እያማታሁ ፡ ከምኖር ፤ በጉል በቴ ፡ እየሠራሁ ፡ ከናንተ ፡ ጋር ፡ እንድኖር፡ ውሰዱኝ ፡ ብሎ፡ ጠየቀን ።

በጥያቄው ፡ ተደናግጠን፡ እንዴት ፡ ይሆናል ፤ ወንድሜ ፡ ከተሜ፡ ነህ ። ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አድካሚ ፡ ነው ፡ አልነው ፤ የማይ ለመድ ፡ የለም ፤ በዚህ ፡ አሳብ፡ አይግባችሁ ። ከተሜ ፡ ነህ ፡ ያላችሁኝ፡ በሰውነቴ ፡ መለስለስ ፡ ከሆን ፡ አታስቡ ፤ እንዳንተ ፡ ያለ፡ የሥራ ፡ ተካ ፋይ ፡ ስናገኝ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ እንዳልነው፤ ከምስጋና ፡ ጋር፡ እጃችንን፡ ጨብጠንና ፡ ለሥራችን ፡ እንቅፋት ፡ የሆኑት፡ ባላጋራዎቻችን ፡ ዋስ ፡ እንዲጠሩ ፡ አድርጎ ፡ ከችሎቱ ፡ ተሰናበትን ።

ወደቤታችን ፡ ስንመለስ ፡ ፀሐይ ፡ በናፍቆት ፡ ተቀብላ ፡ አስተናገ ደችን ። በከተማ ፡ ውለን ፡ በማደራችን ፡ ምን ፡ አጋጠማቸው ፡ ብላ ፡ ሐሳብ ፡ እንደገባት፡ ገለጠችልን ፤ በከተማ ፡ የደረሰብንና ፡ አብሮ ፡ ስላ ለን ፡ ሰው ፡ ተርከን ፡ ነገርናት ።

የሰውዬውን ፡ ታሪክ ፡ ስትሰማ ፡ ተጠራጠረችና ፤ የተፀፀተው ፡ በእውነት ፡ ከልብ ፡ ይሆን ? እንጃ ፡ አቅዋማችንን ፡ አጥንቶ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዳይዘምትብን ፤ በዓይን ፡ ቁራኛ ፡ መጠበቅ ፡ ሳያስፈልግ ፡ አይ ቀርም ፡ አለች ፤ ፀሐይ ፡ በማስተዋል ፡ የተናገረችውን ፡ አላቃለል ነውም ። ካሉን ፡ የሥራ ፡ አቅዋሞች ፡ ጊዜውን ፡ አጣቦ ፡ በሚይ ዘው ፡ እንዲሠራ ፡ አድርገን ፡ በቅርብ ፡ እንከታተለው ፡ ጀመር ። ሥራውን ፡ አክብሮ ፡ በጥብቅ ፡ መሥራቱን ፡ በሥራው ፡ መደሰቱን ፡ ልንገነዘብ ፡ በመቻላችን ፡ እንዲበረታ ፡ የምናቀርብለትን ፡ ምክር ፡ እየ ተቀበለ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አስተሳሰብ ፡ እንዲያውም ፡ ከኛ ፡ የበለጠ ፡ ሆነ ።

ዕውቀቱ ፡ የሚገበየው ፡ ከባዕድ ፡ መሆኑን ፡ አለመዘንጋትም ፡ ያስፈልጋል ፣ ሰው ፡ ለመሆን ፡ ጠንክሮ ፡ መሥራት ፡ የራስ ፡ ፈንታ ፡ ነው ። ራሱ ፡ ለራሱ ፡ ካላሰበ ፡ ሌላ ፡ አሳቢና፡ ተቈጣጣሪ፡ በዚያ ፡ ስፊሜዳ ፡ የለም ።

ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍለ ፡ ዓላማት ፡ ከተጠራቀሙ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ስንማር ፣ የሚበልጡት ፡ የየሀገራቸውን ፡ ባህል ፡ ጠብቀው ፡ ጥበብ ፡ ይቀስማሉ ፡ እንጂ ፣ ባህል ፡ እንደሌለው ፡ ሀገር ፡ ከሰው ፡ ባህል ፡ ጋር ፡ ተጣብቀው ፡ የራሳቸውን ፡ ልብስ ፡ አውልቀው፡ አይጥሉም ። ከአንዳንዶቹ፡ ጋር፡ ስንነጋገር ፡ የቋንቋ ፣ የሃይማኖት ፡ ችግር ፡ ኖሮብን ፡ ወደዚህ ፡ አልመጣንም ። ከዚህ ፡ የምንፈልገው ፡ ዘመናዊውን ፡ ጥበብ ፡ ለመቅዳት ፡ ስለሆነ ፡ ኃይላችንን ፡ አጠንክረን ፡ ማጥናት ፡ አለብን ። በዚህ ፡ የምንኖረው ፡ ለተወሰነ ፡ ዘመን ፡ ነው ፣ እንደወጣን ፡ አንቀርም ፣ ወደ ፡ አገራችን ፡ እንመለሳለን ። ወገኖቻችን ፡ ዓይናቸውን ፡ ከፍተው ፡ የሚጠብቁን ፡ ከነሱ ፡ የተሻለ ፡ ጥበብ ፡ ይዘንላቸው ፡ እንድንመለስ ፡ ነው ።

ባህል ፣ ሃይማኖት ፣ ቋንቋ ፡ ለውጠን ፡ ብንመለስ ፡ እንደዕብድ ፡ ከመቈጠር ፡ በቀር ፡ ሥፍራ ፡ የለንም ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብናፍር ፣ ብንፀፀት ፣ ዕድላችንን ፡ ራሳችን ፡ በራስችን ፡ ያበላሸነው ፡ ስለሆነ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ ይሉኝ ፡ ነበር ።

በዚህ ፡ አስተሳሰብ ፡ ብዙዎቹ ፡ ይጠቀሙበታል ። ከሀገራቸው ፡ ሲወጡ ፡ ያላቸውን ፡ ሰውነታዊ ፡ አቅዋም ፡ ጠብቀው ፡ ይራመዳሉ ፡ እንጂ ፣ ከዚያ ፡ ባዩት ፡ አይጠቀሙም ፡ ሲል ፡ ኪየገሩ ፡ ለትምህርት ፡ ወደአሜሪካ፡ የሄዱት፡ ተማሪዎች፡ ለጥበብና ፡ ለዕውቀት፡ ሕሊናቸውን፡ እንዳስገዙና ፡ እንደሚያስገዙ ፡ አስረዳን ።

ሞገሴ ፡ ሥራችንን ፡ በቅርብ ፡ እየተመለከተ ፡ ያልተጠበቀ፡ ርዳታ፡ በማበርከቱ ፡ ከሁሉም ፡ ምርቃት ፡ ተቀበለ ። ካሉን ፡ እቅዶች ፡ ብዙዎቹ ፡ ይቋቋሙ ፡ እንጂ ፡ የቀሩ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ። ትምህርት፡ ቤትና፡ ሆስፒታል ፡ ቅድሚያ ፡ ሊሰጣቸው ፡ ሲገባ ፡ ዘግይተዋል ፡ ብለን ፡ ስንነጋገር ፣ ትምህርት ፡ ቤትና ፡ ሆስፒታል ፡ ማቋቋም ፡ ቀላል ፡ አይደለም ። ለዚህ ፡ ለዓላማችን ፡ ሞገሴ ፡ ተገቢ ፡ ስለሚሆን ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ደመወዝ፡ ከፍለነው፡ ሥራውን፡ አቋቁሞ ፡ እንዲመራው ፡ ይጠየቅ ፡ ብሎ ፡ ከመካከላችን ፡ አንዱ ፡ አሳብ ፡ አቀረበና ፡ ሞገሴ ፡ ተጠርቶ ፡ ተጠየቀ ። ይህ ፡



ታላቅ ፡ ኃላፊነት ፡ እንደምን ፡ በኔ ፡ ላይ፡ ይጣላል ? ባሳየኸን፡ መልካም፡ ጠባይ ፡ እምነት ፡ አሳድረህብናልና ፡ አቋቁም ፡ አሉት ። እርሱም፡ እሺ፡ ብሎ ፡ አደራውን ፡ ተቀበለና ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ።

ትምህርትና ፡ ሕክምናን ፡ ከሚመሩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ እያደረገ፡ ሥራውን፡ የሚያቃልል፡ ጥናት ፡ አገኘና ፡ ሕንፃዎቹ፡ ተጀመሩ ።

የሕንፃዎቹ ፡ ሥራ ፡ ተጠናቆ ፡ ትምህርት ፡ ቤቱና ፡ ሐኪም ፡ ቤቱ ፡ አገልግሎት ፡ መስጠት ፡ ጀመሩ ። የትምህርት ፡ ቤቱና ፡ የሐኪም ፡ ቤቱ ፡ መቋቋም ፡ በአካባቢው፡ ሲሰማ ፡ ትምህርትና ፡ ሕክምና፡ ፈላጊው ፡ ግቢውን ፡ አጥለቀለቀው። መምህራንና ፡ ሐኪሞች ፡ በብዛት፡ ተቀጠሩ ።

ሞገሴ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ ስላደረበት ፡ ደስ ፡ እያለው ፡ በትጋት ፡ ሥራውን ፡ ያለዕረፍት ፡ ቀጠለ ። የወለደ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ለልጁ ፡ ማሰብ ፡ ስለማይቀር ፡ ሞገሴ ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ቢሆን ፣ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሐሳቡና ፡ የድካሙ ፡ ተካፋይ ፡ ትሆን ፡ ነበር ። አሁንም፡ ሚስት ፡ እንዲያገባ ፡ እንንገረውና፡ የምትሆነውን፡ እናፈላልግ፡ ብለን ፡ ተመካከርን ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ከራት ፡ በኋላ ፣ ትዳር ፡ መያዝና ፡ ልጅ ፡ መወለድ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሚገባ ፡ መሆኑን ፡ በተወያየንበት ፡ ጊዜ ፡ የሞገሴን ፡ ስሜት ፡ ለማወቅ ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡ እንሄድ ፡ ጀመር ፣ እርሱም ፡ ከሐሳቡ ፡ ጋር ፡ እንደሚጫወት ፡ ተከዘ ። ምነው ፡ ተከዝክ ? ሥራህ ፡ ብርቱ ፡ ነው፡ በሐሳብ ፡ የምትረዳህ፡ ጤንነትህንና፡ የዕረፍት፡ ጊዜህን፡ የምትቈጣጠር፡ ጓደኛ ፡ ታስፈልግሃለች ፡ አልነው ።

አሁን ፡ የማስበው ፡ ለሥራ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ በትጋት ፡ እሠራለሁ ፣ ሚስት ፡ ካገባሁ ፡ ያለኝ ፡ አስተሳሰብ ፡ እንደሚቀነስ ፡ ብታውቁልኝ ፡ እወዳለሁ ። ሚስት ፡ ካገባሁ ፡ እንኳን ፡ በዕረፍት ፡ ጊዜ ፣ ከደንበኛው ፡ የሥራ ፡ ሰዓት ፡ እየቀነስኩ ፡ ሚስቴን ፡ ማስደሰትና ፡ ፈቃድዋን ፡ ማሟላት ፡ አለብኝ ። ፈቃድዋን ፡ ካልፈጸምኩ ፡ የጠላኋት ፡ እየመሰላት ፡ ታዝናለች ፣ ሰላምም ፡ ትነሳኛለች ። በዚህ ፡ ላይ ፡ ልጅ ፡ ይወለዳል ። ያለ ፡ ውድ ፡ በግድ ፡ የልጅ ፡ አሽከር ፡ ሆኜ ፡ ስንከባከብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የማሳልፈው ፡ ጊዜ ፡ የተወሰነ ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጠን ።

ከፀሐይ ፡ ጋር ፡ እየተያየን ፡ መልስ ፡ ሳንሰጥ ፡ ዝም ፡ ባልናቸው ፡ ጊዜ ፡ ሞገሴና ፡ ሚስቱ ፡ አተኩረው ፡ እያዩን ፡ የምንሰጣቸውን ፡ መልስ፡ ተጠባበቁ ። እናንተ ፡ ከመጣችሁ ፡ ጀምሮ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የምናሳልፈው ፡ በዕረፍት ፡ ነው ። ወጣ ፡ ብለን ፡ ሀገር ፡ ስናይማ ፡ እንደገና ፡ መታደሳችን ፡ የታወቀ ፡ ነው ። የኅብረቱ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይዎችን ፡ አማክረን ፡ በሐሳቡ ፡ ሲተባበሩ ፡ እንዘጋጃለን ፡ ብለን ፡ መለስንላቸው ።

የኅብረቱን ፡ ሥራ ፡ ተባባሪዎች ፡ እናንተ ፡ ማማከር ፡ የለባችሁም ፡ እንነግራቸዋለን ፡ አሉን ።

በቀጠለው ፡ ቀን ፡ ለኅብረት ፡ ሥራ፡ ተባባሪዎች ፡ ቢያማክሯቸው፡ ሐሳቡን ፡ ደግፈው ፡ በቶሎ ፡ እንድንሄድ ፡ አደረጉ ።

የሚያስፈልገው ፡ ሁሉ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ወደ ፡ እሥራኤል ፡ ሄድን ። ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ለሰው ፡ ሥርየትን ፡ ለመስጠት ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ የሞተበትን ፡ ቀራንዮንና ፡ መካነ ፡ መቃብሩን ፡ ጎልጎታን ፡ ተሳልመን ፣ ቅዱሳት ፡ መካናትን ፡ በሙሉ ፡ በቅድሚያ ፡ ጐበኘን ።

የእሥራኤላውያንን ፡ ልማትና ፡ የሌሎችን ፡ የጐረቤት ፡ ሀገሮች ፡ ይዞታ ፡ ስናይ ፣ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ያህል ፡ የተራራቀበትን ፡ መመዘኛ ፡ መንገድ ፡ ስንፈልግ ፡ የመሬቱ ፡ ተፈጥሮ ፡ ልዩነት ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ አገኘነው ።

ይልቁንም ፡ እሥራኤላውያን ፡ ክረምትና ፡ በጋን ፡ ሳይለዩ ፡ በልዩ፡ የቧንቧ ፡ መጣሪያ ፡ እየተጠቀሙ ፡ ያለሙትን ፡ አትክልትና ፡ አዝርዕት፡ ሲመለከቱት ፡ ፊዞ ፡ መቅረት ፡ ነው ። ሀገሪቱን ፡ በኢኮኖሚ ፡ ከሚገነቡት ፡ የገቢ ፡ ምንጮች ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ የያዘው ፡ ከፍራፍሬ ፡ የሚገኘው ፡ ነው ፡ አለን ፡ ከገበሬዎቹ ፡ አንዱ ።

አንተ ፡ ገበሬ ፡ ሁነህ ፡ ሳለ ፡ ጠቅላላውን ፡ የኢኮኖሚ ፡ አቅዋም ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ማወቅ ፡ ቻልክ ፡ ብንለው ፣ የሀገሪቱ ፡ ተወላጅ ፡ የሆን ፡ ሁሉ ፡ ሀገራችንን ፡ ለሚመለከት ፡ በሁሉም ፡ አቅጣጫ ፡ ለሚቀርብልን ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ እንችላለን ።

እኔ ፡ ገበሬ ፣ ሌላው ፡ ወታደር ፣ ሌላውም ፡ የፖለቲካ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ቢሠማራም ፣ ችሎታው ፡ በፈቀደለት ፡ ለሀገሩ ፡ እኩል ፡ አገልግሎት ፡ ይሰጣል ። ሀገሪቱ ፡ በበኩሏ ፡ የምትሰጠውን ፡ እኩል ፡ ስለምንካፈል ፣ ጉዳይዋንም ፡ በእኩልነት ፡ ደረጃ ፡ እየተካፈልን ፡ በባለቤትነት ፡ ደረጃ ፡ እንመልሳለን ፡ አለን ።



የአዝመራቸው ፡ ወቅት ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ እንደሆነ ፡ ለጠየቅነውም ፣ የተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ የለውም ። በበጋም ፡ ሆነ ፡ በክረምት ፡ ልምላሜ ፡ አናጣም ። ሀገራችን ፡ ዘወትር ፡ በልምላሜ ፡ ያጌጠች ፡ ናት ። በበጋና ፡ በክረምት ፡ የምናዘምረው ፡ አዝመራ ፡ የተለያየ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አስረዳን ።

የሀገሩን ፡ ጠቅላላ ፡ የተፈጥሮ ፡ አቀማመጥና ፡ ልማቱን ፡ እያየን ፡ ስንጓዝ ፣ ለሕዝብ ፡ መሥፈሪያ ፡ የሚሆኑ ፡ ቤቶች ፡ ሲሠሩ ፡ አየን ። ጐራ ፡ ብለን ፡ ስንመለከት ፣ ትምህርት ፡ ቤት ፣ ሐኪም ፡ ቤት ፣ መዋኛ ፣ ሱቅ ፣ ሆቴል ፣ የሲኒማ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ አጠቃሎ ፡ የያዘ ፡ መሆኑን ፡ ሥራውን ፡ የሚያሠራው ፡ ገለጣ ፡ አደረገልን ።

ወጪውን ፡ ብንጠይቅ ፣ በዚህች ፡ ሀገር ፡ የምታዩትን፡ ማናቸውም፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራው ፡ «ኪቡት፡ » የተባለው ፡ ድርጅት ፡ ነው ።

ሠራተኞቹ ፡ በድርጅቱ ፡ ማቢያ ፡ እያደሩና ፡ እየተመገቡ ፡ ስለሚሠሩ ፣ በሀገሪቱ ፡ ምድር ፡ የምታዩት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማት ፡ ከዚህ ፡ ደርሰዋል ። ድርጅቱም ፡ በሀገሪቱ ፡ ምድር ፡ በብዛት ፡ ተቋቁሞ ፡ ሀገሪቱን ፡ ሀገረ ፡ ገነት ፡ አድርጓታል ። « የኪቡትን ፡ » ሥራ ፡ አመሠራረትና ፡ የሥራ ፡ ግዳጁንም ፡ ጠለቅ ፡ ብላችሁ ፡ ማወቅ ፡ ከፈለጋችሁ ፡ ይህን ፡ አንቡ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ ሰጠን ።

ጉብኝታችንን ፡ አጠቃለን ፡ ወደ ፡ ቤይሩት ፡ ሄድን ፣ የቤይሩትን ፡ ከተማ ፡ ከጐበኘን ፡ በኋላ ፣ የፓላስታይንን፡ ስደተኞች ፡ ሠፈር ፣ ከፊሊቂያኖች ፡ ከተሞች ፡ አንዱ ፡ የነበረውን ፡ የባቢሎንን፡ ሕንፃ ፡ ጐብኝተን፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ሄድን ። የደማስቆን ፡ ከተማና ፡ አካባቢውን ፡ አይተን ፡ ካይሮ ፡ ከተማ ፡ ገባን ። በካይሮ ፡ ፒራሚዱንና ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተነሥቶ፡ የካይሮን ፡ ከተማ ፡ ከሁለት ፡ ላይ ፡ ከፍሎ ፡ የሚያልፈውን ፡ ትልቁን ፡ የዓባይን ፡ ወንዝ ፡ ዐይተን ፡ አቴንስ ፡ ከተማ ፡ ገባን ።

በአቴንስ ፡ ከተማ ፡ አክሮፓሎስን ፣ የሂናሲዎስ ፡ የትያትር ፡ ሥፍራና ፡ የፊሌፕፑስን ፡ ተራራ ፡ የፓሳይዳን ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ጐበኘን ። ከዚህ ፡ በኋላ ፣ ጀርመንን ፣ ፓሪስን ፡ ሮምን ፡ ጐበኘን ። በሮም ፡ ቫቲካንና ፡ ታሪካዊ ፡ ሥፍራዎችን ፡ ስንመለከት ፣ ሚካኤል ፡ አንጀሎ ፡ በሳላቸው ፡ ሥዕሎች ፡ ልባችን ፡ ተነካ ።

ለሰው ፡ ፍላጎት ፡ መግቻው ፡ በቃኝ ፡ ስለሆነ ፣ ሁሉንም ፡ ማዳረስ ፡ አንችልም ፣ ቢሆንም ፡ ብዙ ፡ ሀገሮች ፡ ዐየን ። ዓለም ፡ ወረቀት ፡ ስለሆነች ፣ በዚህም ፡ በዚያም ፡ ያለውን ፡ ቀለም ፡ ትቀበላለች ።

የእሥራኤላውያን ፡ የልማት ፡ አቅዋም ፡ አስደንቆናል ፤ ክረምት ፡ ከበጋ ፡ አዝመራ ፡ አይለያቸውም ። በክረምት ፡ የሚያዘምሩት ፡ የተለየ ፡ ነው ። «ኪቡት፡ » የሚባለውን ፡ ድርጅት ፡ የሥራ ፡ አቅዋም ፡ የሚገልጸው ፡ መጻሕፍት ፡ ትምህርት ፡ ይሰጣል ። ለሞገሴ ፡ በበለጠ ፡ ይጠቅመዋል ። ወደሀገራችን ፡ እንመለስና ፡ በእሥራኤላውያን ፡ «የኪቡት፡ » አቅዋም ፡ እንደምን ፡ አድርገን ፡ መጠቀም ፡ እንደምንችል ፡ እናጥና ፡ ብለን ፡ ወደሀገራችን ፡ ተመለስን ።

በፍቅር ፡ የሚመለከቱን ፡ በዛ ፡ ያሉ ፡ ስለሆኑ ፤ በጋለ ፡ ደስታና ፡ ፍቅር ፡ ተቀበሉን ። በጉብኝታችን ፡ ያየነውንና ፡ ልባችን ፡ የተመሰጠበትን ፡ ለሞገሴና ፡ ለሚስቱ ፡ ነገርናቸው ። በጽሞና ፡ አዳምጠው ፡ የኅብረቱ ፡ ድርጅት ፡ ተካፋይዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ ጭምር ፡ ባሉበት ፡ ገለጣ ፡ እንድናደርግ ፡ አሳሰቡን ።

ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ እሑድ ፡ ስብሰባ ፡ ተደረገ ፤ በጉብኝታችን ፡ ጊዜ ፡ ከጀመርንበት ፡ እስከፈጸምንበት ፡ ድረስ ፡ ያየነውን ፡ ተናገርን ። የእሥራኤላውያን ፡ ሀገር ፡ በረሃማ ፡ ደረቅ ፡ አሸዋ ፡ ሆኖ ፤ በመሥራታቸው ፡ ሀገራቸውን ፡ ሀገረ ፡ ገነት ፡ አድርገዋታል ። የሀገሪቱን ፡ የልማት ፡ አቅዋም ፤ ከምድርዋ ፡ የሚገኘውን ፡ የአዝርዕትና ፡ የዕፀዋት ፡ በረከት ፤ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማስረዳት ፡ ቃላት ፡ ያንሰናል ። ልምላሜውና ፡ ፍራፍሬው ፡ ሰውን ፡ ይማርካል ። በአድናቆት ፡ የሚታየውን ፡ ልማት ፡ የሚሠራው ፡ « ኪቡት ፡ » የሚባል ፡ ድርጅት ፡ ነው ።

ክረምት ፡ ከበጋ ፡ ያዘምራሉ ። በክረምትና ፡ በበጋ ፡ የሚያዘምሩትን ፡ አዝርዕትና ፡ ዕፀዋት ፡ ከጊዜው ፡ ጠባይ ፡ ጋር ፡ የተለያየ ፡ ነው ። በነሱ ፡ የግብርና ፡ ሞያ ፡ ለመጠቀም ፤ በመካከላቸው ፡ ተገኝቶ ፡ ማጥናት ፡ ያስፈልጋል ። ካሉን ፡ ሠራተኞች ፡ ልከን ፡ ቢሠለጥኑ ፡ ዛሬ፡በዚያ፡ ያየነውን ፡ ነገ ፡ በዚህ ፡ እናያለን ፡ አልናቸው ።

ከስብሰባው ፡ ተካፋይዎች ፡ አንዱ ፤ የናንተ ፡ ሐሳብ ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ አልቀረም ። ሥራ ፡ መስክርዋልና ፡ አሁንም ፡ በሥራ ፡ ይገለጥ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በጭብጨባ ፡ ሐሳቡ ፡ ተደገፈ ።

ከሠራተኞቹ ፡ የሚልኩትን ፡ መርጠና ፡ ሌላውንም ፡ አሟልቶ ፡ ሞገሴ ፡ እንዲልክ ፡ አደራ ፡ ተጣለበት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በናንተ ፡ መካከል ፡ መሥራትን ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዳለሁ ፡ እቈጥረዋለሁ ።



ከመማር ፤ ከማየት ፡ ከመስማት ፡ የሚገኘው ፡ ዕውቀት ፡ የሚለካው ፡ በሥራ ፡ ነው ፡ አለና ፡ ሞገሴ ፡ ስብሰባው ፡ አበቃ ።

ከሠራተኞቹ ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ ተመርጠው ፡ ቋንቋ ፡ እንዲያጠኑ፡ አደረገ ። ከሚቀበላቸው ፡ ሀገር ፡ ጋር ፡ ተጻጽፎ ፡ ለማሠልጠን ፡ እንደሚቀበሏቸው ፡ ተረጋገጠ ፤ ለመንገድ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ሞገሴ ፡ ይዟቸው ፡ ሄደ ።

በወዳጅነት ፡ ተቀበልዋቸው ፤ ጥናት ፡ ከመጀመራቸው ፡ በፊት ፡ ሁሉንም ፡ አስጐበኝዋቸው ። ጥናት ፡ ሲጀምሩ ፡ ሞገሴ ፡ ወደሀገሩ ፡ ተመለሰ ። የእሥራኤላውያንን ፡ የልማት ፡ ዕድገት ፡ ገብይቶ ፡ እነርሱን ፡ ለመምሰል ፡ ከመጣጣር ፡ በቀር ፤ ይኸ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መናገሩ ፡ አቅዋምን ፡ አይለውጥም ።

ሠራተኞቻችን ፡ የበሰለ ፡ ጥናት ፡ ይዘው ፡ ይመለሳሉ ፤ በሚመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ መሣሪያና ፡ ሥራውን ፡ የሚመሩ ፡ ባለሞያዎች ፡ አብረው ፡ እንደሚልኩልን ፡ የተነጋገረበት ፡ መሆኑን ፡ ሞገሴ ፡ ገልጦ ፤ ሠራተኞቻችን ፡ ጥናታቸውን ፡ በሥራ ፡ የሚገልጡበት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ውሃ ፡ ገብ ፡ መሬት ፡ ያስፈልጋቸዋል ፡ በማለት ፡ አመለከተን ።

ጫካ ፡ የለበሰ ፡ ድንግል ፡ መሬት ፡ ሞልቷል ፤ የተንጣለለውን ፡ ሜዳ ፡ ጫካውን ፡ መንጥረን ፡ መሥራት ፡ እንችላለን ። ይኸውም ፡ የሚገኘው ፡ ቆላማ ፡ በሆነ ፡ ሥፍራ ፡ ስለሆነ ፤ ቆርጦ ፡ መዝመት ፡ ያስፈልጋል ፡ አለ ፡ ከአዳማጮቹ ፡ አንዱ ።

ለማሰብ ፡ ጊዜ ፡ አለን ፤ ሁላችንም ፡ በሐሳብ ፡ በመተባበራችን ፡ ከዚህ ፡ ደርሰናል ። ለሰው ፡ ልጅ ፡ ዋናው ፡ መሣሪያ ፡ መተባበር ፡ ነው ። ይህ ፡ ሁለተኛ ፡ የሥራ ፡ እቅድ ፡ ከግባችን ፡ እንዲደርስ ፡ ሥራውን ፡ ስለምናቋቁምበት ፡ መሬት ፡ እንጠያየቅ ፡ ተባብለን ፡ ተለያየን ።

የኅብረቱ ፡ የሥራ ፡ ድርጅት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድና ፡ በኛም ፡ ብርታት ፡ እያደገ ፡ ስለሄደ ፡ ከዚህ ፡ ደረጃ ፡ አይደርስም ፡ ብለው ፡ አስቀድሞ ፡ የሸሹት ፤ በሥራው ፡ እድገት ፡ እየቀኑ ፡ ጥፋቱን ፡ ይመኙ ፡ ነበር ። ስለዚህም ፡ የቅናትና ፡ የምቀኝነት ፡ ቅንቅን ፡ እያደረ ፡ እየበላቸው ፡ የባሰውን ፡ ጤና ፡ አጡ ።

የኀብረቱን ፡ ሥራ ፡ የመሠረቱትንና ፡ ሠራተኞቹንም ፡ በቅናትና ፡ በምቀኝነት ፡ በተመረዘ ፡ እንደበታቸው ፡ ይነድፏቸው ፡ ጀመር ። ከሥራው ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ የማይነካውን ፡ ሞገሴንም ፡ በበለጠ ፡ በነገር ፡ ለማበሳጨት ፡ ሞከሩ ። ደም ፡ ፈሶ ፡ ሥራችን ፡ እንዲሰናከል ፡ አጥብቀው ፡ ጣሩ ። በኃይል ፡ መጠቀም ፡ ቢያስፈልግ ፡ ኖሮ ፤ ከነርሱ ፡ ይልቅ ፡ የኛ ፡ ክንድ ፡ የበረታ ፡ ነበር ። በመካከሉ ፡ ነገሩ ፡ ወደሕግ ፡ አመራ ፤ እኛን ፡ በደለኞች፡ ያደረጉበት ፡ ዘዴ፡ ከሽፎ ፡ የነገሩ ፡ መሥመር ፡ ወደ፡ ነርሱ ፡ ስለተቀየሰ ፡ የማያውቁትና ፡ ያልጠበቁት ፡ ችግር ፡ በቤተሰቦቻቸው ፡ ላይ ፡ ደረሰና፤ ነገራችንን ፡ እንድንተው ፡ ጠየቁን። ከብዙ ፡ ትዕግሥት ፡ በኋላ ፡ የወሰድነው ፡ እርምጃ ፡ ነውና ፤ እንተውም ፡ ብለን ፡ ጨከን ። ልጆቻቸው ፡ በቀያችን ፡ ፈሰው ፡ አለቀሱብን ። ምን ፡ እና ድርግ ፡ በልጅ ፡ አንጨክን ፡ ልጆች ፡ አሉን ፤ የሰቀልነውን ፡ እንደገና ፡ እናውርድ፡ ብለን፤ የሚነጋገረውን ፡ ወኪላችንን ፡ ጠርተን ፡ አማከርን።

እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ካሁን ፡ ቀደም ፡ ዋስ ፡ ጠርተዋል ፤ አሁንም ፡ የሚለቀቁት ፡ በዋስ ፡ ነው ። ነገርን ፡ አይቶ ፡ ማለፍ ፡ የትልቅነት፡ምልክት ፡ ነው ። ነገር ፡ አለብን ፡ ከማለት ፡ ሥራ ፡ አለብን ፡ ማለት ፡ ይመረጣል ። ታዳጊ ፡ ሀገሮችም ፡ ፍርድ ፡ ቤትና ፡ እሥር ፡ ቤት ፡ አላቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በበለጠ ፡ ዋጋ ፡ በሌለው ፡ ጥቃቅን ፡ ምክንያት ፡ እንደበግ ፡ ሰዎች ፡ አይታጎሩም ።

ማስረጃ ፡ ከመሰማቱ ፡ በፊት ፡ ነገሩን ፡ መተው ፡ ተገቢ ፡ ነውና ፡ ሕግን ፡ ተመርኩዤ ፡ ክርክሬን ፡ አነሣለሁ ፡ አለ ፡ ወኪላችን ።

ተቃዋሚዎቻችን ፡ ከቤታቸው ፡ ገቡ ። ልጆቻቸውና ፡ ቤተሰቦቻቸው ፡ ከቀያችን ፡ ድረስ ፡ መጥተው ፡ አመሰገኑን ። ይሁን ፡ እንጂ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ የሸመቁት ፡ ስላልተፈጸመ ፡ አሁንም ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ እንደሚፈልጉ ፡ በግንባራቸው ፡ ላይ ፡ የሚነበበው ፡ ሁኔታቸው ፡ ይመሰክርባቸው ፡ ነበር ። ይበልጡን ፡ ጥላቻቸውን ፡ ያጠነከሩት ፡ በኔና ፡ በፀሐይ ፡ ላይ ፡ ነበር ።

በወር ፡ ሁለት ፤ በአሥራ ፡ አምስት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከኅብረቱ፡የልማት ፡ ድርጅቶች ፡ ጋር ፡ ቀዋሚ ፡ ስብሰባ ፡ ይደረጋል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የኅብረቱን ፡ የልማት ፡ ድርጅት ፡ ያቋቋምንበት ፡ ኻያ ፡ አምስተኛ ፡ ዓመት ፡ እንዲከበር ፡ ተነጋገርንና ፤ የአከባበሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት፡ እንዲጠና ፡ ንዑስ ፡ ጉባኤ ፡ በሞገሴ ፡ ሰብሳቢነት ፡ ተቋቋመ ።



ቀኑም ፡ ደረሰ ፤ ዝግጅቱ ፡ ከታሰበው ፡ በላይ ፡ ተከናወነ ፡ ከበዓሉ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ በፊት ፡ መግለጫ ፡ ተሰጠ ። በመግለጫው ፡ ላይ ፡ በመልካችን ፡ ተቀርፆ ፡ የቆመ ፡ መታሰቢያ ፡ የሚገለጥ ፡ መሆኑ ፡ ተጽፏል ፤ ለሚወዱን ፡ ደስታ ፤ ለሚጠሉን ፡ ግን ፡ በሽታ ፡ ሆነ ።

በዓሉ ፡ ሊከበር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሲቀር ፤ የኅብረቱ ፡ ልማት ፡ መሥራቾች ፡ ዝግጅቱን ፡ ጐበኙ ። በሞገሴ ፡ የሚመራው ፡ ጉባኤ ፡ ዝግጅቱን ፡ በማሟላት ፡ ተመሰገነ ። በኻያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ጊዜ፡ውስጥ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ የሚለካበት ፡ ታላቅ ፡ በዓል ፡ ስለነበር ፡ የክብር ፡ ልብሳችንን ፡ ለብሰን ፡ የውጪ ፡ እንግዳ ፡ ከመምጣቱ፡ ቀደም ፡ ብለን፡ ተገኘን ። ጥሪ ፡ የደረሳቸውና ፡ ዜናውን ፡ ሰምተው ፡ የበዓሉን ፡ አከባበር ፡ ለማየት ፡ ፍላጎት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ በብዛት ፡ በመምጣታቸው ፡ ለእንግዶች ፡ መቀመጫ ፡ በስፋት ፡ የተዘጋጀው ፡ ሥፍራ ፡ በጣም ፡ ተጣበበ ።

በዓሉን ፡ የምንከፍት ፡ እኔና፡ ፀሐይ ፡ በመሆናችን ፤ በተዘጋጀልን፡ ልዩ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀመጥን ። የበዓሉን ፡ ታሪክና ፡ ዝግጅት ፡ ሞገሴ፡ ተናገረ ። ቀጥሎ ፡ በመሥራቾቹ ፡ ስም፡ እንዲናገር ፡ የተመረጠው ፡ ስለኛ፡ ጥረት ፡ በሰፊው ፡ ተናገረ ። ሦስተኛው ፡ ተናጋሪ ፡ የልማቱ ፡ ድርጅት፡ በገቢና ፡ በወጪ ፡ ያደረገውን ፡ የገንዘብ ፡ ንቅናቄ ፤ በንብረት ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ሀብት ፡ በመዘርዘር ፡ አጥጋቢ ፡ መግለጫ ፡ ሰጥቶ፡ መጽሐፍ፡ ታደለ ።

ምንም ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ ብናውቀውም ፡ በሥራው ፡ ኃላፊ ፡ አንደበት ፡ ሲነገር ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለን ። የመንፈስ ፡ ኵራትም ፡ ተሰማን ። የመጨረሻው ፡ ተናጋሪ ፡ እኔ ፡ እንድሆን ፡ በፕሮግራሙ ፡ ላይ ፡ ተመልክቶ ፡ ስለነበር ፤ ከልማቱ ፡ የተገኘውን ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ የሥራው ፡ ኃላፊ ፡ ገልጦታል ።

ከተሰማን ፡ ደስታ ፡ አንዱ ፤ በሥራ ፡ እጦት ፡ ወደመጥፎ ፡ ተግባር ፡ ይመሩ ፡ የነበሩ ፡ ሥራ ፡ ይዘው ፡ ከመጥፎ ፡ ባሕርይ ፡ ታርመው ፡ በሥራ ፡ መሠማራታቸው ፡ ነው ። በዚህ ፡ በልማት ፡ ጣቢያ ፡ መቆም ፡ የሚገባው ፡ የኛ ፡ መታሰቢያ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የኅብረቱን ፡ የልማት፡ ሥራ ፡ ስናቋቁም ፡ በጎ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ለግሰው ፤ ኻያ ፡ አምስት ፡ ዓመታት ፡ ድረስ ፡ በመካከላችን ፡ ቅሬታ ፡ ሳይኖር ፡ ለሠሩት ፡ ጭምር ፡ ሊቆም ፡ ይገባል ፡ ብዬ ፡ ንግግሬን ፡ ስጨርስ ፤ ባለማቋረጥ ፡ ተጨበ

ጨበ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ አልፈን ፡ የተዘጋጀውን ፡ ኤክስፖሲዚዮን ፡ ከፈትን ። ወደዚያው ፡ ሕዝቡ ፡ ከቦን ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ አላችሁ ፡ እያለ ፡ ፀሐይንና ፡ እኔን ፡ ሲጨብጥ ፡ « የገበያ ፡ ግርግር ፡ ለቀጣሬ ፡ ይመቻል፡ » እንደሚባለው ፡ በምቀኝነትና ፡ በመጥፎ ፡ ቅናት ፡ ከተመረዙት ፡ ተቃዋሚዎች ፡ አንዱ ፤ በጨቤ ፡ ወግቶኝ ፡ ሲሸሽ ፡ ተያዘ ፤ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ገባሁ ፤ በሰው ፡ ዕውቀት ፡ ሊደረግ፡ የሚቻለው ፡ ተደረገልኝ ፤ አቆሳሰሉ፡ አደገኛ፡ ስለነበረ ፡ ሕመሙ፡ እየባሰብኝ ፡ ሄደ ። ሕይወቴ ፡ ከማለፉ ፡ በፊት ፡ መናዘዝ ፡ ይገባኛል ፡ ብዬ ፡ አሰብሁ ። ኑዛዜዬን ፡ በግልጥ ፡ ለማድረግ ፡ አስቤ ፡ የድምፅ ፡ መቅጃ ፡ ቴፕሪኮርደር ፡ እንዲመጣልኝና ፡ ድምፄ ፡ እንዲቀዳ ፡ አዘዝኩ ። የኅብረቱ ፡ ልማት ፡ተካፋዮች ፤ ፀሐይንና ፡ ልጆቼን ፤ የውጪ ፡ ታዛቢዎችንም ፡ ጭምር ፡ አስጠርቼ ፡ ቃሌን ፡ ሰጠሁ ።

የሐሳባችን ፤ የድካማችንና ፡ የሥራችን ፡ ተካፋይዎች ፡ ወንድሞቼ ፤ ከምወዳት ፡ሚስቴና ፡ ከልጆቼ ፡ ስለማለያችሁ ፡ እንደበቴ ፡ በሞት ፡ ከመታሠሩ ፡ በፊት ፡ የምነግራችሁን ፡ አዳምጡ ፡ ባልኩ፡ጊዜ፡ ለቅሶ ፡ በለቅሶ ፡ ሆነ ፤ በመካከል ፡ እኔን ፡ ድካም ፡ ተሰማኝ ። ያሰብኩትን ፡ ሳልናገር ፡ መለያየታችን ፡ ስለሆነ ፤ እባካችሁ ፡ አዳምጡኝ ፡ አልኳቸው ። ሁሉም ፡ ከሲቃው ፡ ጋር ፡ እየታገለ ፡ ንግግሬን ፡ ማዳመጥ ፡ ጀመረ ።

ልጆቼ ፡ እናታችሁን ፡ ጠብቅዋት ፤ እስካሁን ፡ ከፈቃዳችን ፡ አልወጣችሁም ። ከናታችሁ ፡ ዕድሜ ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ የልማት ፡ ድርጅት ፡ ኃላፊነትና ፡ አደራ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የተጣለ ፡ ነው። ሞገሴ፡ እኔን ፤ ቡርክት ፡ ፀሐይን፡ መስላችሁ ፡ የምትመሩት ፡ ከናንተም ፡ በኋላ ፡ የናንተ፡ ልጆች ፡ በዚሁ ፡ ደረጃ ፡ የሚከተሉት ፡ እንጂ ፤ በአንድ ፡ ትውልድ ፡ የሚወሰን ፡ አለመሆኑን ፡ አስተውላችሁ ፡ ድርጅቱ ፡ እንዲጠነክር ፡ አድርጉ ፡ ካልኳቸው ፡ በኋላ ፡ ብርቱ ፡ ድካም ፡ እየተሰማኝ ፡ መናገር ፡ ተሳነኝ ። ከመልአከ ፡ ሞት ፡ ጋር ፡ ሲታገል ፡ የሰነበተው ፡ ሰውነቴ ፡ እያደረ ፡ እየከዳኝ ፡ ሄደ ። እኔም፡ ተስፋ ፡ ቆርጬ ፡ የሕይወት ፡ ገመዴን፡ መቈረጥ ፡ ስጠባበቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት፡ ይሁን ፡ በሕክምናው፡ ርዳታ ፡ ምክንያት ፡ ሕይወቴ ፡ ተርፎ ፡ ከሐኪም ፡ ቤት፡ ወጥቼ፡ ይህን፡ ጽፌ፡ ለማስተላለፍ ፤ ባላጋራዬ ፡ ሕጋዊ ፡ ቅጣቱን ፡ ተቀብሎ ፡ በወህኒ፡ ቤት ፡ እንዳለ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ሕመም ፡ መሞቱን ፡ ለመስማት ፡ በቃሁ።



# መሥራት ፡

መማር ፤ መመራመር ፡ ዐውቆ ፡ ለማሳወቅ ፤
መልካም ፡ ዓላማ ፡ ነው ፤ ግን ፡ በመንደላቀቅ ፤
ይህን ፡ ዐየሁ ፡ ብሎ ፡ አይበቃም ፡ መደነቅ ።

ከመደነቅ ፡ ይልቅ ፤ ለመሥራት ፡ መጣጣር ፤
አንድ ፡ ቀን ፡ አይቀርም ፡ ውጤቱ ፡ ሳያምር ።

ሰማን ፡ በጆሮአችን ፡ በዓይናችን ፡ ዐየን ፤
መግለጥ ፡ ነው ፡ በሥራ ፡ የኛ ፡ ተስፋችን ፤
ለመግለጥ ፡ በሥራ ፡ ይጽና ፡ ኃይላችን ።

ሕልማችን ፡ ሠመረ ፤ ሥራችን ፡ አማረ ፤
አልቀረም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሁሉም ፡ ተባበረ ።

ከተባበረ ፡ ሰው ፤ በአንድነት ፡ ከጸና ፤
ለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ አያጣም ፡ ዋስትና ።

ለኃይላችን ፡ ጽናት ፡ ለኅብረታችን ፤
መተማመኛችን ፡ ሆኗል ፡ ጋሻችን ።

እምነት ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ የመዳኛ ፡ ተስፋ ፤
ጸንተን ፡ በዚሁ ፡ ላይ ፡ ሥራችን ፡ ይስፋፋ ።

አስበን ፡ አሳስበን ፤ የተነሣንበት ፤
ሆኖ ፡ አልቀረም ፡ ከንቱ ፡ ሰጠን ፡ አያሌ ፡ ምርት ።

በሐሳባችን ፡ ውስጥ ፡ የተዘረጋው ፤
ገና ፡ አልተጀመረም ፡ በውጥን ፡ ላይ ፡ ነው ።

ቢሆንም ፡ አልቀረ ፡ ሁሉም ፡ ተጀምሯል ፤
ያለው ፡ አሳባችን ፡ ደግሞም ፡ ይቀጥላል ።

የሥራ ፡ ግባችን ፡ ዓላማችንም ፤
ይቀጥላል ፡ እንጂ ፡ ጭራሽ ፡ አይቆምም ።

የሥራ ፡ ዓላማችን ፡ አይለቅም ፡ ግቡን ፤
እንይ ፡ እንመልከት ፡ መልካም ፡ ፍሬውን ።

ለመሥራት ፤ ለማግኘት ፣ አንዳንድ ፣ ያልታደሉ ፤
ፍሬውን ፣ ለመቅጨት ፣ ያገበግባሉ ።

ዳሩ ፣ ግን ፣ ከንቱ ፣ ነው ፤ ከንቱ ፣ መታከት ፣
የተነሣ ፣ ቆርጦ ፣ እያውቅም ፣ ስንፈት ።

ትዕግሥት ፣ አሸናፊ ፣ የታወቀ ፣ ጀግና ፤
ይዘልቃል ፣ ይሄዳል ፣ በሥራ ፣ ጐዳና ።

ነፍስ ፣ ጡር ፣ ነው ፣ አሳብ ፣ በምጥ ፣ ይጨነቃል ፤
ሲሟላ ፣ ጊዜው ፣ ግን ፣ ሁሉም ፣ ይወለዳል ።

ተነሣን ፣ በምኞት ፣ በሐሳብ ፣ ሩጫ ፤
አይመስለንም ፣ ነበር ፣ የምናገኝ ፣ መውጫ ።

ነገር ፣ ግን ፣ አልቀረም ፣ ተሳካ ፣ በሙሉ ፤
ዓየን ፣ ተከናውኖ ፣ ምኞታችን ፣ ሁሉ ፤
በቀላሉ ፣ አይወድቁም ፣ ሰዎች ፣ ከታገሉ ።

**ተ ፈ ጸ መ ።**





ደ ራ ሲ ው